ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አንድ

(ፉአድ ሙና)

.

.

ይገርማል ወደዚህች ምድር ከመጣሁ አስራዘጠኝ ዓመታቶች

ነንዱ ማለት ነዉ? እዚህች ምድር ከመጣሁ በልጅነት እንደ ልጅ

ከልጆች ጋር የተጫወትኩበት ፣ የእሳቱ እድሜ ደርሶ ልቤ አብጦ

ቤት ማንንም አልታዘዝም ያልኩበት እና ህይወትን ለመረዳት

የሚያስፈልጉ ወሳኝ ነጥቦችን የተረዳሁበት እድሜ ነንደ። አሁን

ወደ ሀያኛ አመት ሩጫዉን ተያይዤዋለሁ።

በነዚህ ዓመታት ዉስጥ በህይወቴ ዉስጥ ብዙ ሰዎች አልፈዋል።

ብዙ የማይረሱ ተወዳጅ እና አናዳጅ ሰዎችን አዉቄያለሁ። አስራ

አምስት ዓመታትን መጨረሻዬን በመናፈቅ በትምህርት

አሳልፌያለሁ።

.

አሁን የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነኝ። ስሜ ፈዉዛን ይባላል። ጠይም እና

ተጫዋች ነኝ። ቁምነገር ላይ ቁምነገረኛ ፣ ቀልድ ላይ ደግሞ

ምርጥ ቀልደኛ ነኝ። በራሴ በጣም አተማመናለሁ። ብዙ ሰዎች

ጢባራም ነህ ይሉኛል። ከሩቅ ሲያዩኝ የሚጠሉኝ ቀርበዉ

የሚያዉቁኝ ደግሞ የሚወዱኝ አይነት ሰዉ ነኝ። ስለራሴ

እንደዚህ በድፍረት የማወራዉ ብዙዎች ከቀረቡኝ በኋላ ምን

ያህል ከሩቅ ሲያዉቁኝ ይጠሉኝ እንደነበር እና ሲቀርቡኝ እና

ሲያዉቁኝ በጣም እንደወደዱኝ በተደጋጋሚ ስለሚነግሩኝ ነዉ።

ለራሳችን ያለን አመለካከት ከሚገነቡበት መንገዶች አንዱ ሰዎች

ስለኛ በሚነግሩን ነገር ላይ የተመሰረተ መሆኑ እሙን ነዉ። ለዛ

እኮ ነዉ ቤተሰብ እምነት የሚጥልባቸዉ ልጆች ፣ ሁሌም

ጀግንነታቸዉን የሚነግራቸዉ ታዳጊዎች ከከፍታ መሰላል ላይ

ቆመዉ የምናየዉ። በአንባሩ ደግሞ አታዉቅም እየተባሉና

ትንሽነታቸዉ እየተነገራቸዉ ያደጉ ልጆች ትንሽ እንደሆኑ ይቀራሉ።

በእርግጥ እየተሞገሱ የሚቀሽሙ እንደሚኖሩት ሁላ ከዚህ

የትንሽነት ቀንበር አምልጠዉ ታላቅ የሚሆኑ ጥቂቶችም

አይጠፉም።

.

እኔ ፈዉዛን ካመንኩበት ነገር ላይ ወደኋላ ዝንፍ አላዉቅም።

እንደወራጅ ዉሀ በተቀደደላቸዉ እንደሚፈሱ ከንቱ ሰዎች አሊያም

ወደነፈሰበት እንደሚነፍሱ ገለባዎች አይነት አይደለሁም። ሰዉ

ነኝ!! እንቢ የማለት አቅም አለኝ። ከአስተሳሰቤ እና ከማንነቴ ጋር

የሚጣረስን ነገር እምቢ ከማለት ወደኋላ አልልም። ሁሌም ቃሙ

ሲሏቸዉ ገረባ ሳይቀር የሚያኝኩ ፣ ጠጡ ሲሏቸዉ ፋራ

ላለመባል አተላ የሚጋቱ ፣ አጭሱ ሲሏቸዉ ከማን አንሼ ብለዉ

ኦ በጭስ ለመስራት አይናቸዉ ተጎልጉሎ እስከሚወጣ

የሚያጨሱ ምስኪን፣ እንቢ የማለት ወኔያቸዉ የተሰለበ ፣

የመጣዉ ጎርፍ ሁሉ እያላጋ የሚወስዳቸዉ፣ የማንነታቸዉን

ልዕልና ያላከበሩ ሰዎች ያሳዝኑኛል። በእንደዚህ አይነት ሰዎች

መካከልም ተከብቤ እነሱ የመጣዉ ጎርፍ ሁላ ሲያላጋቸዉ እኔ

በዕናት ቆሜ አዉቃለሁ። ለዛ ነዉ በድፍረት እንቢ የማለት አቅም

አለኝ የምለዉ።

.

በተማርኩባቸዉ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ሁሉ ዝነኛ ነበርኩ።

የትምህርት ቤት ክበባት ውስጥ መሳተፍ አዘወትር ነበር።

ስነፅሁፍ እወዳለሁ። አንዳንዴ እሞነጫጭራለሁ ብዙ ጊዜ ግን

የሌሎችን የስነ ፅሁፍ ስራዎች መድረክ ላይ ማቅረብ ይዋጣልኝ ነበር። እናም ከዚህ ስብዕናዬ ጋር ብዙ ጓደኞችን አፍርቻለሁ። ብሩክ እና ሄኖክ የልጅነት ጓደኞቼ ናቸዉ። ከብሩክ እና ሄኖክ ጋር የተዋወቅነዉ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ሆነን ነዉ። አንድ ትምህርት ቤት ከመማራችን በዘለለ ሰፈራችንም አንድ ነበር። ብሩክ በአቋራጭ የሚከብርበትን መንገድ ዘወትር የሚያስብ አይነት ሰዉ ነዉ። የሰዉ ታሪክ ማዳመጥ ይወዳል በተለይ የፍቅር ታሪክ። አንድ ሰዉ የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ ገብቶ ካገኘዉ ልምድ ሊያወራ ከሚችለዉ በላይ ብሩክ የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ ለመግባት ከመፈለጉ የተነሳ ብዙ ይቀባጥራል። እኔ ከብሩክ ጋር የምካፈለዉ የህይወቴ ጎን የፍቅር ህይወቴን ነዉ። ማዳመጥ ስለሚፈልግ እነግረዋለሁ።

ሄኖክ ደግሞ ቀላ ያለ አጭር ቁመት ያለዉ ሚስኪን ልጅ ነዉ። መልካም ልብ አለዉ። ወደ መልካም ነገር የሚጠራዉ ሰዉ ካለ ሁሌም መልካም ለማድረግ ዝግጁ ነዉ። ነገር ግን የኔ የሚለዉ አቋም የለዉም። እኔ ጋር ሲመጣ ከኔ ጋር ያነባል ፣ ከብሩክ ጋር ሲሆን ደግሞ ከሱ ጋር ለመመሳሰል ይሞክራል። ከጊዜያት በኋላ ሄኖክ ሰፈር ቀይሮ ከኛ ሰፈር ትንሽ ራቅ ወዳለ ቦታ ስለሄደ ግንኙነታችን እየቀዘቀዘ መጣ። በአንፃሩ ደግሞ ከብሩክ ጋር በጣም እየተቀራረብን ሄድን። ቀናት ቀናትን እየወለዱ ወራት ከወራት ጋር እየተጋቡ ይኸዉ አስራ ዘጠኝ አመት አልፎኝ ወደ ሀያ ሩጫዉን ተያያዝኩት።

.

ዛሬ ዉስጤ ላይ የመሰበር ስሜት ይሰማኛል። ሁሌም ጠንካራ ነበርኩ ፣ ዛሬ ግን በህይወቴ ዉስጥ በፍፁም ሊከሰት ይችላል ብዬ የማልጠብቀዉ ነገር ተከስቷል። ዉስጤ የመሰበር ስሜት

ይሰማኛል። ለካ የኛ ያልናቸዉ ሰዎች የእምነት ባንዲራችንን

ቀድደዉ በተቃራኒ ወገን በኩል ሲሰለፉ ፣ ያመናቸዉን ልባችንን

ፊት ሲነሱ ፣ ያጎረሷቸዉን እጆቻችንን ሲነክሱ በጣም ያማል።

ህመሙ የልብ ምታችንን ከወትሮዉ በተለየ እንዲመታ

ሲያስገድደዉ ፣ አይናችንን ከእንቅልፍ ጋር ሲያጣላዉ ፣ ስሜቱን

መግለፅ ሲከብደን ፣ በደፈናዉ ስብራት እንለዋለን። አዎን ሁሉም

ቀጥ ብሎ የቆመዉ የህይወት መዘዉራችን ሲናጋ ፣ ምንም

ባይገልፀዉም እንኳ መሰበር እንለዋለን። አዎ ዛሬ እኔም

ተሰብሬያለሁ። የስብራቴ ሁሉ ምንጭ ደግሞ ከክብር ዙፋኔ

ወርጄ አብሬያት የተጫወትኩት ፣ ለማንም ያላረከስኩትን እኔነቴን

ያረከስኩላት የህይወቴ ትልቋ ደስታ፣ ስህተት እና ስብራት

ኢክራም ናት።

ኢክራም ቆንጆዋ!! ኢክራም ሀዘንተኛዋ!! ኢክራም አፍቃሪዋ!!

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/amharicfiction

ሃጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል ሁለት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ዉስጤ ላይ የሚሰማኝን የመሰበር ስሜት ለማስታመም ሰፈራችን

ዉስጥ ወደሚገኘዉ ጭር ያለ ካፌ ሄድኩ። ካፌዉ ሰዉ

ስለማይበዛበት ጥንዶች ይመርጡታል። እኔ ካለሁበት ጠረጴዛ

ፊት ለፊት ጥንዶች ተቀምጠዉ ያወጋሉ። እሱ ይቀልዳል እሷ

ትስቃለች ፣ ፀጉሯ አይኗን ሲሸፍናት እሱ ወዲያዉ በጣቱ ፀጉሯን ወደኋላ ይመልስላታል። አይን ለአይን እየተያዩ ይስቃሉ። ስናፈቅር አለም ሁሉ እጃችን ላይ ያለች ትመስለናለች። የኛ አለም ባፈቀርነዉ ሰዉ ህይወት ዉስጥ ይገደባል። ሀዘናችን ያፈቀርነዉ ሰዉ ሀዘን ይሆናል። ደስታችን ያፈቀርነዉ ሰዉ ደስታ ይሆናል። መለማመዳችን የህይወት መዘዉራችን የአንዳችን በአንዳችን ላይ የተደጋገፈ እንዲሆን ስለሚያደርግ አንዳችን ያለ አንዳችን ጎዶሎ እንደሆንን ይሰማናል። አንዳንዴ ደግሞ ከእዉነት ጋር እንከዳዳለን። ከወደድናት ልጅ የሚበልጡ ቆንጆ ሴቶች ሞልተዉ እኛ ግን አፋችንን ሞልተን ከሷ ሌላ ዉብ ከየት መጥቶ እንላለን። ይህ ከፍቅራችን የሚመነጨዉ ስሜት ላፈቀርነዉ ሰዉ የመልአክነት ዘዉድ ይጭንለታል። ሲሳሳት ስህተቱ አይታየንም። ፍቅር የአእምሮን ምክንያታዊ አስተሳሰብ የሚያደነዝዝ እፅ ሳይሆን አይቀርም።

.

ከፊት ለፊቴ የተቀመጡት ጥንዶች አሁንም ይሳሳቃሉ። 'ምን እየተባባሉ ይሆን?' ብዬ አስባለሁ። ምናልባት እሱ "ካንቺ ዉጪ ሴት ምድር ላይ አለ እንዴ?" ይላታል ለሱ ከሷ ሌላ ማንም እንደማይጥመዉ ለመግለፅ። እሷ ደግሞ ኩራተኛ ናት እንዳትባልም እሱንም እግረመንገዷን ለማሞገስ "ኧረ ያንተም እናት አሉ።" ትለዋለች ከዛ ሁለቱም በአንዴ ካካካካካ ብለዉ ይስቃሉ።

አሊያምእሷ "ፈጣሪ ግን አንተን መጥላት የሚችል አንጀት ፈጥሯል?" ስትለዉ እሱ ደግሞ "የአንቺን ዉበት የሚክድ አንደበት ፈጥሮ እንደሆን ምናልባት እኔንም የሚጠላ አንጀት ፈጥሮ ይሆናል።" እያላትም ሊሆን ይችላል የሚሳሳቁት። በጤነኛ

አእምሮ ካሰብነዉ እኮ ምንም አያስቅም። በፍቅር የሚሉት ጉድ ዉስጥ ስንሰምጥ ግን የማያስቀዉ ያስቀናል። ስናፈቅር እኮ የቃላት አደራደራችን አራሱ እንዴት እንደሚያምር። ስነ ፅሁፍ በዞረበት ዞሮ የማያዉቀዉ ራሱ እልም ያለ የስነ ፅሁፍ ሰዉ ይሆናል። ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ባለሙያዎች የሚለየዉ እሱ ያፈቀራትን ሴት ለማሞገስ ቃላትን ሲያስዉብ ፣ ሌሎቹ ደግሞ የማትታወቅ ዉብ እንስትን ለመፍጠር አእምሯቸዉን ማስጨነቃቸዉ ነዉ።

አሁንም ከፊት ለፊቴ የሚሳሳቁትን ጥንዶች እየተመለከትኩ "ምን እየተባባሉ ይሆን የሚሳሳቁት?" እላለሁ። ምናልባት የሚያስቅ ነገርም ላይሆን ይችላል የሚያወሩት ግን አብረዉ መሆናቸዉ የፈጠረባቸዉ ስሜት በራሱ እንደጀል እያሳቃቸዉ ይሆናል። አዉቀዋለሁ ስሜቱን!!

.

የእነሱን የዛሬ ደስታ እያየሁ የራሴን ስብራት አስባለሁ። ዛሬ የተገኘሁበት ካፌ ዉስጥ የዛሬን አያድርገዉና እኔም እንደነዚሁ ጥንዶች ግጣሜ ትመስለኝ ከነበረች ሴት ጋር እመላለስ ነበር። አዎን ሊያዉም መቼም የምለያት ከማትመስለኝ ቆንጆ ሴት ጋር ነበር ምመላለሰዉ። ስሟ ኢክራም ይባላል። ረዘም ያለች ናት። ፊቷ ቀላ ያለ ነዉ። አይኗቿ ጠበብ ብለዉ በጣም ያምራሉ። ከንፈሯ ቆንጆ እንደሆነ ያወቅኩት ጓደኛዬ ብሩክ ከነገረኝ በኋላ ነበር። ምናልባት እኔ ያላየሁት የከንፈሯ ዉበት ለጓደኛዬ ለብሩክ እንዴት እንደታየዉ ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ። እኔ ለሷ ከነበረኝ ፍቅር ይልቅ እዝነቴ ይገዝፍ እንደነበር ያወቅኩት አሁን ከተለያየን በኋላ ነዉ። የህይወቷን እያንዳንዷን ገመና አዉቅ ስለነበር በጣም አዝንላታለሁ። አብረን መንገድ ላይ ስንራመድ እንኳ

እንቅፋት ነካ ሲያደርጋት ልቤ ተገንጥሎ እስከሚወድቅ ድረስ ነበር የምደነግጠዉ። በጣም ታሳሳኝ ነበር። ሰዉ ግን ለሰዉ ይሄን ያህል ይሳሳል? የኔ የተለየ ነበር። እወዳት ነበር። ዉዴታዬ ሙሉ ለሙሉ የተገነባዉ ደግሞ ለሷ ከነበረኝ እዝነት ነበር።

.

እንደምታፈቅረኝ ሁሌም ትነግረኝ ነበር። እኔ ለሷ ካለኝ ፍቅር ፣ እሷ ለኔ ያላት ፍቅር እንደሚበልጥ ታወራልኛለች። አምን እነዛን ውብ አይኖቿን እያስለመለመች "ፈዊዬ አንተ ታፈቅረኛለህ ግን የኔ ድመት እኔ ላንተ ያለኝ ፍቅር ካንተ በጣኣኣም ይልቃል።" ትለኛለች። የፍቅሯን ደረጃ ሰማይ ይገልፀዉ ይመስል ወደሰማይ አይኖቿን እየሰቀለች። እኔም "አንቺ ከኔ በላይ እንደምታፈቅሪኝ አዉቃለሁ።" እላት ነበር። ይሄ ግን ለሷ ያለኝን ታላቅ የእምነት ደረጃ የሚያሳይ ነበር። ይህ እምነቴ የመነጨዉ ደግሞ ለሷ ካለኝ ጥልቅ ፍቅር ነበር። በሰዓቱ እሷ ይሄን ስሜቴን ተረድታዉ ይሁን አይሁን አላዉቅም። እንደምታፈቅሪኝ አምናለሁ ከማለት በላይ የእምነት ደረጃ ፣ ከእምነት ጥግ በላይ ደግሞ የመዉደድ ልኬት እንደሌለ ይግባት አይግባት አላዉቅም።
በነገራችን ላይ የኔ ድመት የምትለኝ ወተት በጣም ስለምወድ ነዉ። እሷ ደግሞ ቸኮሌት ነብሷ ነዉ።

.

ትዝታዎቼ እጅጉን አዲስ ናቸዉ፤አላረጁም። የኢክሩ ጅልባብ መሬት እየጠረገ ፣ የጅልባቡን እጄታ በእጇ ይዛ ፣ በጥርሷ ጅልባቡን ነክሳ እያየችኝ የሳቀችበት ቀን አሁን እንደተከወነ ድርጊት ጥርት ብሎ ትዝ ይለኛል።
ኢክሩ ግጥም አትወድም ፣ እንደዉም የሆነ ጥፋት ካጠፋች መቀጮዉ ግጥም እኔ ሳንብ ማዳመጥ ነበር። ኢክሩን አጥፍታ

አንበርክኬያት አዉቃለሁ። ኢክሩን ተንበርክካ ማየት በራሱ ሀሴት ይሰጣል። ከኢክሩ ሌላዉ የሚጣፍጠኝ ነገር 'ደ' የሚለዉን ፊደል በስርዓት ማለት አትችልም። 'ደ' ስትል ስሰማት ጉረሳት ጉረሳት ነበር የሚለኝ። ግን ማን ይሄ ሁሉ ነገር ነበር ይሆናል ብሎ አሰበ? ማንም!!

.

ዛሬም ከዚህ ሁሉ ስብራቴ ጋር ለኔ የነበራትን እንክብካቤ እና አክብሮት አልከድም። ሰዉ የራሱ መልካም ጎን እንዳለዉ ሁሉ ደካማ ጎንም ይኖረዋል። ገና ለገና ዛሬ ተለያየን ተብሎ የሰዉን ስም አተላ መቀባት አግባብ ነዉ ብዬ አላምንም። ኢክሩ አብረን እያለን ለኔ መልካም ነበረች።

.

አስተናጋጇ ፊቴ መጥታ ቆመች ፈገግ ብላ "ፈዉዛን ሳፊዉ!!" አለችኝ። ስሟ ረሂማ ነዉ። ከኢክራም ጋር እዚህ ቤት ስንመላለስ ሁሌም የምታስተናግደን እሷ ነበረች። "ፈዉዛን ሳፊዉ!!" ያለችኝ ወተት በሳፊ ስለምጠጣ መሆኑ አንዱ ምክንያቱ ነዉ። ሰሞኑን ግን ይሄን ቃል የምትጠቀመዉ ብቻዬን ስለምመጣ ነዉ። ያዉ ወተት ሳፊ ሲሆን ያለቡና ብቻዉን አይደል የሚቀርበዉ።

ጨዋታዋ ደስ ስለሚለኝ ምንም ጥሩ ስሜት ላይ ባልሆንም ፈገግ ብዬ "ወዬ ረሂማ ኮካ" አልኳት። ሳቋ ወዲያዉ ወዲያዉ ቡፍ ስለሚል ነዉ ኮካ የምላት።

"ከወተት ሌላ ምትፈልገዉ ነገር አለ?" አለችኝ። ምን እንደምጠጣ በደንብ ታዉቃለች።

"ወተት ብቻ አምጭልኝ ኮካዬ" አልኳት እየሳቅኩ። ምላሷን አዉጥታብኝ ወተቱን ልታመጣ ሄደች። በነገራችን ላይ ከአስተናጋጆች ጋር እንደዚህ ያለ ወዳጃዊ ግንኙነት መመስረት

ደስ ይለኛል። ካፌ ብቻ ሳይሆን የትም ስሄድ ፊቴን ከመከስከስ

ይልቅ ፈታ ብዬ እየተጫወትኩ ከሰዎቹ ጋር መግባባት

ያስደስተኛል። ተጫዋችማ ነበርኩ ኢክሩ ያደረገችኝ ነገር የሆነ

አዚማም አደረገኝ እንጂ!!

.

ከኢክሩ ጋር የተዋወቅንበት መንገድ ትንሽ ለየት ይላል። ፈጣሪ

እራሱ ተዋወቁ ብሎ ሜዳዉንም ፈረሱንም እንካችሁ እንደማለት

ነበር ያመቻቸልን።

ከኢክሩ ጋር እንዴት እንደተዋወቅን በደንብ አስታዉሳለሁ!! አዎ

በደንብ!!

ቀኑ ጁምዓ(አርብ) ቀን ነበር!!

ከኢክራም ጋር የተገናኘነዉ የዛሬ ሁለት ዓመት እኔ የዩኒቨርሲቲ

መግቢያ ፈተናዬን ለመዉሰድ ስዘጋጅ ፣ እሷ ደግሞ የመሰናዶ

ትምህርት ቤት መግቢያ ፈተና ለመዉሰድ ስትዘጋጅ ነበር።

ይህቺን ዉብ ፈጣሪ ሲያንቀለቅል ታክሲ ዉስጥ ይዞልኝ መጣ።

ታክሲዉ ዉስጥ ብቻም አይደለም!! ከታክ

ሲዉም እኔ

የተቀመጥኩበት የመጨረሻዉ ወንበር ላይ በመካከላችን አንድ

ሰዉ ብቻ እስከሚኖር ድረስ አቀራርቦ አስቀመጠልኝ።

በመካከላችን አንድ ሰዉ መኖሩ ፈጣሪ "አንተም የድርሻህን ያህል

ጣር እንጂ" ሊለኝ ያደረገዉ ነበር የመሰለኝ። እኔም እሷም

ከትምህርት ቤት እየተመለስን ነበር። እሷ የምትማርበት

ትምህርት ቤት እኔ ከአራተኛ ክፍል እስከ አስረኛ ክፍል

የተማርኩበት ትምህርት ቤት ነዉ።

ታክሲ ዉስጥ ያሉት ልጆች የለበሱትን ዩኒፎርም ስመለከት

በትምህርት ቤቱ ያሳለፍኩት ትዝታ ወለል ብሎ ይታየኝ ጀመር።

ታክሲዉ ዉስጥ የሷን አይነት ዩኒፎርም የለበሱ ተማሪዎች ነበሩ።

ከነሱ ጋር የመምህራንን ስም እና ባህሪ እየነገርኳቸዉ ስንሳሳቅ

እሷም እየሰረቀች ስታየኝ ተመለከትኩ። ጥሎብኝ ሴት ቀድማ

ሳታናግረኝ አላዋራም። ለራሴ ዋጋ ስለምሰጥ ነዉ መሰለኝ

ለማንም መርከስ አልፈልግም። የዛን ቀን ግን እየተሸኮረመመች

ስትመለከተኝ ሳይ ወዲያዉ ፊቴን ወደሷ አዙሬ እርግጠኛነት

በተሞላበት ስሜት "አንቺ የሆነ ቦታ ታዉቂኛለሽ።" አልኳት።

እሷም አሁንም ከሳቋ ጋር እየታገለች በአዎንታ ጭንቅላቷን

ነቀነቀችልኝ። በሁለታችን መካከል የነበረችዉ ልጅ "በሉ

ልውጣላችሁ" ብላ ከታክሲዉ ወረደች። የመዉረጃ ቦታዋ ደርሶ

ይሁን የወረደችዉ አሊያም የኛን የማዉራት ፍላጎት ተረድታ

አላወቅኩም። ብቻ ለትዉዉቃችን አስተዋፅዖ አበርክታለች። ግን

ምናለ ልጅቷ ከመካከላችን ባልወጣች እና እኔና ኢክሩ

ሳንተዋወቅ በቀረን። ከነዉበቷም ከነፈገግታዋም ስብራቴ መሆኗ

ላይቀር ምናለ ባላወቅኳት።

ልጅቷ ከመካከላችን እንደወጣች ኢክራምን የት እንደምታዉቀኝ

ጠየቅኳት። መስጂድ የሚዘጋጁ ገዘጮቶች ላይ መድረክ ስመራ

እንደምታዉቀኝ ነገረችኝ።

.

በትርፍ ሰዓቴ መስጂድ ዉስጥ የስነ ፅሁፍ ስራዎችን እሰራለሁ።

በእስልምና ሀይማኖት መሰረት የወንዶች መስገጃ ቦታ እና

የሴቶች መስገጃ ቦታ የተለያየ ቦታ ላይ ነዉ የሚሆነዉ። እኔ

ኢክራምን ከዛ ቀን በፊት አላዉቃትም ነበር። መስጂድ ነዉ

የማዉቅህ ስትለኝ ወዲያዉ አደብ ያዝኩ!! የተከበረ ቦታ ላይ

ታዉቄማ እዚህ አልረከስም አልኩ በልቤ። ግን ወዲያዉ

የጓደኛዬ የአዩብ ፍቅረኛ ሪም ትዝ አለችኝ እና ታዉቃት ከሆነ ብዬ

ጠየቅኳት። በጣም የቅርብ ጓደኛዋ እንደሆነች ነገረችኝ።

ለማንኛዉም ከሷ ጋር የሚተዋወቁ ከሆነ የእኔ እና የእሷ ነገር

እንዳለቀለት አሰብኩ። አዩብ እና ሪም ሲኮራረፉ ሁሌም እኔ

ነበርኩ የማስታርቃቸዉ። ሪም ቀርባ ሳታዉቀኝ በጣም ትጠላኝ

ነበር። ስንቀራረብ ግን በጣም ወደደችኝ። አዩቤ ደግሞ ቁጡ

ስለሆነ ሲጣሉ ለማረጋጋት ግዴታ እኔ መግባት አለብኝ።

ስለፍቅር ህይወት እኮ ምንም አላዉቅም ግን እንደ ቀበሌ ሹም

በባዶ ጉብቼ እለምድባቸዉ ነበር።

ኢክራም ስሜን እንደምታዉቀዉ ብገምትም ለወጉ ያክል ፈገግ

ብዬ "እንተዋወቅ ፈዉዛን እባላለሁ" አልኳት። አይኖቿን በሀፍረት

ሰበር እያደረገች "ኢክራም እባላለሁ" አለችኝ። የመዉረጃ ቦታዋ

ከኔ ትንሽ ይቀድም ስለነበር ቀድማኝ ወረደች። የዛን ቀን

ከለበሰችዉ ዩኒፎርም ላይ ጥቁር ሰማያዊ ጅልባብ ለብሳ ነበር።

ጅልባብ ማለት በአብዛኛዉ ሙስሊም ሴቶች የሚያዘወትሩት

እጅንና ፊትን ብቻ የሚያሳይ ሰፊ ልብስ ነዉ።

ከወረደች በኋላ ስልኳን እንዳልተቀበልኳት አስታወስኩ። ኩራቴ

ተናንቆኝ ነዉ? ለምን ስልኳን አልተቀበልኳትም? አዎን ገባኝ

የሪም ጓደኛ ነኝ ስላለችኝ ነዉ ስልኳን ያልተቀበልኳት። የሪም

ጓደኛ ከሆነች እኔና ሪም በጣም ስለምንግባባ ስልኳን በቀላሉ

ማግኘት እንደምችል ስላሰብኩ ነዉ ዝም ያልኳት።

.

የዛን ቀን ታክሲ ዉስጥ ኢክራምን ሳወራት የነበራት አይነአፋርነት

አሁን ላሉት አይንአዉጣ ሴቶች እና ለአሁን እሷነቷም ጭምር

ቢታደል ይበቃ ነበር። የሆነ ከአይናፋርነትም ቀልብ የሚገዛ

አይናፋርነት አለ እኮ የእዉነት!! የተመጠነ በዉስጡ ትህትናን እና

አክብሮትን ያዘለ አይናፋርነት!!

ከተለያየን በኋላ ቤት ገብቼ አረፍ አልኩ። ግን አሁንም የማስበዉ ዛሬ ታክሲ ዉስጥ ስለተዋወቅኳት ቆንጆ ልጅ ነበር። አይናፋርነቷ ፣ ፈገግታዋ ሁሉ ትዝ እያለኝ ብቻዬን ፈገግ አልኩ። ወዲያዉ ራሴን አረጋጋሁት ምንድነዉ ስለማላዉቃት ሴት ማሰብ? በሰዓቱ እኔ የአስራሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። ሀይማኖታዊ መድረኮችን መርቼ ከወረድኩ በኋላ በራሱ የሴቶቹ የፌስቡክ እና የስልክ መልዕክቶች ፈተና ነበር የሚሆኑብኝ። አንዳንዴ ፍላጎታችን ተመሳሳይ ሆኖ ግን የፍላጎታችንን ለማግኘት የተለያየ ቦታ እንሄዳለን። አንዳንድ ሴቶች ሀይማኖታዊ መድረኮች ላይ የሚታዩ ወንዶችን ለመጥበስ በየገፃቸቶቹ ላይ ይገኛሉ። አሁን ላይ እኮ ሁላችንም የመጥበስ መልዕክተኞች ሆነናል። በየትምህርት ቤቱ በየሄድንበት ሁሉ!! ሀይማኖት ቦታ ላይ ያለዉ አጠገቡ ያለችዉን ይጠብሳል ወይ ትጠብሰዋለች። ይሄ ደግሞ ሁሉም ሀይማኖት ላይ ያስተዋልኩት ሀቅ ነዉ። እኔም ብዙ ጊዜ እንደዚህ ያሉ ነገሮች ገጥመዉኛል ግን ፊት አልሰጠኋቸዉም። በየጊዜዉ የማላዉቃቸዉ ሴቶች ልብ የሚያቀልጡ መልዕክቶችን ፌስቡክ ላይ ይልኩልኛል። እኔ ግን ብዙም ግድ አይሰጠኝም ነበር። ታዲያ ቆይ ዛሬ ምን ተገኝቶ ነዉ ስለማላዉቃት ሴት የማስበዉ? ገርሞኛል። ቀልቤን ስርዓት ማስያዝ አለብኝ።

.

ሁሌም ከትምህርት ስመለስ እንደማደርገዉ አልጋ ላይ ተዘርፌ ፌስቡክ ላይ የምከታተላቸዉን ተከታታይ ፅሁፎች ማንበብ ጀመርኩ። ሲመሻሽ የማላዉቀዉ ስልክ ተደወለልኝ። አነሳሁት ፣ ሳነሳዉ ሪም እየተፍለቀለቀች "ፈዊ ግን ኢክሩን ምን አስነከተህት ነዉ? ቅድም ካገኘኋት ጀምሮ ስላንተ ነዉ የምታወራልኝ።"

አለችኝ። ከሪም ድምፅ ጀርባ ኢክራም እንድትዘጋዉ ስትማፀናት

ይሰማኛል። ልክ ነበርኩ የሪም ጓደኛ ከሆነች የኔና የሷ ነገር

አልቆለታል አላልኳችሁም ነበር? እየሳቅኩኝ "እስኪ እድል ስጫት

ታናግረኝ" አልኳት። "ኧረ ፊዋ ልትገለኝ ምንም አልቀራትም፣

አሁን በመካከላችን መኪና ገብቶ ነዉ የማወራህ" አለችኝ።

የሪም ስራ እያሳቀኝ "ይሄ የሷ ስልክ ነዉ?" አልኳት። "አዎ ፊዋዬ

ቆጥበህ ተጠቀመዉ።" ብላኝ እየተፍለቀለች ስልኩን ዘጋችዉ።

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

(ፉአድ ሙና)

ክፍል 3

.

.

mame:

የኢክራምን ስልክ የሪም እድሜ ይርዘምና ምንም ሳልለፋ

አገኘሁት። በነጋታዉ ኢክራምን ለመጀመሪያ ጊዜ በስልክ ላወራት

ደወልኩ። ስታወራ ደስ ትላለች። አዳማጭ ብቻ ሆና

አታስጨንቅም። አስራስድስት ደቂቃ አወራን ፣ ከማላዉቃት ሴት

ጋር ያዉም ለመጀመሪያ ጊዜ እያወራን ይህን ሁላ ደቂቃ ማናገሬ

ገርሞኛል። በሁለተኛዉ ቀን ደዉዬ ስናወራ "ኢክሩ ግን

ትኮሪያለሽ አይደል?" አልኳት።

"ምነዉ? ምናጠፋሁ?" አለችኝ ግራ እየተጋባች። "አንቺ መች

ታስታዉሺኛለሽ፣ ኧረ አንቺም ፈልጊኝ!!" አልኳት። ሁሉም ነገር

እኮ በአንድ ወገን በኩል ብቻ ሲሆን ያስጠላል። ሰጥቶ

እንደመቀበል የሚያስደስት ነገር የለም። አንዳንዶች ሁሌ

እንድትሰጣቸዉ ብቻ ይፈልጋሉ። እነሱ ግን በምላሹ ምንም

አይሰጣችሁም። ይሄ የወዳጅነት ትስስርን ይነቀንቃል። እኔም እኔ

ብቻ ስደዉል እኔ ብቻ ፈላጊ እንደሆንኩ ስለተሰማኝ ነዉ እንዲህ

ያልኳት።

ኢክሩ እየተቅለሰለሰች "ኧረ አልኮራም፣ እደዉላለሁ ችግር

የለዉም ፈዉዛኔ!!" አለችኝ።

ከዚህ ቀን ጀምሮ በተራ መደዋወል ጀመርን። እኔ ዛሬ ከደወልኩ

እሷ ነገ ትደዉላለች። በስልክ በምናወራበት ሰአት ስለሷ አንዳንድ

ነገሮችን አወቅኩ። አባቷ በህይወት የለም። ወንድምም ሆነ

እህት የላትም። ከእናቷ ጋር ብቻቸዉን ነዉ የሚኖሩት። ብቸኛ

ወዳጇ ፊልም ነዉ። ሲደብራት ተከታታይ ፊልሞችን ዲሽ ላይ

ትከታተላለች። ፊልም ነዉ ያሳደጋት። ፊልም እያየች አድጋ ነዉ

እኔም ላይ ቆንጆ ፊልም የሰራችብኝ!! ያየችዉን ነዉ

የተገበረችብኝ!!

.

ኢክራም ታሪኳን ስትነግረኝ ምናልባት በህይወቷ ዉስጥ

ያጣችዉን ወንድሟን ሆኜ ብቸኝነቷን ላስረሳት አሰብኩ። የጅንጀና

ሙዷ ሁሉ ተጦለበ። በቃ ንፁህ ወንድሟ ለመሆን አለምኩ።

አንድ ቀን ማታ ላይ ኡስማን ከሚባል ጓደኛዬ ጋር ወደ ሰፈር

እየገባን ስሟን ሳልነግረዉ ታሪኳን አጫወትኩትና ከኔ ይልቅ እሱ

ሴት መንከባከብ ስለሚችል እንደዉም ባስተዋዉቃቸዉና እሱ

ቢንከባከባት ደስ እንደሚለኝ ነገርኩት። ኡስማን ደግሞ በጣም

የምወደዉ መስጂድ የተዋወቅኩት ጓደኛዬ ነዉ።

ታሪኳን ከነገርኩት በኋላ እሱም ልቡ ተነክቶ "ፈዉዛኔ እቺን

ምርጥ ሁበታም ፊልን አሁኑ መዳር ነዉ!!" አለኝ። በሰፊዉ

እንደምናወራበት ተነጋግረን ከኡስማን ጋር ተለያየን። ከዛ በኋላ

ግን ከኡስማን ጋር ስለዓ አወርቼ አላዉቅም። ኡስማን ወንድ ነዉ

ግን እዉነት ለመናገር ለሴት ከንፈሯ ሲያምር ምናምን

እንደምንለዉ ፀጉሩ፣ መልኩ በአጠቃላይ የሚያምር ልጅ ነዉ።

በጣም ደግሞ ተግባቢ ነዉ። በጣም ብዙ ሴቶች የሚመኙት

ወንድ ነዉ። ኢክሩን እንዲንከባከባት ያሰብኩት ከዚህ በፊት

ካለዉ ልምድ ተነስቼ ነበር። ዉስጤ ላይ ያደረዉ የወንድምነት

መንፈስ ከኔ ሴት በመንከባከብ ለተሻለ ወንድ አሳልፎ

እስከመስጠት ወስዶኝ ነበር። የፈጣሪ ጥበብ ግን ይገርማል

ትናንተ ስለማላዉቃት አንድ ሴት ዛሬ ከማንም በላይ የምጨነቅ

ፍጡር እንድሆን አደረገኝ።

.

ከኢክራም ጋር ግንኙነታችን ከስልክ በአካል ወደመገናኘት

ሊያድግ ቀን ቆረጥን። አርብ ዕለት ማታ አንድ ሰአት ላይ

ሰፈራችን በሚገኘዉ አስፓልት ላይ ዎክ ለማድረግ ተቀጣጠርን።

ከሴት ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመገናኘት ስትቀጣጠሩ የሆነ

የሚጨንቅ ነገር አለዉ። ልጅቷ ተጫዋች ናት ወይስ አንገቷን

ከማነቃነቅ ዉጪ ምንም የማታወራ ልጉም የሚለዉ ያስጨንቃል።

እኔ ግን አንድ ቀን ታክሲ ዉስጥ ስላገኘኋት ነዉ መሰለኝ ብዙም

አልተጨነቅኩም። ይልቁንስ ስለወደቷ ነዉ የማስበዉ ፣

ስትሽኮረመም በአይነህሊናዬ ይታየኛል። ከዛም በስልክ ያወራነዉ

ታሪኳ ትዝ ይለኝና ስሜቴን አፍነዋለሁ። ከሴት ጋር ተቀጣጥሮ

የመንዘላዘል ልምድ የለኝም። አሁን ግን መንዘላዘልም በሉት

ምን ከኢክራም ጋር ለመገናኘት ተቀጣጥሪያለሁ።

.

ጁምዓ ደረሰ!! ማታ ላይ ኢክራም ከሪም ጋር ሆና

የተቀጣጠርንበት ቦታ ላይ ተገናኘን። እኔ ግን ግራ የሚገባኝ

ሴቶች ለምንድነዉ የመጀመሪያ ቀን ስትቀጥሯቸዉ ከጓደኞቸዉ

ጋር የሚመጡት? እኔ ግን ስገምት ደህንነት የሚሰማቸዉ

አይመስለኝም። ምናልባት ወንዱ አደብ ከሌለዉ ስርዓት

ለማስያዝ አሊያም አብሮ ለመጮህም ሊሆን ይችላል ሁለት

ሆነዉ የሚመጡት። ኢክራም ቤት ስትመለስ ሪም ጋር ነበርኩ

ለማለት አቅዳ ነዉ በድፍረት በማታ ያገኘችኝ። ከዛ ቀን በኋላ

እስክንለያይ ድረስ በዛ ሰዓት አግኝቼያት አላዉቅም። እስከምሸቱ

ሁለት ሰዓት ያመሸነዉ የዛኔ ብቻ ነዉ።

ኢክራምን ገና ከሩቅ ሳያት ልቤ "የምን ወንድምነት ነዉ? እያት

እስኪ ያስችልሀል?" እያለ ሞገተኝ። ልቤን አደብ አስገዝቼ እነ

ኢክራምን ተቀላቀልኳቸዉ። ሁለቱም የለበሱት ሺቲ ነዉ። ኢክራም

ከላይ ጀኬት ደርባለች። በጅልባብ ስላልመጣች ጌታዬን

አመሰገንኩ። ሺቲ እና ድሪያ ልዩነቱ ምን እንደሆነ አላዉቅም።

የልብሱ ስም ሺቲ እንደሚባል ኋላ ላይ ነዉ ኢክሩ ራሷ

የነገረችኝ። ንፋሱ የለበሰችዉን ሺቲ ገላዋ ላይ ሲለጥፈዉ

የሰዉነቷ ቅርፅ ወለል ብሎ ታየኝ። መጠነኛ መቀመጫ አላት ፣

ወገቧ ከመቀመጫዋ እጅጉን ቀጥኖ ስምንት ቁጥር ሰርቷል።

ንፋስን ቅርጿን እንዳይ ስፖንሰር ስላደረገኝ ከልብ አመሰገንኩ።

ወዲያዉ ሪም ተሰናብታን ሄደች።

እኔና ኢክሩ ብቻ ፣ ማታ ላይ ፣የመንገድ መብራት ባስጌጠዉ ዉብ

ጎዳና ላይ አብረን ቀረን። ግን አልተፈራራንም አንዳንችን

በአንዳችን መኖር ምቾት ተሰምቶናል። ምናልባት በህይወቴ

እስከዛሬ ካደረግኳቸዉ ዎኮች ዉስጥ የህይወቴን ልዩ ታሪክ

የመሰረተዉ ዎክ ይሄ ይመስለኛል።

"ኢክራም" አልኳት መንገድ መንገዱን እያየሁ።

"አቤት ፈጢዛን" አለችኝ አንገቷን ወደኔ አዙራ።

"ባለፈዉ ታክሲ ዉስጥ ስንገናኝ ጅልባብ ነበር የለበስሽዉ ዛሬ

እንዴት አወለቅሽዉ?" አልኳት።

ፈገግ አለች እና እጆቿን እያፋጨች "ጅልባብ ሀይማኖታዊ ልብስ

ነዉ!! እስልምና ደግሞ በጋብቻ ካልተሳሰርኩት ወንድ አሊያም

ዘመዴ ካልሆነ ሰዉ ጋር እንዲህ እንድሆን አይፈቅድም። በአጭሩ

የሀይማኖት ልብስ ለብሼ እምነቴ የከለከለኝን ነገር ላለማድረግ

ብዬ ነዉ!! ሀይማኖታችንን ላለማሰደብ!!" አለችኝ።

በመልሷ በጣም ደስ ተሰኘሁኝ። እኔም ለጅልባቧ እና ለሀይማኖቷ

ባላት ክብር አደነቅኳት።

ፈገግ ብዬ "ሁሌም እኔን ስታገኚኝ ጅልባብ ባትለብሺ ደስ

ይለኛል።" አልኳት።

"ይሸዉ ልክ እንደዚህ በሺቲ እመጣለሁ።" አለችኝ አንገቷን

በሀፍረት እየሰበረች

በልቤ በጣም ሳቅኩ ፣ ደስ አለኝ!! በሺቲ እመጣለሁ ስላለችኝ

አይደለም። ግን በንግግሯ ዉስጥ ከዚህ በኋላም እንገናኛለን

የሚል መልዕክት ነበር።

"ኢክሩ ባለፈዉ ግን ለምንድን ነበር ታክሲ ዉስጥ እያየሽኝ

የሳቅሽዉ?" አልኳት ትልቅ ነገር እንዳስታወሰ ሰዉ ወደሷ እየዞርኩ

"እንዴ ፈጢዛኔ ታክሲዉ ዉስጥ ስትቃለድ የነበረዉ እኮ ከሴቶች

ጋር ነበር። እኔ ደግሞ በጣም ኮስታራ ስለምትመስለኝ ሴት

የምታናግር ራሱ አይመስለኝም ነበር።" አለችኝ ልክ እንደባለፈዉ

እየሳቀች

ብዙዎች የሚታሰቡት እነሱ እንደሆኑት አይደለም። ተመልካቹ

እንደሚሰላቸዉ ነዉ። እንደኔ እኮ ተጫዋች የለም ግን ኮስታራ

መሰልኳት። ይገርማል!!

.

ሁለት ሰአት ሊሆን ሲል ከኢክሩ ጋር ተለያየን። ቤቷን ስለማላዉቀዉ እስከቤቷ አልሸኘኋትም። የሰፈራችን መስጂድ ጋር ስንደርስ አዛን እያለ ነበር። አዛን ማለት ሁሌም ከመስጂድ የሚሰማዉ "አላሁአክበር" የሚለዉ የስግደት ሰዓት መድረሱን መጠቆሚያ ድምፅ ነዉ። እሷ በቅያሱ ታጥፋ ሄደች እኔ መስጂድ ገባሁ። መስጂዱ አካባቢ ያሉ ሰዎች እንዳያዩን ሁለታችንም እየተጠነቀቅን ነበር። በተለይ እኔ በጣም ብዙ ሰዉ ስለሚያዉቀኝ ከሴት ጋር በማታ መታየቴ ጥሩ አርአያ አይደለም።

ስግ

ደቱ ካለቀ በኋላ ማታ ላይ ወደቤት ገብቼ ኢክሩን ማሰብ ጀመርኩ። የሆነች ትልቅ ባህር ዉስጥ የተጣለች ትንሽዬ አሳ መሰለችኝ። ሰዉ በሞላበት ሀገር ዉስጥ ሰዉ የምትራብ ሚስኪን ፍጡር!! የእዉነት በጣም አሳዘነችኝ። የብቸኝነት ብርዷን ገፍፌ በሷነቷ ዉስጥ ትንሽ ሙቀት ለመፍጠር ለራሴ ቃል ገባሁ። ሰዉ ነኝ ስሜቴን ልቆጣጠረዉ እንጂ እሱ እንዲቆጣጠረኝ ልፈቅድለት አይገባም። ምንም ወንድነቴ ቆንጆ ከንፈሮቿን እንደቀሰመለት ቢማፀነኝም ከሷ ጋር ክፍተቷን ለመሙላት በወንድምነት መቆየቱ የተሻለ እንደሆነ አሳመንኩት። ግን ቀላል አልነበረም ከራስ ጋር መደራደር ይከብዳል። እዉነት ሰዉ መሆኔን ለማረጋገጥ ግን በየቀኑ የሚያማልሉ መልዕክቶችን የሚልኩልኝን ሴቶች ገፍቼ ለቀረብኳት ኢክራም ወንድም ለመሆን ወሰንኩ። የወንድነቴን ልመና እምቢ አልኩት። እምቢ የማለት አቅም አለኝ ብያችሁም አልነበር? ይኸዉ ወንድነቴን እምቢ አልኩት።

.

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/amharicfiction

ጥቁረቶች

ክፍል አምስት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ለመጀመሪያ ጊዜ ዎክ ካደረግን በኋላ ማክሰኞ የኔ እና የኢክራም

ዉድ ቀን ሆነች። ማክሰኞ ኢክራም ከሀይማኖታዊ ትምህርት ነፃ

የምትሆንበት ቀን ነዉ። ሌሎቹን ቀናት ጁምዓን ሳይጨምር

መስጂድ ሀይማኖታዊ ትምህርቶችን ትማራለች። ሁሌም ማክሰኞ

አስር ሰዓት ላይ ተገናኝተን እስከ አስራሁለት ሰአት ድረስ አብረን

እናሳልፋለን። አስራሁለት ሰዓት ሲሞላ እናቷ ከስራ ስለምትመጣ

ወደ ቤቷ እሸኛታለሁ። እናቷ ከስራ አርፍዳ የምትመጣ ቀን ኢክራ

እስከ አንድ ሰአት ድረስ ከኔ ጋር አርፍዳ ወደ ቤቷ ትገባለች። ከኔ

ከተለየች በኋላ ወደ ቤቷ ስትገባ እናቷ እስከምትመጣ ድረስ

ብቻዋን ቤት ዉስጥ እንደምትቀመጥ ሳስበዉ ለሷ እኔ

እታመማለሁ። ከብቸኝነት በላይ ህመም የለም። የሚያዳምጠን

ሰዉ ከማጣት በላይ ስቃይ አይኖርም።

.

አንድ ቀን ከኢክራ ጋር ሁሌም ወደምንቀመጥበት ከሰፈራችን

ትንሽ ዝቅ ብሎ ወዳለዉ ሰፊ የሳር ሜዳ ሄድን። ሜዳዉ ላይ ኳስ

የሚጫወቱ ልጆች አሉ። ከሜዳዉ ራቅ ብሎ ደግሞ ልክ እንደኛ

የአካባቢዉን ከሰዉ አይን የራቀ መሆን ፈልገዉ የመጡ ጥንዶች ተቀምጠዋል። ሁሌም እንደምናደርገዉ ከክቡ የድንጋይ ቋጥኝ አጠገብ ያሉ መቀመጫዎች ላይ ተቀመጥን። ኢክሩ ድብር ብሏታል።

ቀስ ብዬ "ኢክሩዬ ስለምን እያሰብሽ ነዉ?" አልኳት። እንባ እየተናነቃት "ፈዊ እናቴ ላይ ሸክም እንደሆንኩባት እየተሰማኝ ነዉ።" አለችኝ።

እየሳቅኩ "ኢክሩዬ እናት ላይ እንዴት ሸክም ይኮናል? እናቶቻችን እኮ ሁሌም እኛን ለመንከባከብ አይታክቱም።" አልኳት። አንገቷን በአሉታ እየነቀነቀች እንዳልተረዳኋት ገልፃልኝ ማብራራቷን ቀጠለች።

"ፈዊ እናቴ በጣም ወጣት ናት። አንድ ላይ ብታየን እህትማማቾች እንጂ እናት እና ልጅ አንመስልህም። እሷ የማታገባዉ ባል ጠፍቶ አይደለም ግን እኔን ከእንጀራ አባት ጋር ማኖር ከብዷት ነዉ። እራስ ወዳድ እንደሆንኩ ይሰማኛል ፣ በእናቴ መቅለጥ ነዉ እየፈካሁ ያለሁት።" ንግግሯ በእንባ መታጀብ ጀምሯል። ወይኔ ሰዉ ሲያለቅስም እንዲህ ያምራል? ወንድነቴን አደብ አስገዝቼ በለቅሶ የታጀበ ንግግሯን ማዳመጤን ቀጠልኩ።

"ፈዊ እኔ ባገባ እኮ ማማ ያለስጋት አግብታ መኖር ትችል ነበር። ግን እኔ አሁንም እንደ ልጅ እየተጨማለቅኩ የሷን ህይወት እየቀማኋት ነዉ።" ብላ እንባዋን መጥረግ ጀመረች። አሁን የኢክራምን ዉበት ያየ በዚህ ሁሉ ችግር ዉስጥ እየተፈተነች ያለች ይመስለዋል? በፍፁም አይመስለዉም። ኢክሩ ከተረጋጋች በኋላ ጭንቀቷን እንድትረሳዉ ብዬ ስላሳለፍነዉ የፍቅር ታሪክ እንድንጨዋወት ጠየቅኳት። እሷ ከዚህ በፊት ብዙ ያፈቅሯት

የነበሩ ልጆች የነበሩ ቢሆንም የሚነገር የፍቅር ታሪክ እንደሌላት

ነገረችኝ። እኔ በልጅነቴ ስላፈቀርኳት መርየም ስለምትባል ልጅ

አጫወትኳት። ታሪኩን ከነገርኳት በኋላ

"ኢክሩዬ ለመርየም ካደረግኳቸዉ ነገሮች ዉስጥ የቱ

እንደሚገርመኝ ታዉቂያለሽ?" አልኳት። እንድቀጥልላት ምልክት

ሰጠችኝ "ሰባተኛ ክፍል እያለሁ ነዉ። አንድ ቀን ናቲ የሚባል

ጓደኛችን አስተማሪ ገርፎት ክፍል ዉስጥ እየተንሰቀሰቀ

ያለቅሳል። መርየም እና ጓደኛዋ ናቲን ሲያባብሉት አየሁ።

መርየም አይዞህ እያለች ስትንከባከበዉ ሳይ ናቲን መሆን

ተመኘሁ። በቀጣዩ ክፍለጊዜ ሰበብ ፈልጌ ከአስተማሪ ጋር

ተጣላሁ። ግን አስተማሪዋ አልገረፈችኝም። ተቆጥታኝ አለፈችኝ።

እኔ ግን አላማዬ የመርየምን ማዕናኛ ማግኘት ስለነበር

ተንሰቅስቄ አለቀስኩ።" ኢክራም ሳቅ እያፈናት "እና መርየም

አባበለችህ?" አለችኝ። "ባክህ ዝም በል" አለችኝ ስላት ኢክሩ

እንባዋ ከአይኗ እስኪፈስ ድረስ እየተንከተከተች ሳቀች። ኢክሩ

ስትስቅ በጣም ታምራለች። በዛ ላይ ደግሞ ሳቋን ሊያጅቡ

እንባዎቿ ከዉብ አይኖቿ ሲፈሱ በጣም ለየት ያለ ዉበት አላት።

ኢክሩን እንደዛ ቀን ስትስቅ አይቻት አላዉቅም። ሌላም እንደዚህ

የሚያስቅ ታሪክ በኖረኝ እና ነግሬያት እንዲህ ስትፍለቀለቅ

ባየኋት ብዬ ተመኘሁ።

.

ከኢክራም ጋር ወንድሟ ሆኜ ህዘኗን እየተካፈልኳት እና ጭንቀቴን

እያማከርኳት ለሁለት ወር ቆየን። አንድ ቀን እንደለመድነዉ

ተገናኝተን ተጨዋዉተን ከተለያየን በኋላ ኢክሩ ፌስቡክ ላይ

የሚያስደነግጥ መልዕክት ላከችልኝ።

"ፈዊ የእኔ እና አንተ ሁሌ መገናኘት ጥቅሙ አልታይሽ ብሎኛል።

ቢቀርብን የሚሻል ይመስለኛል።" ይላል መልዕክቷ!! ግራ ገባኝ

ኢክሩ ከኔ ጋር ስትሆን ሁሌም ደስተኛ ነበረች። ዛሬ ምን ተገኘና

በቃኸኝ አለችኝ? ዉስጤ ተረበሸ። እኔ ሳዉቅ ለሷ ጥሩ ወንድም

ነበርኩ። ቢሆንም አልተበሳጨሁባትም በአካል አግኝቼ ላዋራት

ወሰንኩ። ደወልኩላት እንደተለመደዉ እየተፍለቀለቀች

አናገረችኝ። ላናግራት እንደምፈልግ ነግሬያት በነጋታዉ ሰፈራችን

ዉስጥ ያለዉ ቤተ መፅሀፍ ለመገናኘት ተቀጣጠርን።

.

በነገራችን ላይ የኛ ሰፈሩ ቤተ መፅሀፍ ማንበቢያ ከሚባል ይልቅ

የወንድና ሴቶች መቀጣጠሪያ ቢባል የሚገልፀዉ ይመስለኛል።

ለማንበብ ከሚመጣዉ ሰዉ በቁጥር የማያንሱ ቤተ መፅሀፍ

ተቀጣጥረዉ የሚገናኙ ጥንዶች አሉ። የሰዉ ልጅ ለአንድ አላማ

የተለያዩ ቦታዎች ይሄዳል አላልኳችሁም ነበር? ይኸዉ ቤተ

መፅሀፍ እንኳ አልተረፈም። መጣበሻ ሆኗል። እኔና ኢክሩ ቤተ

መፅሀፍ የተቀጣጠርነዉ እኔ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናዬን

የምወስድበት ጊዜ ስለተቃረበ እና በንባብ ተጠምጄ ስለነበር

ነዉ። በነጋታዉ ኢክሩ ደዉላ ከቤተ መፅሀፉ እንድወጣ ነገረችኝ።

ስወጣ በር ላይ ቆማለች። የቤተ መፅሀፉ አጥር ላይ ወዳለዉ

መቀመጫ ሄደን ስለላከችልኝ መልዕክት ማብራሪያ እንድትሰጠኝ

ጠየቅኳት።

"ፊዊ መገናኘታችን ትርጉሙ አልገባኝም። በስልክ ከተደዋወልን

የሚበቃ ይመስለኛል።" አለችኝ። ስታወራ ይብቃን ሳይሆን

እንቀጥል የምትል ነዉ የምትመስለዉ።

ትኩር ብዬ ተመለከትኳት ፣ በረዥሙ ተነፈስኩና "ኢክሩዬ አብሬሽ

በወንድምነት ያሳለፍኩት ጊዜ በጣም ደስ ይል ነበር። አንቺ በቃኝ

ካልሽ ግን ዉሳኔሽን አከብራለሁ።" ብዬ እስክ ቤቷ ድረስ

እንደተለመደዉ ሽኝቼ ተሰናበትኳት። ከዚህ ቀን ጀምሬ ኢክራም

ጋር መደወል አቆምኩ። በሰዓቱ ለፈተና እየተዘገጃጀሁ የነበረ

መሆኑ ብዙም ስለ ኢክራም እንዳላስብ ረዳኝ። ሰዉ መለማመጥ

አልወድም። ኢክራም ከበቃት በቅቷታል አለቀ። ደግሞ ምንም

የተለየ ነገር አልነበረንም።

ግን የእኔ እና እሷ የመገናኛ ዉድ ቀን ማክሰኞን በጉጉት ትናፍቅ

የነበረችዉ ኢክራም ይብቃን ያለችበት ምክንያት ምንድነዉ?

ኢክሩ ልታገባ ነዉ? ፍቅረኛ ልትይዝ ነዉ? ለምን? ምክንያት

እንዳለዉ ገብቶኛል። ግን ምን እንደሆነ አላዉቅም።

.

ይቀጥላል...

ልብ ወለድ

ማንበብ ሙሉ ሰው ያረጋል.....

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል ስድስት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ከኢክራም ጋር መገናኘት ካቆምን ጥቂት ቀናት አለፉ።

እኔም ለፈተና ዝግጅት ቤተ መፅሀፍ ማዘዉተር አበዛሁ።

በዚህ አጋጣሚ እንደኔዉ ተፈታኝ ከነበሩ ሁለት ሴቶች ጋር

በጣም ተግባባሁ። ረዊና እና ሁዳ ይባላሉ። ረዊና ወፈር

ብላ ቀላ ያለች ፣ የደስ ደስ ያላት ቆንጆ እና ትሁት ናት።

ጉንጯ ላይ ስርጉድ አላት። ሲስቁ ጉንጫቸዉ የሚሰረጉዱ

ሴቶች ልቤን ነዉ የሚያሰረጉዱት። ሁዳ ደግሞ ቆማ

መሄጄ በራሱ ተዓምር የሆነ በጣም ቀጫጫ ልጅ ናት።

ከረዊና እና ሁዳ ጋር ያለን ቅርበት በጣም እየጠበቀ

መጣ። ቤተ መፅሀፍ መጥተዉ ይደዉሉልኛል። አብረን

ዉለን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን እንለያያለን። አብረን

መሆናችን ደስ የሚል ደስታ ይሰጠናል። አንዳንዴ

በህይወታችሁ ዉስጥ በድንገት የተከሰቱ ሰዎች ሳታስቡት

የማይረሳ ትዝታ ጥለዉባችሁ ያልፋሉ። ከነሁዳ ጋር

አንዳንዴ የቤተ መፅሀፍቱ ግቢ ዉስጥ እንገናኝና ቤተ

መፅሀፉ ዉስጥ ሳንገባ ቀኑን ሙሉ አብረን እንዉላለን።

ምሳ ሰዓት ላይ የረዊና እህት እምነት ከቤት ምሳ ቋጥራ

ይዛልን ትመጣለች። እምነት ቀይ ፣ በጣም ቆንጆ ፣

የሰዉነት ቅርጿ በጣም የሚያምር ዉብ ልጅ ናት። ቁንጅና

ከቤት ነዉ መሰለኝ። በጊዜዉ እሷ የአስራ አንደኛ ክፍል

ተማሪ ነበረች። እምነት ምሳ እንጂ ወሬ መቋጠር

አይሆንላትም። እራሷ "ሚስጥር አትንገሩኝ መያዝ

አይሆንልኝም" ትል ነበር።

.

አንድ ቀን እንደተለመደዉ ቤተ መፅሀፍ እያነበብኩ እያለ

አንድ የማላዉቃት ልጅ ዉጪ ኢክራም እየጠራችኝ

እንደሆነ ነገረችኝ። ልጅቷ የኢክራም አብሮ አደግ ጓደኛዋ

እና ዘመዷ ነበረች፤ ስሟ ሪሀና ነዉ። ከቤተ መፅሀፉ

ኢክራምን ለማግኘት ወጣሁ። በር ላይ ብሩክን አገኘሁት።

ብሩክ ሰላምታ እንኳ ሳይሰጠኝ አሁን መጥታ የጠራችኝ

የኢክራም ጓደኛ እንደሆነች እና እንዳጣብሰዉ ጠየቀኝ።

የብሩክ ፍጥነት ገርሞኛል። ግን በሰዓቱ ብሩክ የፍቅር

ህይወት ዉስጥ መግባት ይፈልግ እንደነበር ስለማዉቅ

ብዙም አልደነቀኝም። ፍቅረኛ መያዝ ፋሽን ስለሆነ ሁሉም

ስለተፋቀረ ሳይሆን ፍቅረኛ አለመያዙ ከሌሎች

እንዳያነጥለዉ ብሎ ፍቅረኛ ይይዛል። ለምን ብለን

ብንፈትሽ ከመንጋዉ ላለመለየት ከሚል ምክንያት ዉጪ

ምንም አናገኝም።

ኢክራም ግን ግንኙነታችንን እንድናቀዘቅዘዉ ከጠየቀችኝ

በኋላ ዛሬ ለምን ልታገኘኝ እንደመጣች ግራ ገብቶኛል።

ሪሀና እየመራችኝ ኢክራም እየጠበቀችኝ ወዳለበት የቤተ

መፅሀፉ ጀርባ አመራሁ። ኢክራም ዛፍ ተደግፋ ቆማለች።

አሁንም ያ አስደንጋጭ ዉበቷ አብሯት አለ።

.

ሪሀና ኢክራምን ካሳየችኝ በኋላ በነግነት እንድናወራ ትታን

ሄደች። ከኢክራም ጋር መደዋወል ካቆምን ከሁለት

ሳምንታት በላይ ተቆጥረዉ ነበር።

ኢክሩ እየተፍለቀለች "ፊዊዬ አኩርፈኸኛል አይደል?"

አለችኝ። ዘንድሮ እኮ አልቻልንም ጎበዝ!! በራሷ ጊዜ

መገናኘታችን ጥቅሙ አልታየኝም እናቀዝቅዘዉ ያለችኝ

እሷዉ እራሷ ነበረች። "አኩርፈኸኛል አይደል?" ብላ

ጥፋቱን ወደ እኔ ስትጠመዝዘዉ ተመልከቱ።

ፈገግ አልኩና "ኢክሩዬ አላኮረፍኩሽም ፣ መገናኘታችን

ጥቅሙ አልታይ አለኝ ፣ ይብቃን ያልሽኝ አንቺዉ ነሽ። እኔ

ደግሞ የሰዉን ፍላጎት መጠበቅ ላይ ጎበዝ ስለሆንኩ

ዉሳኔሽን እያከበርኩ ነዉ።" አልኳት።

ኢክሩ አይኖቿን እያስለመለመች ዝም ብላ አየችኝ እና

"ፊዊ የሆንክ ጢባራም ነገር ነህ። ታዉቃለህ ግን እኔ

ጢባርህን እወደዋለሁ።" አለችኝ።

ይሄ ነገር ወዴት ወዴት ነዉ? ኢክራም ጢባሬን

ትወድልኛለች? ምን ለማለት ፈልጋ ነዉ? ሰሞኑን

ያመጣችዉ ፀባይ ግራ ነዉ የሆነብኝ። ሲላት ይብቃን ፣

ሲላት ጢባርህን እወድልሀለሁ።

.

ወደ ቤተ መፅሀፍ ተመልሼ ንባቤን መቀጠል ስለነበረብኝ

ኢክራምን ትንሽ መንገድ ሸኝቻት ተመለስኩ።

አሁን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ለመፈተን የቀረኝ ጊዜ

ሁለት ወር አይሞላም። ፈጣሪ ምስጋና ይግባዉና ረዊናን

እና ሁዳን ከተዋወቅኩ ጀምሮ ቤተ መፅሀፍ ስመጣ

አይደብረኝም። የረዊና እህት እምነትም አንዳንዴ አብራን

ትሆን ስለነበር አስደሳች ጊዜ ነበር የምናሳልፈዉ።

እናነባለን ፤ በደንብ ደግሞ እንዝናናለን። ለመዝናናት የትም

መሄድ አይጠበቅብንም። በወራያችን ቤተ መፅሀፉን

ከማንበቢያነት ወደ መዝናኛነት እንቀይረዋለን።

ከብሩክ ጋር በብዛት መገናኘት አቁመናል። ድሮም በብዛት

አንገናኝም ነበር። እኔ ቤተ መፅሀፍ ነዉ የምዉለዉ። እሱ

ደግሞ ቤተ መፅሀፍ መግባት በራሱ ያመዋል። እንደኔዉ

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወሳጅ ቢሆንም እምነቱን

በአስኮራጆቹ ላይ ጥሏል። ሄኖክን በዚህ የፈተና ዝግጅት

ሰሞን በፍፁም አግኝቸዉ አላዉቅም ነበር።

.

ቅዳሜ ቀን ይመስለኛል። የማላዉቀዉ ስልክ ተደወለልኝ።

አነሳሁት።

"ፈዉዛን ሪሀና ነኝ የኢክራም ጓደኛ አወቅከኝ? " አለችኝ

በጣም በቀጭን ድምፅ።

"አዎ አዉቄሻለሁ ባለፈዉ ቤተ መፅሀፍት መጥተሽ

የነበርሽዉ ነሽ አይደል?" አልኳት።

"አዎ ፈዉዛን በአካል አግኝቼ ላናግርህ ፈልጌ ነበር

ይመችሃል እንዴ?" አለችኝ።

"ቤተ መፅሀፍት ነዉ ያለሁት እዚህ መምጣት ትችያለሽ?"

አልኳት።

በአስር ደቂቃ ዉስጥ እንደምትደርስ ነግራኝ ስልኩን

ዘጋችዉ። እንዳለችዉም ለመምጣት ከአስር ደቂቃ በላይ

አልፈጀባትም። ሪሀና ቀጠን ያለችና የደስ ደስ ያላት ልጅ

ናት። ስታወራ በጣም ትፈጥናለች።

መጥታ ስትደዉልልኝ ከቤተ መፅሀፍቱ ወጥቼ አገኝኋት።

"እሺ ሪሀና ለምን ነበር የፈለማሽኝ?" አልኳት።

እየተቅለሰለሰች "ፈዉዛን ስለ ኢክራም ነበር ላወራህ

የመጣሁት። ለኢክሩ ምን አይነት ስሜት አለህ?" አለችኝ።

"እኔ አክራምን እንደወንድም እወዳታለሁ። ለሷ መልካም

ስሜት ነዉ ያለኝ።" አልኳት።

"ይሸዉልህ ፈዉዛን ኢክራም ወሬዋ ሁሉ ስላንተ ሆኗል።

አብረን ዎክ ስናደርግ እራሱ ካንተ ጋር ዎክ

ስላደረጋችሁበት ጊዜ ምናምን ብቻ ነዉ የምታወራኝ። እኔ

እሷ የወደደችህ ይመስለኛል።" አለችኝ።

ፈገግ ብዬ "ኢክራም እራሷ ናት መጥተሽ እንድትነግሪኝ

የላከችሽ?" አልኳት።

"አይ አይደለም እኔዉ ራሴ ነኝ የመጣሁት። የሷን ሁኔታ

ስገምት ያፈቀረችህ ይመስለኛል። አንተ ጋርም ተመሳሳይ

ስሜት ካለ በቃ ጠይቃት እና ፍቅረኛ ሁኑ።" ተነፈሰችዉ።

እንደጓደኝነቷ የኢክራምን ጥቅም ባስከበረ መልኩ ነዉ

እየተደራደረችኝ ያለችዉ። ደግሞ ዉጤቱን በፍጥነት

ለማወቅ ነዉ የፈለገችዉ።

ስልኳን እየሰጠችኝ "ይኸዉ እንካ ደዉልና እንደምትወዳት

ንገራት" አለችኝ። የሪሀና ፍጥነት እያስደመመኝ ነዉ።

ስልክ ለመደወል ፈቃደኛ እንዳልሆንኩ ነገርኳት። በነጋታዉ

ከኢክራም ጋር እንደሚመጡ ነግራኝ ተሰናበተችኝ።

.

ቆይ እኔ ኢክራምን አፈቅራታለሁ እንዴ? ከራሴ ጋር

ሙግት ዉስጥ ገባሁ። የሰሞኑ የኢክራምን የፀባይ

መቀያየር አስታወስኩ። የኔና የአንተ ግንኙነት ትርጉሙ

አልታየኝም ስትለኝ ግንኙነታችንን ትርጉም እንስጠዉ

እያለችኝ መሆኑ እንዴት እንዳልገባኝ ገረመኝ።

ለኢክራም ዉስጤ ላይ መልካም ወንድማዊ ፍቅር እንጂ

የተለየ ስሜት የለኝም። የኢክራምን ዉበት ሁሌም አደንቅ

ነበር ግን ከወንድነት ስሜቴ እንጂ ከፆታዊ ፍቅሬ የመነጨ

አልነበረም።

.

በነጋታዉ ኢክራም እና ሪሀና አንድ ላይ ሆነዉ ቤተ

መፅሀፍ መጡ። አብረዉ እንደሚመጡ አስቀድማ ነግራኝ

ስለነበር ለብሩክ ደዉዬለት መጥቷል። ብሩክ ሪሀናን

እንዳጣብሰዉ ጠይቆኝ ስለነበር እድሉን ተጠቅሜ

ማገናኘቴ ነዉ እንግዲህ።

ብሩክ እና ሪሀና አንድ ላይ ፣ እኔ እና ኢክራም አንድ ላይ

ጥንድ ጥንድ ሆነን የቤተ መፅሀፍቱ ግቢ ዉስጥ እነሱ

በላይኛዉ የቤተ መፅሀፍቱ አጥር በኩል ፣ እኔና ኢክሩ

ደግሞ በታችኛዉ በኩል ተቀምጠናል።

የሪሀና የዛሬዉ እቅዷ እኔ ኢክራምን እንደምወዳት

እንድነግራት

ማድረግ ነዉ። እኔ ጋር ግን ለኢክራም ፆታዊ

የፍቅር ስሜት የለም። ግን የፍቅር ጥያቄዉ ከሷ ከመጣ

ለመቀበል እና በወንድምነት የጀመርኩትን ብቸኝነቷን

የማስረሳት ፕሮጀክት በፍቅረኝነት አጠናክሬ ለመቀጠል

ወስኛለሁ።

ከኢክራ ጋር ማዉራት ከጀመርን የቆየን ቢሆንም

ሁለታችንም ስለፍቅር ጥያቄዉ አላነሳንም ነበር። ሪሀና

ከፊት ለፊቴ ከብሩክ ጋር እንደቆመች ስልክ ደወለችልኝ።

"ወዬ ቀዉሷ"

"እ ፈዉዛን ጠየቅካት?"

"አይ" አልኩ አልጠየቅኳትም ካልኩ ኢክራም ይገባታል

ብዬ መጠንቀቄ ነዉ።

"ፈዉዛን በቃ አሁን ጠይቃት። አሁን!!" አለችኝ።

ስልኩን ዘጋሁት እና ከኢክራም ጋር ወሬዬን ቀጠልኩ። እሷ

ካልጠየቀችኝ ላለመጠየቅ ወስኛለሁ።

ብሩክ እና ሪሀና ዛሬ የተዋወቁ አይመስሉም። በጣም

ጠልቀዉ ገብተዋል። እኔና ኢክራ ወሬያችንን ጨርሰን

ከተቀመጥንበት ተነሳን። ብሩክ እና ሪሀና አሁንም በወሬ

ተመስጠዋል።

"ኧረ በቃችሁ በአንድ ቀን እንዲህ ትሰምጣላችሁ እንዴ?"

ብዬ አቋረጥኳቸዉ።

ከተቀመጡበት ተነስተዉ እኛ ወዳለንበት መምጣት ጀመሩ።

ኢክራምን ሪሀና የት እንደምትማር ጠየቅኳት። መደበኛ

ትምህርት እንዳቋረጠች እና አሁን የፀጉር ሙያ

እየተማረች እንደሆነ ነገረችኝ።

እነ ብሩክ ከተቀላቀሉን በኋላ ኢክሩን እና ሪሀናን

ለመሸኘት የቤተ መፅሀፍቱን ግቢ ለቀን ወጣን። ሪሀና

ኢክሩን ስላልጠየቅኳት በጣም ተበሳጭታብኛለች። አይኗ

ያሳብቃል። ሸኝተናቸዉ ስንመለስ ብሩክን ስለሪሀና

ጠየቅኩት። በጣም እንደተመቸችዉና በጣም እንደተግባቡ

ነገረኝ። ጓደኛዬን የፈለጋትን ልጅ ስላስተዋወቅኩት በጣም

ደስ አለኝ።

የፍቅር ጥያቄዉ እንደተዳፈነ ሊቀር ነዉ? ወይስ ኢክሩ

እራሷ ድፍረት አግኝታ ትጠይቀኛለች? ቀጣዩ ምን

እንደሚሆን ለማወቅ በጣም ጓጉቻለሁ። በጣም!!

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል ሰባት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ማታ ከቤተ መፅሀፍት ተመልሼ ቤት ሳሎን ዉስጥ

ተቀምጫለሁ። ቤት ሁሉም ቴሌቭዥን እያዩ ነዉ። እኔ ፌስቡኬን

ለመጎርጎር ስልኬን አወጣሁ። ፌስቡክ ላይ ስገባ አንድ

መልዕክት አለኝ። ከፊትኩት ኢክራም ነበረች።

"ፊዊ ሪሀና ያለችህን ነገር ነግራኻለች። እኔ አልነበርኩም

እንድትነግርህ የላኳት። ግን እዉነቷን ነዉ። ላንተ የተለየ ስሜት

አለኝ። እና ምን ትላለህ?" ይላል።

ትንሽ ላስጨንቃት ፈለግኩ "ኢክሩዬ ምን ለማለት ፈልገሽ ነዉ?"

ያልገባኝ ይመስል።

"ፈዉዛን እኔ አፍቅሬሀለሁ። እና አንተ ለኔ ምን አይነት ስሜት

አለህ?" አፈረጠችዉ።

መለመን ግን ደስ ሲል ፣ሊያዉም እንደ ኢክሩ ባለች ቆንጆ!!

የፍቅሬ ምርኮኛ ሆና አፈቅርህለሁ ስትለኝ ፣ የኔ ለመሆን

ይሁንታዬን ስትለምነኝ ። ጥርሴ ሳይሆን ልቤ መሳቅ ጀምሯል።

ሲፈጥረኝም መለመን እወዳለሁ። ግን መለመን የምወደዉ

የበላይነቱ በኔ እጅ ላይ እንዲሆን ነዉ። የበላይነቱ በእኔ እጅ ላይ

እንዲሆን የምፈልገዉ ደግሞ መልሱን ይሁንታ ለማድረግ ነዉ።

አዉቅላችኋለሁ ከሚሉት ወገን ነኝ።

.

ዘፋኙ "አሸነፈ ልቤ ሸጋ ልጅ ወደደ

በፍቅር ሰከረ በደስታ አበደ።" አይደል ያለዉ። አስቡት እሱ እኮ

ሸጋ ልጅ ወዶ ነዉ እንደዚህ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለዉ። እንደኔ ሸጋ

ልጅ ብትወደዉ ምን ብሎ እንደሚዘፍን እንጃለት። እሺ ኧረ

ከሸጋም ልጅ ኢክሩ ብታፈቅረዉ ምን ሊዉጠዉ ነዉ? ስገምት

ሙስሊም ከሆነ ፈጣሪዉን ለማመስገን እንደ መልአክቱ በግንባሩ

እንደተደፋ ትንሳኤ ይደርሳል። ክርስቲያን ከሆነ ደግሞ አለም

በቃኝ ብሎ ይመንናል። እንዴ በአይንአፋሯ ኢክሩ እኮ ነዉ

የተፈቀረዉ፣ በዉዷ ኢክሩ!! ለየት ያለ ስሜት አለዉ። ከዚህ ሁሉ

አድናቆቴ ጋር ግን ለኢክሩ የፍቅር ስሜት አልነበረኝም።

.

ኢክራም መልስ ሳልሰጣት ስዘገይ "እ?" ብላ ላከችልኝ። መልሱን

አፍጥነዉ ማለቷ ነዉ እንግዲህ። ከዚህ በላይ ልቧን መስቀል

ወንጀል እንዳይሆንብኝ ለመልሴ የምትሆን ቆንጆ እንግሊዘኛ

የፍቅር አባባል ከጎግል ኮፒ አድርጌ ላኩላት። ጎግል ዉሎ ይግባ

እንጂ የሴቶቹን ቀልብ ለማቅለጥ ምርጥ ምርጥ የእንግሊዘኛ

አባባሎች ኢንተርኔት ላይ ሞልተዋል።

ኢክሩ በደስታ ሳታብድ አትቀርም። እንግዲህ እኔም እንደመንጋዉ

ባለፍቅረኛ መሆኔ ነዉ። ያቺ ለሊት ባለፍቅረኛ ሆኜ ያደርኩባት

የመጀመሪያዋ ለሊት ነበረች። ልዩ ከመሆን ዙፋኔ ዝቅ ብዬ

መንጋዉን የተቀላቀልኩባት ለሊት!!

ትራስ አቅፌ መንከባለል ሁላ አምሮኝ ነበር። ቤት ሰይጣን

ተጠጋዉ ብለዉ ቁርዓን እንዳያስቀሩብኝ ፈርቼ ተዉኩት።

ምክንያቱም ቤት ሲያዉቁኝ በጣም ፎርማል ነኝ። ልጅ ልጅ

አያጫዉተኝም። ብታዩኝ እኮ ጠይቄያት እሺ ያለችኝ ነዉ

የምመስለዉ። በዚህ አይነት እሷ እንዴት እንዴት እየሆነች

እንዳደረች ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ።

እንግዲህ እስካሁኗ ሰአት ድረስ እኔና ኢክሩ ፍቅረኛ መሆናችንን

ያወጋነዉ በፌስቡክ ነዉ። በነጋታዉ ወደማታ ገደማ ኢክራም

ደወለችልኝ። አሁን የማወራዉ በወንድምነት ከማዉቃት ኢክራም

ጋር ሳይሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅረኛዬ ከሆነችዉ ኢክሩ ጋር

ነዉ። የመጀመሪያዬ ስለ መርየምስ ትሉ ይሆናል እኮ!! መርየምን

እወዳት ነበር እንጂ ከሷ ጋር የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ አልገባሁም

ነበር።

ስለኩን አነሳሁትና ያዉ ፍቅረኛዬ እንደመሆኗ አነጋገሬን ወደ የኔ

ቆንጆ ምናምን አሳድጌ አወራኋት። መጨረሻ ላይ ልሰናበታት ስል

የፍቅር ጥያቄዋን መቀበሌን ማረጋገጫ እንዲሆናት ብዬ

"እወድሻለሁ" አልኳት። የእዉነት እንዲህ መሚዘገዝ አይመቸኝም

ግን የሷን ስሜት ለመጠበቅ ብዬ ያደረግኩት ነበር። ፍቅር

የቃላት ጨዋታ አይደለም። ማንነትን የመቀበል ጉዳይ ነዉ።

ትናንት የማታዉቃትን ሴት የእኔ የምትልበት ቀመር ነዉ።

ኢክራም ስቃ አላባራችም። "አትሚዘገዝ ባክህ!! እኔ እወድሻለሁ

ምናምን መባባል ደስ አይለኝም።" አለችኝ።

ኦኬ ተግባሩ ነዋ የሚመቻት!! በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ሰፈር

መሆናችን ደስ ብሎኝ ተሰናበትኳት። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነበር

አሁን እኔ መሰበሬን ለመርሳት የመጣሁበት ካፌ መመላለስ

የጀመርነዉ።

ከፊት ለፊቴ ተቀምጠዉ የሚሳሳቁት ጥንዶች አሁንም በወሬ

እንደሰመጡ ናቸዉ። አስተናጋጇ ረሂማ አጠገቤ መጥታ "ምነዉ

ሳፊዉ ወተቱ ላይ ችግር አለ እንዴ?" አለችኝ ሳቋ እየፈነዳ።

ይህቺ ልጅ ፈዉዛን የሚለዉን ከነጭራሹ ትታ ሳፊዉ ትለኝ ጀመር

ማለት ነዉ?

ያዘዝኩትን ወተት አልነካሁትም ነበር። ረሂማ አክብሮቷ እና

ተጫዋችነቷ ከስራዉ ጋር የተስማማ ነዉ።

"አይ ችግር የለዉም ከካፌ ሀሳብ ዉስጥ ሰምጬ ቀዘቀዘ"

አልኳት።

ወዲያዉ ወተቱን አሙቃ ልታመጣልኝ ይዛዉ ሄደች። እኔም ወደ

ሀሳቤ ተመለስኩ።

.

እንግዲህ ኢክራም እና እኔ ፍቅረኛሞች ስንሆን በመካከላችን

ሚስጥር የሚባል ነገር ጠፋ። ምንም አልደብቃትም። እሷም

ምንም አትደብቀኝም። የሆነ ትልቅ ሰላም ልቤ ዉስጥ ሲሰፍን

ይሰማኛል። ሌላ ቤተሰብ ያገኘሁ ያህል ነዉ የተሰማኝ።

ስናፈቅር ግን የሆነ ጅል የሚያደርገን ነገር አለ አይደል? እኔ ህግን ሆኜ እንኳ የህፃናት ጨዋታ የማይጥመኝ ልጅ ነበርኩ። አሁን ግን ከኢክራም ጋር እንደመጀጃል የሚያስደስተኝ ነገር የለም።

በነገራችን ላይ እኔና ኢክሩ ጋር እንደ ፍቅረኞች አለ አይደል መንነታተል መሳሳም ምናምን የለም። እሱንም እሷ እስክትጀምር እየጠበቅኩ ይሁን አላዉቅም።

ሁለታችንም መስጂድ ጀመዓዎች(ህብረቶች) ላይ ስለምንሳተፍ እምነታችን ላይም ጠበቅ ያልንበት ሰዓት ስለነበር እንኳን ሌላ ነገር ቀርቶ አንጨባበጥም ነበር።

ከኢክሩ ጋር ስለ ህይወታችን እናወራ፣ ምክር የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ሲገጥመን ደግሞ ሳንደባበቅ እንወያይ ነበር። ኢክሩ ላይ ስሜቴን ለማስተናገድ ብዙም ትኩረት አልሰጥም ነበር። እሷን የሚያስደስታትን ነገር ማድረግ ፣ የሷን ስሜት መከተል የህይወቴ ህሁ ሆነ። ፍቅረኛሞች ይሳሳማሉ!! እኔና ኢክሩ አንሳሳምም ግን ፍቅረኞች ነን። ፍቅረኛሞች ይተቃቀፋሉ እኔና ኢክሩ አንተቃቀፍም ግን ፍቅረኞች ነን!! ህይወታችን ነገን በማለም ተወጥናለች። ስለመጋባት ነዉ የምናልመዉ። ምንም እንቅፋት ይኖራል ብለን ማመን አንፈልግም። ገና ተማሪዎች ነን ግን እንደምንጋባ እናምናለን ሊያዉም በቅርብ ጊዜ ዉስጥ!!

.

ስናፈቅር እንታወራለን መሰለኝ። እኔና ኢክሩ እንቅፋቶቹ ሁሉ አይታዩንም። አንዳንዴ ስለ ልጆቻችን ብዛት ረዥም ሰአት እንከራከራለን። ኢክሩ እንደነገርኳችሁ የፊልም ሱስ አለባት ያዉ ብቸኛ ወዳጇም እሱ ነበር። ስንጋባ ፊልም መከታተል እንደምታቆም ነገርኳት። እሷም ወዲያዉ ስንጋባ እንደምታቆም

ቃል ገባችልኝ። ቆይ ግን ምን አይነት ጋፊጣ ለመጋባት

የሚጎድሉንን ነገሮች ጋርዶብን ነዉ? አሁን ላይ ሳስታዉሰዉ

በጣም ይገርመኛል።

አንድ ቀን እኔና ኢክሩ እያወራን ኢክሩ መሀል ላይ ኮስተር አለችና

"ፊዊ ግን ሁሌ ስደዉልልህ እቤት ሆነህ አታዉቅም። ለምንድን

ነዉ ቤት የማትቀመጠዉ?" አለችኝ።

"ኢክሩዬ እኔ ቤት መቀመጥ አይሆንልኝም። የምሄድበት ባይኖር

እንኳ ዉጣ ዉጣ የሚለኝ ነገር አለ።" አልኳት።

"ስንጋባ ግን ከስራ መልስ ሁሌም ቤት ነዉ የምትሆነዉ እሺ!!"

አለችኝ እየተቆጣች።

"እሺ የኔ አይጥ ካንቺ ጋር ብቻ ነዉ የምሆነዉ የትም አልሄድም።"

አልኳት እየሳቅኩ።

.

በቃ ለመጋባት ሳምንት የቀራቸዉ ጥንዶች ነበር የምንመስለዉ።

ለመጋባት የነበረን ጉጉት ይመስለኛል ለመሳሳም እና ለመሳሰሉት

እንዳንቸኩል ያደረገን። አሊያም ለእምነታችን የነበረን ክብር

እምነታችን እነዚህን ተግባሮች የሚፈቅድበትን ትዳር የተባለ

ተቋም ለመመስረት እንድናልም አደረገን።

ከኢክሩ ጋር ጣፋጭ ጊዜ እያሳለፍን ቀናት ደግሞ መ

ቁጠራቸዉን

ቀጥለዉ ፤ እኔ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና መፈተን ጀምሬ ሁለት

ቀናት ተፈትኛለሁ። ፈተናዉ የተጀመረዉ ሀሙስ ቀን ስለነበር

ሀሙስ እና አርብ ተፈትነን ቅዳሜ እና እሁድ አርፈን ሰኞ እና

ማክሰኞ ነበር የሚቀጥለዉ። እሁድ ቤተ መፅሀፍት ግቢ ዉስጥ

እንደተለመደዉ ከረዊና እና ከሁዳ ጋር ተቀምጠን

እየተጨዋወትን ነዉ። ኢክራም ልታገኝኝ ወደ ቤተ መፅሀፍ

መጣች። ኢክሩ ስትደርስ ከነረዊና ገንጠል ብዬ ተቀበልኳት።

ኢክሩ ትንሽ ግራ የመጋባት ስሜት ይታይባታል።

.

ሰላምታ ተሰጣጥተን እንደቆምን

"ፊዊ ከኔ ሌላ ብዙ ሴቶች አሉ።" አለችኝ።

ፈገግ ብዬ "ሞልተዋል እንዳንቺ ቆንጆ አይደሉም እንጂ!!"

ኢክሩ አመረረች "ምናልባት እኔ ያንተ ባልሆን ሌላ ሴት አግባ

እሺ!!" አለችኝ። ይህቺ ልጅ ዛሬ ምን የሚል ፊልም አይታ መጥታ

ነዉ እንዲህ የምትቀባጥረዉ? እኔ ለንግግሯ ትኩረት መስጠት

አልፈለግኩም አይን አይኗን እያየሁ

"ኢክሩዬ እኔ አንቺን ካላገባሁ ሌላ ሴት አላገባም።" አልኳት።

"ይኸዉልህ አግባ!! ከኔ የተሻሉ ቆንጆ እና ጥሩ ሴቶች አሉ።

የሚፈጠረዉ አይታወቅም" አለችኝ። ዛሬ ምን እንደነካት ግራ

ገብቶኛል።

በረዥሙ ከተነፈስኩ በኋላ "ኢክሩ እኔ ወደፊት ትዳር የሚባል

ነገር ላለመመስረት ለራሴ ቃል በገባሁበት ሰአት አንቺ ወደ

ህይወቴ መጣሽ። ከዛ ለትዳር እንድጓጓ አደረግሽኝ። አንቺን

ካላገባሁ ማንንም አላገባም። ይሄ ደግሞ ከመጀመሪያዉም የኔ

አቋም ነበር።" አልኳት።

ኢክሩ መልስ ሳትሰጠኝ ፈገግ ብላ እንድሸኛት ጠየቀችኝ።

መጀመሪያ እነረዊናን እንድትተዋወቃቸዉ ወደ ተቀመጡበት ቦታ

ይዣት ሄድኩ።

.

የረዊና እህት እምነት ምሳ ይዛ መጥታ ከነረዊና ጋር

ተቀምጣለች። ሁሉንም አስተዋዉቂያት ሸኘኋት።

ሽኝቼያት ስመለስ ረዊና እና እምነት የኢክራምን ቁንጅና እያደነቁ

መቀመጫ አሳጡኝ። እኔ ግን የማስበዉ ስለዛሬዉ የኢክራም

እንግዳ ፀባይ ነዉ። "ከኔ ሌላ ሴት አግባ!!" "ከኔ ሌላ ቆንጆ እና

ጥሩ ሴቶች አሉ!" ምን ለማለት ፈልጋ ነዉ? የፍቅር ግንኙነት

ከጀመርን ሁለት ወራት ሊሞላ ነዉ። እና ምን ተፈጠረ?

.

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል ስምንት

(ፉአድ ሙና)

.

.

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ጨርሰን ሁላችንም በደስታ

አብደናል። ረዊና ሁዳ እና እኔ በያለንበት ነፃነት ተሰምቶናል።

አሁን ዉጤቱን የምንጠባበቅበት ጊዜ ነዉ። ከዚህ ሁሉ ደስታ

መሀል ደግሞ ያሳዘነን ነገር አለ። ከዚህ በኋላ እንደከዚህ

ቀደሙ ቤተ መፅሀፍት ተሰብስበን የምናሳልፋቸዉ ዉብ ቀናት

አይኖሩም። ለማንኛዉም ላለመጠፋፋት ተመካክረን በፈተናዉ

ማለቅ አብደናል።

ኢክሩ ደዉላ "እንኳን ከኔ እኩል ነፃ ለመሆን አበቃህ!!" አለችኝ።

እሷ ከኔ ቀድማ ነበር የመሰናዶ መግቢያ ፈተና የወሰደችዉ።

ኢክሩ በነጋታዉ ረቡዕ ዕለት እንደምንገናኝ ነግራኝ ስልኩን

ዘጋችዉ።

ኢክሩ ግን አንዳንዴ ሳስባት እናት ነገር ናት እኮ! ስለአንድ ጉዳይ ስጨነቅ የምትሰጠኝ ምክሮች ሁሌም ወኔ ይሆኑኝ ነበር። ትልቁ ችግሯ የነበረዉ ካፌ መግባት አይመቻትም ነበር። በኋላ ላይ ነዉ እንደምንም እያሳመንኳት ወደዚህ ካፌ መመላለስ የጀመርነዉ። እሱንም እኔን ወጪ ላለማስወጣት ብላ ነበር። ከኔ እኔን እንጂ ሌላ ምንም አትፈልግም። እኔም ከሷ ኢክራምን እንጂ ምንም አልፈልግም። ዛሬ ደስታ አፍኖኛል። ፈተና ጨርሻለሁ ምንም የሚያስጨንቀኝ ነገር የለም።

ማክሰኞ ከከሰዓት በኋላን ከብሩክ ጋር ፊታ እያልን አሳለፍነዉ። ረቡዕ ጠዋት ላይ ኢክራም እና ሪሀና ደዉለዉ እንድንወጣ ነገሩን። በሰዓቱ እኔም እነ ብሩክ ቤት ስለነበርኩ ከብሩኬ ጋር ሆነን አገኘናቸዉ። በነገራችን ላይ ብሩኬ እና ሪሀና የሌለ ፎንቃ ዉስጥ ሰምጠዋል። እንደዉም እነሱ መጎሻሸም መሳሳሙንም በደንብ እያስተናገዱት ነዉ። እኔ ከኢክራም ጋር ለመሳሳምም ሆነ ለመጎሻሸም ብዙም ፍላጎት የለኝም ፤ እሷም ላይ አላየሁም። እኔና ኢክራም አንድ ላይ ፣ብሩኬ እና ሪሀና አንድ ላይ ፤ዋንድ ጥንድ ሆነን ከነ ብሩኬ ቤት ወደኛ ቤት በሚወስደዉ መንገድ አድርገን ከአንድ ትምህርት ቤት ጀርባ ላይ ያለ ከፍታ ቦታ ላይ ተቀመጥን።

.

ኢክሩ ፊቷን ለቀቅ ጨምደድ ታደርገዋለች። የዉሸት ፈገግታ ፊቷ ላይ ይታየኛል። ሪሀና እና ብሩኬ ከኛ ትንሽ ፈቀቅ ብለዉ ተቀምጠዋል።

ኢክራም መሬቱን በስንጥር ትጭራለች። ግራ አጋባችኝ!

"ፈዊዬ እኔ እወድሀለሁ።" ንግግሯ በእንባ የታጀበ ነዉ። መሬቱን በሀይል እየጫረች መናገር ቀጠለች

"ፊዊዬ እኔ እራስወዳድ ልመስልህ እችላለሁ። ግን ወድጄ

አይደለም።"

"ኢክሩዬ ተረጋጊና ምን እንደተፈጠረ ንገሪኝ።"

"ፊዊ ላገባ ነዉ!!" መብረቅ አናቴን የፈረከሰዉ ነዉ የመሰለኝ

ደርቄ ቀረሁ።

"ኢክሩ እንዴት?"

"ፊዊ የቤተሰቤን ሁኔታ ታዉቃለህ። እኔ ካላገባሁ እናቴ ህይወት

የላትም። አሁን ማግባት እንዳለብኝ ወስነዋል። እኔም እነሱን

ከዚህ በላይ ማስጨነቅ አልፈልግም።" ድምጿ በሳግ ታፍኗል።

ከነዛ ዉብ አይኖቿ መንታ መንታ እንባዎች እየተሽቀዳደሙ አገጯ

ስር ይሸሸጋሉ። ስታለቅስ እንባዎቿን እያየሁ አዳምጣታለሁ።

ለቅሶዉን አላቋርጣትም። በእንባዋ ዉስጥ ብዙ ታሪክ

ይነበባሻል። አባትን ማጣት ፣ የድሀ ልጅ መሆን ፣ ብቸኝነት፤ ብዙ

ብዙ በእንባዋ ዉስጥ የተከተቡ ድርሳናት አሉ።

ራሴን ማረጋጋት እንዳለብኝ ወሰንኩ። እንደምንም ራሴን

አረጋግቼ

"ኢክሩ ሁሉም ነገር ይገባሻል። አንቺ ፈልገሽ ያደረግሽዉ ነገር

የለም። እረዳሻለሁ ህይወትሽ ይገባሻል። አይዞሽ ለመልካም

ነዉ።" አልኳት።

ኢክሩን ከዚህ በላይ ፊቴ ስታገዝን ማየት አልፈለግኩም ፤ ሁሉንም

ረስታዉ የመጨረሻ ቀናችንን እንድናስዉበዉ ፈለግኩ። ፈገግ

አልኩ ኢክራምን በፈገግታዬ ፈገግ እንድትል አስገደድኳት።

እኔና ኢክሩ ከመቀመጫችን ስንነሳ ሪሀናና ብሩክም ወዲያዉ

ብድግ አሉ። ለካ የዛሬዉ ቀጠሮ እኔን ለማርዳት ነበር። ሪሀና እና

ብሩክ አስቀድመዉ ሁሉንም ነገር ያዉቃሉ። ከአሁን አሁን ምን

ይላል እያሉ እኔን በአይናቸዉ እየሰለሉ ነዉ። ባለፈዉ ኢክራም

ቤተ መፅሀፍት መጥታ "ከኔ ሌላ ጥሩ ሴት አለ!!" ምናምን

ያለችኝ ቅኔዉ አሁን ተፈታልኝ። በሰዓቱ ያልነገረችኝ ፈተና

ስላልጨረስኩ እንዳልረበሽ ብላ ነበር። ለራሷ አፍናዉ ስትሰቃይ

ነበር!! ኢክሩዬ የኔ ሚስኪን!!

.

ኢክሩን ወደ ቤቷ ስሸኛት በቻልነዉ መጠን መንገዱን ለማስረዘም

ዙሪያ ጥምጥም ተሽከረከርን። በመሽከርከር ብዛት ጋብቻዉ

ይሰረዝ ይመስል። መንገዱ ላይ በጠጠር ኳስ እየተጫወትን

ለጊዜዉም ቢሆን ጭንቀቷን እንድትረሳዉ ለማድረግ ሞከርኩ።

እሷ ፊት ሀዘኔን አሳይቼ የባሰ እንድትጎዳ አልፈለግኩም።

ኢክሩዬን የዛን ቀን ወደ ሪሀና ቤት ነበር የሸኘኋት ፣

እስከመጨረሻዉ የቻልነዉን ያህል መንገዱን ለማስረዘም

ብንሞክርም እነሪሀና ቤት ደረስን። ልቤ ዉስጥ የታመቀዉን

ሀመም እኔ ነኝ የማዉቀዉ። ጥርሴ ግን ይስቃል። ሰማዩ

ያጉረመርማል።

"ኢክሩዬ በቃ ቻዉ!!" ድምፄ ዉስጥ ስቃይ አለ!!

"ፈዊዬ ቻዉ!!" እንባዋ ለመፍሰስ ከአይኗ ጋር ይታገላል።

ኢክሩን ድጋሚ ስታለቅስ ማየት አልፈለግኩም። ብሩክ ከርቀት

ቆሞ እየጠበቀኝ ነዉ። ሪሀና ወደ ቤት ገብታለች። ዞሬ ብሩክ

ቆሞ ወደሚጠብቀኝ ቦታ ስሄድ ዝናቡ መዝነብ ጀመረ። ከብሩኬ

ጋር ሮጥ ብለን ሱቅ ስር ተጠለልን። ሱቁ ስር ቆሜ ኢክራምን

ከርቀት ተመለከትኳት አይኖቿን እየጠራረገች ወደነ ሪሀና ቤት

ሄደች። ኢክሩን ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ ይሆን የማያት? ግራ

ተጋብቻለሁ። ብሩክ ዝናቡ ሀይሉ ሳይጨምር እንድንሮጥ

ጠየቀኝ። እየሮጥን ከነ ሪሀና ሰፈር ወጣን። ወደነ ብሩኬ ሰፈር

መግቢያ ጋር ስንደርስ ዝናቡ በሀይል መዝነብ ጀመረ። አንድ ፎቅ

ስር ገብተን ተጠለልን። ፎቁ ስር ረዊና እና ሁዳን አገኘናቸዉ።

ተያይዘን ፎቁ ላይ ወዳለዉ ካፌ ገባን።

ረዊና እየተሸኮረመመች "ፈዊዬ ቀሽቷ ሚስትህ እንዴት ናት?"

አለችኝ።

ምን ልበላት? አሁን ነዉ ቁርጤን አዉቄ የመጣሁት። ፈገግ ብዬ

"ደህና ናት" አልኳት። በደህና ናት ዉስጥ ስንት ስቃይ፣ ምን

ያህል ህመም እንዳለ ማን ይረዳል? ማንም። ሰዉ የፈለገ

ተሰቃይቶም እንዴት ነህ ብትለዉ "ደህና ነኝ" ነዉ የሚልህ።

ቁጭ አድርገህ "ችግር አለ?" ስትለዉ ነዉ ስቃዩን

የሚዘረግፈዉ። "ደህና ነህ?" እኮ ጥያቄ አይደለሁም ብሎ ራሱን

ሰላምታ ካደረገ ቆየ። "ደህና ነህ?" ይሉት ሰላምታ በጣም

ይቀፋል።

.

ከነረዊና ጋር ተጨዋዉተን ዝናቡ ሲያባራ ሁዳ ሂሳብ ከፍላ

ወጣን።

ኢክሩን የእዉነት አጥቼያታለሁ የሚል ስሜት እየተሰማኝ

አይደለም። ቅዠትም ቀልድም ይመስለኛል። ገና ከእዉነታዉ ጋር

ለመጋፈጥ አልደፈርኩም።

እንዴ እኔና ኢክሩ እኮ የመጋባት እቅድ አለን። እኔና ኢክሩ እኮ

የምንወልዳቸዉ የልጆች ብዛት ላይ ብዙ ተከራክረን ተስማምተን

ወስነናል። ኢክራም እኮ ከኔ ጋር ስትጋባ ፊልም መከታተል

ለማቆም ቃል ገብታልኛለች። እኔ እኮ ለኢክሩ ስንጋባ ከስራ

መልስ ሁሌ ቤት ከሷ ጋር ለመሆን ቃል ገብቼላታለሁ። ኢክሩ እና

እኔ እኮ ጁምዓ(አርብ) ቀንን ቤታችን ዉስጥ እንደ ኢድ

አድምቀነዉ ለማሳለፍ ተስማምተናል። እና ይሄ ሁላ ህልም

ገደል ሊገባ ነዉ? የኢክሩን ሙብ አይኖች ዳግመኛ ላላይ?

ማነዉ ከዚህ በኋላ የኔን ህይወት እንደ ኢክሩ ተረድቶ

የሚያማክረኝ? ኢክሩ እኮ ያልገባችበት የህይወቴ ጓዳ የለም!!

ቤተሰቤ እኮ እሷ ነበረች። እሺ ኢክሩዬ 'ደ'ን እየተኮላተፈች ስትል

ላልሰማ ነዉ? ቆይ ግን ማነዉ ትዳርን እንዲህ ከባድ ያደረገዉ?

ለምን ኢክራምን እኔ አላገባትም? ለምን ኒካህ ታስሮልን

ራሳችንን እስክንችል በየቤታችን አንኖርም? ሀብታም ካልሆነ ሰዉ

አያገባ ያለዉ ማነዉ?

ማነዉ ጥፋተኛዉ? ቤተሰቦቿ? እነሱ ስለኔ መች ያዉቃሉ?

እንደዉም እኔ ነኝ ተጠያቂዉ በዚህ ሰአት ሀብታም ሆኜ ኢክራምን

የማትፈልገዉ ሰዉ ሚስት እንዳትሆን ማድረግ ያቃተኝ ቀሽም ሰዉ

እ

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል ዘጠኝ

(ፉአድ ሙና)

.

.

ኢክራም ከህይወት መስመሬ ወጥታ ወደማትፈልገዉ ሰዉ

የህይወት መስመር ዉስጥ ልትገባ እንደሆነ ያወቅኩበት ጨለማ

ቀን መሸ። ከብሩክ ጋር ተለያይተን ቤት ገባሁ። ኢክሩን መርሳት

ይኖርብኛል። ትዳር ዉስጥ ልትገባ ነዉ። ልረብሻት አልፈልግም።

የእዉነት ካሰብኩላት ዝም ከማለት ዉጪ ምንም ማድረግ

የለብኝም። መዉደድ የወደዱትን የራስ ማድረግ ብቻ አይደለም።

እንደሻማ እየቀለጡ ሌሎች ለቤተሰባቸዉ ሲሉ እንዲያደርጉት

የተገደዱትን ነገርም እንዲያደርጉ መፍቀድ ነዉ። የአይዞሽ

ባይነት ፈገግታን መሳየት መቻል!! ማድረግ ያለብኝ እሱኑ ነዉ።

በጊዜዉ የማስተዳደር አቅም ኖሮኝ የኔ ላደርጋት አልችልም።

ያለኝ ምርጫ የሚሆነዉን እጇን አጣጥፌ መመልከት ብቻ ነዉ።

.

ስልኬን አዉጥቼ ፌስቡክ ላይ ስገባ ኢክሩ ፕሮፋይል ፒክቸሯን

ደም በምታነባ ሴት ፎቶ ቀይራዋለች። ሰው በሰርጉ መዳረሻ

የሰርጉን ቀን ናፍቆ የደስታ መግለጫ ይፖስታል እሷ ደም

በምታነባ ሴት ምስል ስታይዋን ትነግረኛለች። ይሄ ሰርግ

ለኢክራም አዲሱን ባሏን የምታገባበት ሳይሆን ባሏ እንዲሆን

የምትፈልገዉንና ሚስቱ እንድትሆን የሚመኛትን ሰዉ ከህይወቷ

የምትገነጥልበት ምዕራፍ ነዉ።

ሁሉ ነገሬን የቻለችኝ እኮ ኢክሩ ነበረች!! የእምነት ጥንካሬዬ ዝቅ

ብሎ ሙዚቃ በግድ ሳስደምጣት ዞር በልልኝ አላለችኝም፣ አቋሜ

እስኪስተካከል ቻለችኝ!! እንደድሮዉ እንድሆን አደረገችኝ!! እና

እኔ እንዴት ይህቺን ልጅ ማጣቴን ልመን?

ብሎክ ላደርጋት አሰብኩ ግን ስለኔ ሁኔታ ለማወቅ አካዉንቴን

መንብኘት መፈለጓ ስለማይቀር አንፍሬንድ ብቻ አደረግኳት። ልብ

ለልብ ስትግባቡ አጋራችሁ ምን እንደሚፈልግ ሳይነግራችሁ

ታዉቃላችሁ። አዎ ኢክሩ አካዉንቴ ላይ እየገባች ሁኔታዬን

ለመከታተል መፈለጓ አይቀርም። በልቤ የሆነ ሰዉ በቀሰቀሰኝ ፣

ምነዉ በህልሜ በሆነ እላለሁ።

.

እጇን ቆነጠጥኩት፣ አመመኝ፤ አዎ በእንቅልፍ ልቤ አይደለም።

አልጋዬን አየሁት በጣም ሰፋኝ። ከዚህ በፊት ሳየዉ ኢክሩ

ልጃችንን አልጋዉ ላይ ስታጫዉተዉ ነበር በእዝህሊናዬ

የማይበት። ዛሬ ጭር ያለ ሜዳ መሰለኝ።

ኢክሩን ከኔ ሌላ የሆነ ወንድ ሊያገባት ነዉ። እሺ ታግባ!! ግን እኮ

የምትፈልገዉን ሰዉ አይደለም የምታገባዉ!! እኔን

የሚያንገበግበኝ ኢክሩ የምትወደዉን ሰዉ አለማግባቷ ነዉ።

ከብቸኝነት ብርዷ ዉስጥ መቀት ለመፍጠር በወዳጅነት

በቆየንባቸዉ ቀናት እና ፍቅረኛ ሆነን ባሳለፍናቸዉ ጊዜያት ዉስጥ

ይሄ ባል ተብዬ መጥቶ እስኪበጠብጠን ብዙ የኢክራምን

የህይወት ታሪኮች አዳምጫለሁ። ሁሉም የህዘን ታሪክ ናቸዉ።

ዛሬ የማትፈልገዉን አታግባ የምለዉ ቢያንስ ቀሪ ህይወቷን ፊቷ

በፈገግታ ተዉቦ ደስተኛ ሆና እንድታሳልፍ ስለማልም ነዉ። እሷ

የምትወደዉ ሰዉ ደግሞ እኔ ነኝ። የኔ ህልም ደግሞ ኢክሩን

ደስተኛ ማድረግ ነበር። ምን ያደርጋል ነበር ሊሆን ነዉ!!

ከህይወቷ እንደጨረቃ ቤት ልፈርስ ነዉ። ለነገሩ ትዳር

ያልመሰረቱ ጥንዶች ምሳሌ እንደጨረቃ ቤት ነዉ። ቤተሰብ

ሴቷን ለልማት ሲፈልጋት ጥምረታቸዉን ያፈርሰዋል። ልማቱ

ደግሞ ትዳር ነዉ። ምን ነበር የማልማት አቅሙ በኖረኝ!!

.

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሳ ቤት ዉስጥ ማንም የለም። ባዶ ቤት

ዉስጥ ባዶነት የተሰማኝ እኔ ብቻ አለሁ። አሁን ከእዉነታዉ ጋር

ፊት ለፊት ተጋፈጥኩ። ኢክራም ሌላ ሰዉ ልታገባ ነዉ። እንደዛ

የምሳሳላት ቆንጆ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር የከነፈችልኝ ሴት

ልታገባ ነዉ። የማትፈልገዉን ሰዉ እንደምታገባ ሳስብ በጣም

ከፋኝ። አልጋዬ ላይ እንዳለሁ እንባ ከአይኖቼ ፈሰሰ። ሰዉነቴ

መንዘፍዘፍ ጀመረ። ተንሰቀሰቅኩ። ወንድነቴ ትጥቁን ፈቶ

ተማረከ ፣ ለአምስት ሰዓታት ተነፋረቅኩ።

ኢክሩን እያሰብኩ አልቅሼ ሲበቃኝ አምስት ሰዓት ላይ ብሩክ ጋር

ደዉዬ ቤት እንዲመጣ ነገርኩት።

ቤት መጥቶ አብረን ቁጭ እንዳልን ብሩኬ "ፈዉዛን በተፈጠረዉ

ነገር በጣም አዝኛለሁ!!" አለኝ።

የብሩኬ ንግግር ስሜቴን አገነፈለዉ። ተንሰቅስቄ ማልቀስ

ጀመርኩ።

"ብሩኬ እኔ እኮ የሚያሳዝነኝ መለያየታችን አይደለም። ግን ኢክሩ

የማትፈልገዉ ሰዉ ላይ ልትወድቅ ነዉ።" እያልኩ እንሰቀሰቃለሁ።

ብሩክ አቅፎኝ ማልቀስ ጀመረ። ተላቅሰን ሲያባራልን ተነስተን ወደ

ብሩክ ቤት ሄድን።

ብሩኬ መንገድ ላይ ሆነን "ፈዊ ግን የኢክራም ቤተሰቦች በጣም

ደደብ ናቸዉ።" አለኝ እልህ እየተናነቀዉ።

"ያሉበት ሁኔታ ይሆናል ያስገደዳቸዉ።" አልኩት የኢክሩ ቤተሰቦች

ሲሰደቡ ኢክሩ የተሰደበችብኝ ያህል ነበር የተሰማኝ።

አሁን ላይ ሳስበዉ የዛን ቀኑ የብሩኬ ሁኔታ ያስቀኛል። እኔን

እንደማባበል እሱ ራሱ ተንሰቅስቆ ያለቅሳል።

.

እኔና ኢክሩ ከተለያየን ቀናት አልፈዉ ሳምንታት ተተኩ። ሰዉ

አጠገቤ ሲኖር ህመሙን እረሳዋለሁ። ብቻዬን ስሆን ግን እሷን

ብቻ ነዉ የማስበዉ። የኢክራም ጓደኛ ሪሀና አንዳንዴ እየደወለች

ታፅናናኛለች።

ጌታዬን ለመንኩት!! ህይወቷን ያማረ እንዲያደርግላት ፣ ባሏንም

ለሷ ጥሩ እንዲያደርግላት ተማፀንኩት። ምንም ብወነጅለዉ

ጌታዬን ለምኜዉ ከልክሎኝ አያዉቅም። በሰዓቱ ፈስቡኬ የሀዘን

ቤት መሰለ። የምፖስታቸዉ ነገሮች ሁሉ ብሶቶች ነበሩ።

ከኢክራም ጋር አንገናኝም፣አንደዋወልም በቃ የግንኙነት

መስመሮቻችን ሁላ ተቋርጠዋል። ስለሷ ማወቅ ስፈልግ

የፈስቡክ አካዉንቷ ላይ የፖስተችዉን እያየሁ ሁኔታዋን

እረዳለሁ።

ሪሀና አንዳንዴ ኢክራም ባል ተብዬዉን ስታገኘዉ አብራ

ስለምትሄድ ደጢላ ያለዉን ሁኔታ ትነግረኝ ነበር።

በሰዓቱ ስብራቴን የሚገልፅልኝ አንድ ግጥም ነበር። "በዝናብ

ቅጠሪኝ" የአንዱአለም ኪዳኔ ግጥም ነዉ።

"አማልዱኝ ባልልም አስታራቂ ልኬ

ባልማፀንሽም ፊትሽ ተንበርክኬ

እንባዬ እንዳይታይ ካንቺ ተደብቄ

አነባለሁ ዛሬም ዝናቡን ጠብቄ

ልቤ በስቃይ ጣር ብሶቱን ሲያሰማ

ሀዘኔ ተሰምቶሽ ልብሽ እንዳይደማ

ቀኑ ጨለልሞልኝ ክረምቱ እስኪገባ

መጥተሽ አጠይቂኝ ሆድሽም አይባባ

.

ዝናብ የኔን ብሶት ሀዘኔን ባያጥበው

ሳለቅስ እንዳታዩ እንባዬን ይጋርደው

በጉንጬ የሚፈሰው ዝናብ እንዲመስልሽ

ሁሌም ክረምት ይሁን ጉዳቴ አይታይሽ

ውዴ:-

ጥፋቴ ሲገባኝ ዛሬ ተመልሼ

ነይልኝ አልልም እፊትሽ አልቅሼ

አዲሱ ኑሮሽን ልረብሽ በ'ንባዬ

በበጋ አልጣራም ናፍቀሽኛል ብዬ

.

ሳለቅስ እንዳታዩኝ

ሁሌ በየአመቱ በክረምት ነይልኝ

ጉርምርምታው ሲብስ በዝናብ ጠይቂኝ

አንቺን ያገኘሁ ለት

ከንፈሬ ተላቆ ስስቅ እንድታይኝ

ቀን የጨለመ ለት

ዶፍ እየወረደ ዝናብ ውስጥ ጠብቂኝ

እስከዛው ግን ውዴ ሰላም ክረሚልኝ።

.

አንዱአለም የኔን ብሶት አይቶ የፃፈዉ ግጥም ነበር የመሰለኝ።

ከአንዱአለም ግጥም ዉስጥ ከኔ ታሪክ ጋር የሚለያየዉ እሱ

ጥፋቱ ሲገባዉ ነዉ ተመልሶ ሀዘን ዉስጥ የገባዉ። እኔ

ሲጀመርም አልተዉኳትም ፣አብረን ሆንን ነዉ ይህ ነገር

የተፈጠረዉ።

ከኢከሩ ጋር እንሄድባቸዉ የነበሩበት ቦታዎች ጋር ሳልፍ ከሷ ጋር

እዛ ቦታ ላይ ያደረግናቸዉ ነገሮች ትዝ እያሉኝ እንባ እንባ

ይለኛል።

.

ከኢከሩ ጋር ከተለያየን ወደ አንድ ወር ገደማ ሆነ። ሰአቱ

የረመዳን ፆም የተጀመረበት ጊዜ ነበር። ሪሀና ደዉላ ልታገኘኝ

እንደምትፈልግ ነገረችኝ። ረመዳን ላይ ከሴት ጋር መቀጣጠር

አልወድም!! ትኩረቴን ሙሉ ለሙሉ አምልኮ ላይ ማድረግ

ያስደስተኝ ነበር። ግን ሪሀና ስለሆነች ለጥቂት ደቂቃ ላገኛት

ተቀጣጠርን። ሪሀና ልትነግረኝ የፈለገችዉ ነገር እንዳለ

ገብቶኛል። ምን እንደሆነ ግን አላወቅኩም። ምናልባት ከብሩኬ

ጋር ተጋጭተዉ ይሆን? ብቻ ግራ ገብቶኛል።

ሪቾ ለምንድነዉ በአካል ልታገኘኝ የፈለገችዉ? ለነገሩ ምን

አስቸኮለኝ ራሷ ትነግረኝ የለ።

.

ይቀጥላል...

h

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስር

(ፉአድ ሙና)

.

.

ሪሀና ስትደዉልልኝ መስጂድ ዉስጥ ነበርኩ። ረመዳን ላይ

መስጂድ ድርሽ ብሎ የማያዉቅ ሰዉ ሳይቀር በረመዳን

መስጂዱን ቤቱ ነዉ የሚያደርገዉ። ወንጀለኛ ልቦች ሁሉ ወደ

ጌታቸዉ ይዋደቃሉ። ቀን ላይ መስጂዱ ቁርዓን በሚቀሩ ሰዎች

ተዉቦ ይዉላል። ምሽቱን በዉብ ድምፃቸዉ ቁርአንን በምሽቱ

የተራዉሂ ሰላት ላይ በሚያሰግዱ ኡስታዞች ይደምቃል። የሁሉም

እጅ ይፈታል። ያለዉ ለተቸገረዉ በጣሙን እጁን የሚዘረጋበት

ወር ነዉ። እኔ እንኳ ረመዳን ባይሆንም ከመስጂድ አልጠፋም።

ዞሬ ዞሬ መመለሻዬ መስጂድ ነዉ።

.

ከመስጂድ ወጥቼ ሪሀና ወደ ቀጠረችኝ ቦታ ሄድኩ። በሪሀና

ተወስዉሼ ፆሜ እንዳይበላሽ አይኔን ሰብሬ ነዉ የማናግራት።

መወሰወስ ስል ሴት ናትና የሚያምር ነገር ይኖራታል። ደግሞም

ቆንጆ ናት እና ዉበቷን አይቼ ልቤ እንዳይንሻፈፍ እየተጠነቀቅኩ

መሆኑ ነዉ። ሴት ሲፈጥራትም ሁሉ ነገሯ ዉብ ነዉ። እኛ ደግሞ

የሴት ልጅን እንኳ መልኳን አይተን በድምጿ ብቻም ልባችን

ይዋልላል። እኛ ወንዶች!!

ሪቾ የተቆጣሁ መስሏት ግራ እየተጋባች "ፊዊ የሆነ ነገር

ልነግርህ ነበር።" አለች

"ሪቾ ፈታ ብለሽ ንገሪኝ ምንድነዉ?"

"ፈዊ እየቀለድንብህ ምናምን ሊመስልህ ይችላል! እኔ ራሱ

ይቅር ብዬ ነበር ግን እሷ ሁሌ አንተን እያሰበች ስታለቅስ

አልቻልኩም።"

"ምንድነዉ ለምን ግልፅ አታደርጊዉም?" አልኳት ግራ እየተጋባሁ

"ፈዊዬ ኢክሩ ልታገባዉ ከነበረዉ ሰዉ ጋር ስላልተስማሙ

ጋብቻዉ ከተሰረዘ ቆይቷል። እና እስከአሁንም ልንነግርህ ነበር

ግን ፈራንህ። ከኢክሩ ጋር እንደድሮዉ ብትመለሱ ምን

ይመስልሀል? እሷ እያለቀሰች አስቸገረችኝ።" አለች

ገረመኝ ኢክሩን ድጋሚ ላገኛት ነዉ? ድጋሚ እነዛን ዉብ

አይኖቿን ላያቸዉ ነዉ? ጆሮዬ የናፈቀዉ ቁምነገር የተሞላ

ንግግሯን ሊያደምጥ? ስለኔ የሚጨነቅ ሌላ ሰዉ ላገኝ ነዉ?

በጣም ነዉ የሚገርመዉ!! በጣም!!

ከኢክሩ ጋር የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ ስንገባ እኔ ጋር ለኢክሩ

የወንድምነት እንጂ የፍቅር ስሜት አልነበረም። ኢክሩን ስለያት

ግን መላመድ ምን ያህል መለያየትን እንደሚያከብድ ተረዳሁ።

"ሪቾ ልልሽ የምችለዉ አንድ ነገር ነዉ። ኢክራምን እወዳታለሁ።

አሁን ብቻ ሳይሆን ከዚህ በኋላም ከህይወቴ ወጥታ ብትመለስ

እቀበላታለሁ።" አልኳት።

ሪቾ ይሁንታዬን በማግኘቷ ፊቷ ፈካ።

.

ሪሀና ለኢክራም ምርጥ ጓደኛ ናት። እኔን ለሷ ስትጠይቀኝ ራሱ

ለጓደኛዋ በጣም ታደላ ነበር።

ሪቾ ለኢክራም ደዉዬ እንድንቀጥል መፍቀዴን እንድነግራት

ጠየቀችኝ። ሪቾ ትቸኩላለች። አሁን ነዉ እንድደዉል የፈለገችዉ።

እኔ ወደ ማታ እንደምደዉልላት ነግሬያት ተለያየን።

ከሪቾ ጋር እንደተለያየን ወደ መስጂድ ሮጥኩ። ጌታዬን በግንባሬ ተደፍቼ አመሰገንኩት። ጌታዬ ምስጋናዬን ይቀበለዉ አይቀበለዉ አላዉቅም። ሲጀመር በእስልምና ሀይማኖት ፍቅረኛ የሚባል ነገር በጣም የተወገዘ ነዉ። እስልምና ወደ ዝሙት የሚወስዱ መንገዶችን ገና ከሩቁ ነዉ የሚዘጋቸዉ። ግን እኔ ስሜቴ አሸንፎኝ ተነከሬበታለሁ። አላማዬ ግን ኢክራምን ማግባት ነዉ። እስከአሁን ዝሙት ዉስጥ አልገባሁም። ከዚህ በኋላ ላለዉም ዋስትና የለኝም። ዝሙት ዉስጥ መግባት ይቅርና ኢክራምን ነክቼያት እንኳ አላዉቅም። በእምነቴ ሌሎች ጎኖች ላይ ጠንካራ ነኝ። እንዱና ዋነኛዉ ክፍተቴ ከኢክራም ጋር የፍቅር ግንኙነት መጀመሬ ነዉ።

.

ሲመሽ ኢክሩ ጋር ደወልኩላት። ኢክሩዬን አናገርኳት። ከአንድ ወር በኋላ ድምጿን ሰማሁ። ጊዜዉ ረመዳን ስለሆነ ፆሙ እስከሚጠናቀቅ በአካል እንደማንገናኝ እና እስከዛዉ በስልክ እንደምንገናኝ ተነጋገርን።

ረመዳን ሊያልቅ አስር ቀናት ቀሩት። እነዚህ የመጨረሻ አስር ቀናት ከረመዳን ሌሎች ቀናት በጣም ከፍ ያለ ክብር አላቸዉ። ከነዚህ አስር ቀናት በአንደኛዉ "ለይለተል ቀድር" የምትባል ለሊት አለች። በነዚህ አስር ቀናት ዉስጥ እንደሆነች እንጂ የትኛዉ ለሊት ላይ እንደምታልፍ አይታወቅም። ስለዚህ ሰው በዚህች ለሊት የሚገኘዉን ታላቅ ምንዳ ለማግኘት የመጨረሻዎቹን አስር ቀናት ከሌሎች የረመዳን ቀናት በተለየ በአምልኮ ተወጥሮ ያሳልፋቸዋል።

በነዚህ የመጨረሻ አስር ቀናት ከኢክሩ ጋር ላለመደዋወል

ተስማምተን ከኢድ በኋላ ለመገናኘት ከወዲሁ ተቀጣጠርን።

.

እነዛ ዉብ የረመዳን ለሊቶች አልቀዉ የኢድ ዕለት ደረሰ።

ከኢክራም ጋር ተደዋዉለን በነጋታዉ ለመገናኘት ተቀጣጠርን።

ከተጣጣን በኋላ ድጋሚ በአካል ተገናኘን። ኢክሩ እንደድሮዉም

እንዳማረባት ናት። ቤቴ ዉስጥ ሚስቴ ሆና ላያት የምመኝላት

ኢኩዬ ደህና ናት።

የሀፍረት ፈገግታ ፈገግ እያለች "ፈዊዬ እራስወዳድ ሆኜ ትቼህ

ስለሄድኩ በጣም ይቅርታ!!" አለችኝ።

አይኗን እየተመለከትኩ "ኢክሩ ከዚህ በፊት ያጠፋሽዉን እና

ከዚህ በኋላም የምታጠፊዉን ቁምር ይቅር ብዬሻለሁ።"

አልኳት። ይሄ ንግግር ከፈጣሪ የተኮረጀ ነበር። አላህ ለነብዩ

ሙሀመድ (ሰ ዐ ወ) ያላቸዉ ነዉ። አላህ ነብዩን ስለወደዳቸዉ

እንዲህ አላቸዉ። እኔ ኢክራምን ስለወደድኳት የፈጣሪን ንግግር

ኮረጅኩላት። ወደፊት የሚፈጠረዉን ሳላዉቅ ይቅር ብዬሻለሁ

ማለቴ አግባብ ይሁን አይሁን አላዉቅም።

.

ከኢክሩ ጋር የፍቅር ግንኙነታችን አዲስ ምዕራፍ ከፈተ። ብሩክን

በድጋሚ ስለመመለሳችን ነግሬዉ ደስ አላለዉም። "ድጋሚ

ማልቀስ ፈለግክ?" ነበር ያለኝ። እሱ ለኔዉ አስቦ ይመስለኛል።

እኔ ደግሞ ለኢክራም የማሰብ በሽታ አለብኝ።

ብሩክ እና ሪሀና በየመሀሉ ቢጋጩም አሁንም እንደከነፉ ናቸዉ።

.

ኢክሩ ቾኮሌት በጣም ዝንደምትወድ ነግሬያችኋለሁ። ሰሞኑን

ስንገናኝ ቸኮሌት ይዤላት መሄድ አዘዉትሬያለሁ።

በዚህ መሀል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ዉጤት ወጣ። አሪፍ

ዉጤት ነበር ያመጣሁት። ረዊና እና ሁዳም ሰቅለዉታል።

ብሩኬም አልፏል። ሄኖክ ግን ዉጤቱ ወርዷል።

አሁን የዩኒቨርሲቲ ዉጤት ተለቅቋል። የምንመደብበትን

ዩኒቨርሲቲ በጉጉት እየጠበቅን ነዉ። እኔ አዲስአበባ እንዲደርሰኝ

ነዉ የምፈልገዉ። ስነ አእምሮ ማጥናት እፈልጋለሁ። የሰዉን

አስተሳሰብ እና ማንነት መረዳት ወትሮዉንም እወዳለሁ። ይሄን

ፍላጎቴን ዩኒቨርሲቲ ገብቼ በትምህርት ማዳበር ይኖርብኛል። ስነ

አእምሮ (Psychology) መማር ህልሜ ነዉ።

.

ኢክሩ ገና ከአሁኑ ስጋት ይዟታል። አንዳንዴ ክፍለሀገር ደርሶኝ

እንዳንለያይ ትሰጋለች። ድጋሚ እንዳታጣኝ ነዉ ስጋቷ! አንዳንዴ

ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ስገባ ከሌላ ሴት ጋር የፍቅር ግንኙነት

የምጀምር እየመሰላት ትፈራለች። እኔ ቆንጆ ሴት በጣም

እወዳለሁ። አልዋሽም!! የኢክራምም ስጋት ዩኒቨርሲቲ ስገባ ሌላ

ሴት አይቼ እንዳልከዳት ነበር። ለኔ ግን ጭንቀቷ መሰረት የለሽ

ነዉ። ኢክራምን በጣም እወዳታለሁ። እኔ ሴት ቀድማ

ካላናገረችኝ እንኳ የማላናግር ልጅ ነኝ። ኢክሩ ስትጠረጥረኝ ደስ

አይለኝም።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የዩኒቨርሲቲ ምደባ መዉጣቱ ተነገረ።

ምሽቱን እኔና ብሩኬ ለማየት ብንሞክርም ኔትዎርኩ ተይዞ

ስለነበር አልቻልንም። ክፍለሀገር እንዳይደርሰኝ በጣም

ፈርቼያለሁ!! በጣም!!

.

ይቀጥላል...

ልብ ወለድ:

ttps://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራ አንድ

(ፉአድ ሙና)

.

.

ለሊት ተኝቼ ስልክ ተደወለልኝ። ስልኬን በእንቅልፍ ልቤ

ለማንሳት ስታገል ወደ ታች ጣልኩት። እንደምንም ስልኬን

ከአልጋ ስር አውጥቼ አነሳሁት። አዩብ ነበር። የሪም ፍቅረኛ!!

እንደዉም የኢክሩን ስልክ እንዳገኝ የረዳችኝ ልጅ!!

አስታወሳችኋት?

"ፈዉዛዬ እንኳን ደስ አለህ!" አለኝ።

"ምንድነዉ?" አልኩት ከእንቅልፌ ለመላቀቅ እየታገልኩ።

"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደርሶሀል!" አለኝ።

በጣም ደስ አለኝ "አንተስ የት ደረሰህ?"

"ባክህ አብረን ነን እኔም እዚሁ ነኝ።" አለኝ። ስለደወለልኝ

አመስግኜዉ ስልኩን ዘጋሁት።

ያዉ አዩብ የሪጅስትሬሽን ቁጥራችንን ያዉቀዉ ስለነበር ነዉ

ያየልን።

.

ኢንተርኔቴን አብርቼ የጓደኞቼን ምድብ ማየት ጀመርኩ።

ብሩኬ አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ደርሶታል። ስለተለያየን በጣም

አዘንኩ። እኔ አዲስ አበባ ስለደረሰኝ ደግሞ በጣም ደስ አለኝ።

ረዊና ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ፣ ሁዳ ደግሞ ጅማ ደርሷቸዋል።

ሁለቱም የመጀመሪያ ምርጫቸዉን ነበር ያገኙት።

ወዲያዉ ፌስቡክ ላይ ገብቼ "አልሀምዱሊላህ" የምትል ምስል

ለጥፌ ወጣሁ። አልሀምዱሊላህ ማለት ለአላህ ምስጋና ይገባዉ

ማለት ነዉ። ደስታዬን ለመግለፅ ነዉ የለጠፍኩት። ነግቶልኝ

ለኢክሩ ደስታዬን እስክነግራት ጨንቆኛል። ግን ትንሽ

ላስጨንቃትም ፈልጌያለሁ።

ኢክሩ ግን ገና ከፌስቡክ ፖስቴ አዲስ አበባ እንደደረሰኝ

ተረድታለች። ወደማታ ስንገናኝ ፈገግ ብላ "የት ደረሰህ?"

አለችኝ በነዛ ዉብ አይኖቿ ፊቴን እየሰለለች። ፊቴን አጨፍግጌ

ክፍለሀገር እንደደረሰኝ ነገርኳት። ሳቋን ለቀቀችዉ። ኢክሩ እኮ

ትሳቅ! የእዉነት ትሳቅ! ስትስቅ በጣም ነዉ የምታምረዉ።

"ምን ያስገለፍጥሻል!" አልኳት ሳቋ እየተጋባብኝ

"ፎግረሀ ሞተሀል!! ባክህ እዚሁ አዲስ ነዉ የደረሰህ!!" አለች

በከሸፈዉ የፋገራ ሙከራዬ እየሳቀች።

.

ሰዓቱ ትንሽ ሀይማኖቴ ላይ የነበረኝ ጠንካራ አቋም እየላላ

ያለበት ነዉ። እስከዚህች ቅፅበት ድረስ እኔና ኢክራም

ተጨባብጠን እንኳ አናዉቅም ብላችሁ ታምናላችሁ? በታ

በእስልምና ሀይማኖት እንድትጨብጣቸዉ የተፈቀዱልህ

የተቆጠሩ ዘመዶችህ አሉ ከነሱ ዉጪ ማንንም መጨበጥ

አይፈቀድልህም። ምክንያቱ ደግሞ የዝሙትን መንገዶች ሁሉ

ከሩቁ ለመጠንቀቅ ነዉ። የእኔና የኢክሩ ግንኙነት ማለትም

ፍቅረኛ መሆን የሚባለዉን ግንኙነት ደግሞ ሀይማኖታችን አበክሮ

ያወግዘዋል። አንዳንድ ሰዎች "ቆይ ፍቅረኛ መሆናችሁም ሀራም

(የተከለከለ) ነዉ ፣ አንጨባበጥም ማለቱ ምን የሚሉት ነዉ?"

ብለዉ ይፎግሩናል።

ግዴታ አንደኛዉን ወንጀል ከሰራህ ሁለተኛዉንም ወንጀል መስራት

አለብህ ብዬ አላምንም። እኔና ኢክሩ የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ

ገባን ጥፋት ነዉ አዉቃለሁ!! ግን አለመጨባበጣችን ወደ ዝሙት

የምትወስደዋን መንገድ ይዘጋል ብዬ አስባለሁ። ሁሉም ነገር

ደረጃ በደረጃ ነዉ እያደገ የሚሄደዉ። ሳልጨብጣት ልስማት

አልችልም።

.

ግን ጊዜዉ እየተራዘመ ሲመጣ ከኢክሩ ጋር መላፋቱ እያማረኝ

ስሜቴ ምክንያታዊነቴን እየተጫነዉ መጣ። የኢክሩን ዉብ

ከንፈሮች መቅሰም አማረኝ። የማንጨባበጥ ሰዎች በአንዴ

ለመሳሳም ለመድረስ ከባድ ስለሆነ ትንሽ የማላመድ ስራዎችን

መስራት ነበረብኝ። እኔ ግን የሚገርመኝ ጭንቅላቴ በአንድ ጊዜ

ዉስጥ ስንት እቅድ እንደሚያቀነባብር!! በእቅዱ መሰረት

የመጀመሪያዉ ስራ መጎሻሸም መጀመር ነበር። በተለምዶ

ሴቶችን ስንነካቸዉ ከጮሁ ድንግል ናቸዉ ምናምን እያልን

የምናረጋግጥበት ቦታ አለ አይደል? በዳሌያቸዉ እና በወገባቸዉ

መካከል ስምንት ቁጥር የሚፈጥረዉ ቦታ ማለት ነዉ። ኢክሩዬ

እሱ ጋር ስትነካ ትጮህለች!! ትጮህለች አይገልፀዉም በቃ

ትሰቃያለች። ደስታም ለቅሶም አይደለም ግን ለየት ያለ ጩኸት!!

እንድትነኳት አትፈልግም። አብረን የምንቀመጥበት ቦታ ላይ

ስንሆን እሱጋር እየነካኳት ምናምን መላፋት ጀመርን። መላፋቱ

ሲያድግ ወደ መኮራኮር አደገ።

ደረጃዉን ወደ ላይ ከፍ አደረግነዉ ማለት ነዉ እንግዲህ!!

ኢክሩዬን እንባዋ እስኪፈስ ነበር የምኮረኩራት። ሳቅ ፣ እንባ እና

ትንፋሿ አሁንም ድረስ ትዝ ይለኛል። በጣም ከምወዳቸዉ

ሽታዎች መካከል የኢክሩን የላብ ጠረን የሚደርስ የለም።

ምናልባት በፀሀይ ዎክ አድርገን አሊያም ከትምህርት ቤት

ደክሟት እኔ ጋር ስትመጣ የሚሸተዉ የሰዉነት ጠረኗ ወደር

የለዉም። ሽቶ አይደለም!! ትክክለኛ የተፈጥሮ የላብ ጠረኗ በጣም ደስ ይለኝ ነበር!! በጣም ነበር የምወደዉ። ስወድ እወዳለሁ! የኢኩዬ ሲሆን ምንም እወዳለሁ!! እስከአሁንም ሳስባት ጠረኑ ያዉደኛል። ሁሌም ጠረኗ ሚስቴ ሆና በእቅፌ ተኝታ ሳሸተዉ በኖርኩ እል ነበር። ደስታ ይሰጠኝ ነበር። እናም ወገቧን ከመንካት ወደመኮራኮር ዙሩ ከዥል። ኢኩዬን መኮርኮር!! ሰዉ እንዴት አንድን ሰዉ ኮርኩሮ እንደዚህ ደስ ይለዋል? ከጀርባችን እያረካነዉ ያለዉ ፆታዊ ፍላጎታችን ስላለ ነዉ እንዲህ ደስ የሚለን። ይህን ድርጊት ለጥቂት ጊዜ ደጋገምነዉ። ጉልበቴ ላይ አድርጌ ስኮረኩራት ቀልቧ እስከሚጠፋ ድረስ እየሳቀች እንባዋ ሲፈስ አስታዉሳለሁ። የኔ ቆንጆ!! ለቅሶሽም ሳቅሽም የተዋበ!!

አሁን መጎሻሸሙም መኮራኮሩም መንገዱን ይዟል። አሁን ቀጣዩ እቅድ መሳሳም የሚለዉ ነዉ!! ኢክሩዬን መሳም የታፈነዉን ስሜቷን ማዳመጥ!! የታፈነዉን ሰዋዊ ስሜቴን ማስተናገድ!! የፈጣሪን ህግ መናድ!!

.

ሴት ልጅ አይነአፋር ናት ብትፈልግም አትናገርም ምናምን ሲባል ስለሰማሁ ፊልጋ በፍርሀት ታፍና ከምትሞት እኔ ራሴ ልስማት ወሰንኩ። ግን በጣም ይከብድ ነበር ሊያዉም ከኔ ኩራት ጋር ተደምሮ አስቡት!! ግን መሆን እንዳለበት ስለወሰንኩ እኔንም እሷንም ጀማሪ በማያስብል መልኩ የምንሳሳምበትን እቅድ አወጣሁ። አሁን ሰዉ ለመሳሳም እቅድ ያወጣል? ፎርማል ነገር ነኝ አላልኳችሁም ነበር? አሁን እቅዱ ተነድፎ ወደ ትግበራ ለመግባት በቀጣይ የምንገናኝበትን ጊዜ እየጠበቅኩ ነዉ። እምቢ ብትለኝስ? መዋረድ አልፈልግም። ለዛ ነዉ እቅዱን እኔን ጀማሪ

በማያስመስል መልኩ የነደፍኩት። አሁን የትግበራ ሰአት

ደርሷል።

.

ሁሌም ባይሆንም በአብዛኛዉ ኢክሩ ጋር ስሄድ ቸኮሌት ይዤ ነዉ

የምሄደዉ። ኢክሩ ቸኮሌት ነብሷ ነዉ። እና የእኔም እቅድ እንደ

ነብሷ በምትወደዉ ቸኮሌት ነብሷን መዉሰድ ነዉ። ሌላ ጊዜ

ቾኮሌት ስወስድላት በእጇ ነበር የምሰጣት አሁን ግን በእጇ

እየሰበርኩ ላንርሳት እና መጨረሻ ላይ በአፌ ይዤ እንድትጎርስ

መጠየቅ ነዉ። ቸኮሌቱን ለመጉረስ ከንፈሬ ጋር ስትደርስ

ቾኮሌቱን ወደ አፌ አከተዋለሁ። ከንፈሯ ቸኮሌቱን ስቶ ከንፈሬ

ላይ ያርፋል። እንግዲህ እቅዱ ይሄ ነዉ። ሚሽኑን Chocolet

kiss ብየዋለሁ።(በቤትም ሆነ በስራ ቦታ እንዳይሞክሩት)

ኢኩፌን ለመሳም እቅድ ተነድፏል አሁን ለትግበራ

የምንገናኝበትን ሰዓት በጉጉት እየጠበቅኩ ነዉ።

.

ይቀጥላል ...

ልብ ወለድ

ማንበብ ሙሉ ሰው ያረጋል.....

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራሁለት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ከኢክሩ ጋር ተገናኝተን ሰሞኑን ወደምንሄድበት ቄር ያለ ቦታ

ሄድን። ቦታዉ ደስ ይላል። ሰዉ አይበዛበትም ነፃነት ነገር

ይሰጣል። ቾኮሌት ይዣለሁ። ሊያዉም ሁለት ቾኮሌት ነዋ!!

በአንዱ ቢከሽፍ በአንዱ እቅዱን ላሳካ ታጥቄያለሁ።

ከኢክሩ ጋር ትንሽ ካወራን በኋላ ሰሞኑን የጀመርነዉን መጎሻሸም

ጀመርን። ወገቧን ስነካት ስትለምነኝ ምናምን!! ስነካት ፣

ስትጮህ ፤ ስኮረኩራት "ፈዊዬ በአላህ!!" እያለች እየሳቀች

ስታለቅስ፤ በቃ ምንልበላችሁ ሙዱ ውስጥ ገባን።

አሁን ቾኮሌቱን ከኪሴ ዉስጥ አወጣሁና በእቅዴ መሰረት በእጄ

እየሰበርኩ አጎረስኳት። ቾኮሌቱ አልቆ ትንሽ ሲቀር በጥርሴ ይዤ

እንድትጎርስ ጠየቅኳት። ኢኩ አየችኝ እና ፈገግ አለች። አላማዉ

በደንብ ገብቷታል። "ቾኮሌቱን ልበላ ስል ነዉ የሳመኝ"

የምትልበትን ምክንያት ስላመቻቸሁላት ደስ ሳይላት አይቀርም።

አንዳንዴ ነገሮችን ማድረግ እየፈለግን ይሉኝታን ስንፈራ ነገሮችን

ለማድረግ የሚገፋን ምክንያት እንፈልጋለን። ከራሳችን ላይ

ሀላፊነቱን ለመግፋት እንሞክራለን። እኔም ኢኩዬ በቾኮሌቱ

ምክንያት ስትስመኝ አጋጣሚ እንጂ እኔ አስቤዉ አይደለም

ለማለት ነዉ እቅድ ያዘጋጀሁት። እሷም ሳምኩት ላለማለት ቆንጆ

ምክንያት ታገኛለች ማለት ነዉ። ግን ይሄ ከሰዉ ይሉኝታ እንጂ

ከፈጣሪ አያስጥልም።

.

ወደ አፌ ቀረብ ስትል ቾኮሌቱን ትንሽ ወደ ዉስጥ ሳብ

አደረግኩት። ትንሽ ቀረብ ብላ ከከንፈሬ የራቀዉን በላችዉ።

እየበላች ወደ ከንፈሬ ስትደርስ አቆመች።

ፈገግ ብላ "እሱን በእጄ ስጠኝ!!" አለችኝ። እቅዱ ተሳካ ስል

ልታበላሸዉ ነዉ ብዬ ተናደድኩ። ግን አሁንም ጭንቅላቴን

አሰራሁት። ቾኮሌቱን ትንሽ ወደ ዉጪ ገፍቼ እንድትበላ ነገርኳት።

መብላት ጀመረች አሁን ቸኮሌቱን እየበላች በከፊል ከንፈሮቻችን

እየተነካካኩ ነዉ። አሁንም ትንሽ በልታ አቆመች እና አየችኝ "ብዩ

እንጂ!!" አልኳት። "ኧረ ልትስመኝ ነዉ አይደል?" አለችኝ።

መግደርደር መጀመሩ ነዉ እንግዲህ!

"እስከአሁንስ ከንፈሮቻችን አልተነካኩም እንዴ? ባክሽ ብዩ!"

አልኳት እየሳቅኩ ሀፍረቴን ለመደበቅ እየሞከርኩ።

ወደ ከንፈሬ ተጠግታ ቾኮሌቱን መብላት ጀመረች። ቸኮሌቱ

ሲያልቅ ከከንፈሯ ጋር ተገናኘን። ነዘረኝ!!! ከንፈር ስስም

ለመጀመሪያ ጊዜዬ ነዉ። እሷም የመጀመሪያዋ ይመስለኛል።

ኢክሩ አይኖቿ ተዘጉ ሰዉነቷን ከንዶቼ ላይ ጣለችዉ። ኢክሩን

አንገቷን ደግፌ ከንፈሯ ዉስጥ ጠፋሁ። እየሳምኳት አያታለሁ።

ደስ ትላለች። እምነቷን እኔ ላይ ጥላ፣ አይኖቿን ጨፍና ፣ሰዉነቷን

ከንዶቼ ላይ አደላድላ ሌላ አለም ዉስጥ ገብታለች።

"ከንፈር መሳም የረጠበ ስፖንጅ እንደመምጠጥ ነዉ።" ብሎ

ኡስማን የነገረኝ ትዝ አለኝ። እዉነቱን ነዉ።

.

ስሜታችን ሲግል መሳሳሙ መላላስ ሆነ። ከንፈሮቻችንን ዘለን

ምላሳችንን መመጣጠጥ ጀመርን። በስሜት አበድን!

ለረዥም ሰዓት ከተሳሳምን በኋላ ሁለታችንም በቃን እና

አቆምን። ካለንበት ስሜት ለመዉጣት ትንሽ ቁጭ ብለን

ራሳችንን አረጋጋን።

ተነስተን ከነበርንበት ቦታ መዉጣት እንደጀመርን ኢክሩ እየሳቀች

"አሁን አንተ አሚራቸዉ ነህ?" አለችኝ። በሰዓቱ አንድ አቋቁመነዉ

የነበረ ሀይማኖታዊ ህብረት አሚር(ሰብሳቢ) ነበርኩ።

ይሄን የሚያክል ህብረት ላይ እየተሳተፍኩ ከንፈሯ ስር ስሜት

ትንፋሼን ሲቆራርጠዉ ስታይ ቀለልኩባት። እንኳን እኛ ንጉሶቹም

ለሚስቶቻቸዉ ቀልለዋል ብዬ አለፍኩት።

ኢክሩን ቀረብ ብዬ ሳያት ከንፈሯ አብጧል። ይህቺ ልጅ እዉነትም የመጀመሪያዋ ነዉ። እንዴት የእኔ ከንፈር አላበጠም? ጉንጭ መሳም አበዛ ስለነበር ይሆናል።(ሀሀሀ)

በጣም የሚገርማችሁ ነገር አሁን ከተሳሳምን በኋላ እንኳ ሸኝቼያት ስንለያይ አልተጨባበጥንም ፣ አልተቃቀፍንም። በቃ ለምዶብናል መጨባበጡ ግዙፍ ወንጀል ሆኗል። መሳሳሙ ያን ያህል አላስጨነቀንም። አሁን ላይ ሳስበዉ ያስቀኛል። አንዳንድ ሰዎችን ካስተዋላችሁ ዉዱዕ አለኝ አልጨብጥሽም ባይሆን ጉንጩን ሳሚኝ ይላሉ እጃቸዉን ወደ ኋላ አጣምረዉ። ፊቴን አልታጠብም ባይሆን ዋና ልዋኝ እንደማለት ነዉ።

.

ለማንም ከኢክሩ ጋር ያደረግኩትን ነገር አልተናገርኩም።

ኢክሩዬን አከብራታለሁ። ማንም ስለሷ አንስቶ እንደሌላዉ ሴት እንዲዘበዝብ አልፈቅድም። እኔ ስለማከብራት ጓደኞቼ ዘንድም የተከበረች ነበረች። ሁለተኛዉ ምክንያቴ ደግሞ መሳሳማችን ሃጢያት ከመሆኑ ጋር አላህን ከወንጀሉ በላይ ወንጀሉ መወራቱ ስለሚያስቀጣዉ ነዉ።

በነጋታዉ ደዉዬ ስጠይቃት አሁንም የከንፈሯ እብጠት እንዳልጠፋ ነገረችኝ። ገርሞኛል።

በነጋታዉ ተገናኝን ከትምህርት ቤት በቀጥታ ነበር ወደምንገናኝበት ቦታ የመጣችዉ። ምናልባት የትናንቱን ትዕይንት እንደምንደግመዉ ሳታስብ አትቀርም። እኔ ግን ኢክሩዬን ለስሜቴ እንደምፈልጋት ብቻ እንድታስብ ስላልፈለግኩ እንኳን መሳሳም መጎሻሸሙንም ተዉኩት። ያመጣሁላትን ቾኮሌት በእጇ ሰጠኋት። እስኪበቃን አወርተን ተለያየን።

.

በሶስተኛዉ ቀን ስንገናኝ ልስማት ሞከርኩ። ኢክሩ እንዲቀርብን

ጠየቀችኝ። በጣም ተሰማኝ። ኢክሩን የማትፈልገዉ ነገር ዉስጥ

እንደዘፈቅኳት አሰብኩ። ኢክሩን ስለምትወደኝ ከሀይማኖታ

ህግጋት ጋር እያጋጨኋት እንደሆነ ነበር የማስበዉ። ፊቴ

ሲቀያየር ኢክሩ ፀፀቴ አመማት። ለማለት የፈለገችዉ እንደዛ

እንዳልሆነ እንድረዳት "ሁሌ ጥፋቶችን ወደራስህ ማስጠጋት

ትወዳለህ።" አለችና አንገቴን ስባ ከንፈሬ ላይ ተለጠፈች።

ቀለጥን። ሳናስበዉ በጣም ለረዥም ሰዓት ተሳሳምን።

.

ረሂማ ልታሞቀዉ ወስዳዉ የነበረዉን ወተት ይዛልኝ መጣች።

"በጣም ቆየሁ ይቅርታ ሳፊዉ!!" አለችኝ።

ከሀሳቤ ለመዉጣት እየታገልኩ "ችግር የለዉም ኮካዬ!" አልኳት።

ወተቱን ረስቼዉ ነበር። አሁን ቅድም ካፈዉ ዉስጥ ከፊት ለፊቴ

ተቀምጠዉ የነበሩት ጥንዶች የሉም። ሌሎች ጥንዶች ቦታዉ ላይ

ተተክተዋል። አዲሶቹን ጥንዶች እያየሁ ወደ ሀሳቤ ባህር

ተመለስኩ።

.

ከኢክሩ ጋር ግንኙነታችን በዚህ መልኩ እየቀጠለ ባለበት ሰዓት

ዩኒቨርሲቲ ተጠራሁ።

እዚሁ አዲስ አበባ ስለደረሰኝ ብዙም ከኢክሩ ጋር ክፍተት

አልፈጠርንም። እንደሁሌዉ እንገናኛለን።

ብሩኬ ወደ ካምፖስ ሄደ። በነገራችን ላይ ሄኖክ የግል ኮሌጅ

አካዉንቲንግ ተመዝግቧል። ብሩክ አርባምንጭ ከሄደ በኋላ

ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ እደዉልለታለሁ። እሱ ግን ሳይረሳኝ

አይቀርም። ሁለ ነገሩ ተቀያይሯል። ከጥሩ ልጆች ጋር

አልገጠመም። የካምፓስ ላይፍ የሚባሉት እንደ ክለብ መዉጣት

መቃም ምናምን አታለዉታል። ብሩክ እምቢ የማለት አቅም

የለዉም። ከሰዉ ጋር ተመሳስሎ ነዉ የሚኖረዉ።

እኔ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አብረን ከተመደብን የሸገር ልጆች

ጋር ጊዜዬን አሳልፋለሁ። ከክፍለሀገር ልጆች ጋር ግን በፍፁም

መግባባት አልቻልኩም። ብዙዎቹ እንደጠላት ነዉ የሚያዩኝ። ግን

ብዙም ግድ አልሰጠኝም። ኢክሩ አሁን የመሰናዶ ተማሪ

ሆናለች። ኢክራምን በትምህርት ደረጃ ልብለጣት እንጂ

እድሜያችን እኩል ነዉ ማለት ይቻላል። በወራት ነዉ

የምበልጣት!!

.

ዩኒቨርሲቲን ተላምደነዉ እኔም ስነ አእምሮ(Psycology)

ደርሶኝ በፍቅር እየተማርኩት ትንሽ እንደቆየሁ ብሩኬ ወደ ሸገር

ተመለሰ። ሀገሩ አልተስማማችም አልቀጥልም አለ። እኔ የእዉነት

ደስ አለኝ። በጣም ናፍቆኝ ነበር። እዚሁ ቆይቶ ቀጣይ ዓመት

የግል ኮሌጅ ለመማር ነዉ ያሰበዉ። ከሪሀና ጋርም በአካል

ለመገናኘት በቁ!! ግን በመካከላቸዉ ትንሽ ክፍተት ተፈጥሯል።

ከአርባምንጭ ከተመለሰ በኋላ ብሩክ በፍፁም የማዉቀዉ ብሩክ

ሊሆንልኝ አልቻለም። ፀባዩ ተቀያይሯል። ለሱ እርድና ማለት

ክለብ መዉጣት እና ሴት ማዉጣት ሆ

ኗል። በተግባር

አያደርገዉም በምላሱ ግን ሁሌም የሚያወራዉ እሱኑ ነዉ።

እኔ የኢክራምን እና የእኔን ግንኙነት በተመለከተ ትልቅ ዉሳኔ

ለመወሰን እያዉጠነጠንኩ ነዉ።

.

ይቀጥላል...

ልብ ወለድ

ማንበብ ሙሉ ሰው ያረጋል.....

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራሶስት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ካምፓስ ገብቼ ሁለተኛዉ የትምህርት ዘመን አጋማሽ ተጀምሯል።

ብሩኬ ጊዜዉን ፊልም በማየት ያሳልፋል። እኔ የላላዉን

ሀይማኖቴ ላይ የነበረኝን አቋም ለማስተካከል እየሞከርኩ ነዉ።

ከኢክሩ ጋር ከሁለቱ ቀናት በኋላ ድጋሚ ተሳስመን አናዉቅም።

አንነካካም!! እናወራለን!! ስለ ጋብቻ እናልምና እንለያያለን!!

አለቀ።

ቀኑ ሀሙስ ነበር። ከ 6 ኪሎ ካምፓስ ታክሲ ይዤ ወደ ፒያሳ

ሄድኩ። ወደ መስጂደ ኑር!! ይሄ መስጂድ በተለምዶ በኒ

መስጂድ ይባላል። መስጂዱ ዉስጥ ገብቼ ከመድረኩ

የሚሰጠዉን ትምህርት መከታተል ጀመርኩ። የመስጂዱ ግርማ

ሞገስ የሆኑት ሸህ ኡመር ኢድሪስ የቁርዓንን ትርጉም

ይተነትናሉ። ከቁርዓኑ እየተተነተነ የነበረዉ አንቀፅ የዩሱፍ(የሴፍ)

ምዕራፍ ነበር። ይህ ምዕራፍ የዩሱፍን ታሪክ በሰፊዉ ይተርካል።

ዩሱፍ በወንድሞቹ የዉሀ ጉድጓድ ዉስጥ ከተጣለ በኋላ

ነጋዴዎች አግኝተዉት ለአንድ የምስር(ግብፅ) ባለስልጣን

ይሸጡታል። ይህ የገዛዉም ሰዉ ዩሱፍን ለሚስቱ በስጦታ መልክ

ያበረክትላታል። ዩሱፍ በጣም ቆንጆ ከመሆኑ የተነሳ የባለስልጣኑ

ሚስት ለነፍሷ ትመኝዋለች። ከዚህ ዉብ ፍጥረት ጋር አለሚን

መቅጨት ያምራታል። ዩሱፍንም በሮቿን ሁሉ ዘጋግታ ለሱ

እንደተዘጋጀችለት እና አብሯት የስጋ ጥሙን እንዲያረካ

ትጋብዘዋለች። ዩሱፍ ግን ጥሪዉን ገፍቶ አልቀበልም ይላል።

የባለስልጣኑ ሚስት እልህ ግን ዩሱፍን ከእርሷ ጋር ከመተኛት

አሊያም ከመታሰር የሚያስመርጥበት ደረጃ ላይ ይደርሳል።

.

ሽይኹም(መምህሩም) ትኩረት ሰጥተዉ እየተነተኑት ያለዉ ቦታ

ይሄ ነዉ። ዩሱፍ ከመታሰር እና ጌታዉን ከማመፅ ምርጫ

ሲቀርብለት የተናገረዉን ንግግር ሽይኹ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ

"ዩሱፍ ሴቲቱ የዚህ አይነት አጣብቂኝ ዉስጥ ስትከታቸዉ

እንዲህ ብለዉ ጌታቸዉን ለመኑ 'ጌታዬ ሆይ በርሱ ከሚጠሩኝ

ነገር (ከዝሙት) ይልቅ መታሰር ለኔ የተወደደ ነዉ።

ተንኮላቸዉንም ከኔ ላይ ባትመልስልኝ ወደነሱ እዘነበላለሁ ፣

ከስህተተኞችም እሆናለሁ።' አለ። አላህም ፀሎቱን ተቀበለዉና

ታሰረ።"

ከዚህ በላይ ማዳመጡ ከበደኝ ከኢክራም ጋር ያሳለፍኳቸዉ

ሁለቱ ቀናት ትዝ አሉኝ።በጋብቻ ያልተሳሰርኳትን ኢክራምን ከንፈር

የሳምኩባቸዉ ፣ የተከለከልኩትን የአካሏን ክፍሎች የነካሁባቸዉ

ሁለት ቀናት!!

እኔ ጌታዬን ለማመፅ እቅድ አዉጥቼ ተገበርኩ። ዩሱፍ ግን

ማንም ሰዉ በሌለበት ሊያዉም ከባለስልጣን ሚስት የደረሰዉን

የእንተኛ ጥያቄ ገፋዉ ፤ ጌታዉንም ላለማመፅ ሲል ታሰረ።

ዛሬ ሁሉም ነገር ግልፅ ሆኖ ይታየኝ ጀመር። እኔ አሁን ገና

የካምፓስ ተማሪ ነኝ። ኢክራምን ለማግባት የቁስም ሆነ የስነ

ልቦና ዝግጅቱ የለኝም። የኢክራምን ዉድ የወጣትነት እድሜ

እያባከንኩባት ነዉ፤ ጌታዬንም እያስቆጣሁት ነዉ። መጃጃሉ

ይበቃል! ከኢክሩ ጋር እዉነቷን ተነጋግሮ መለያየት ይሻላል!! ግን

የዛን ቀን ለራሴ አንድ ቃል ገባሁ። እኔ የስነ ልቦናም ሆነ የቁስ

ዝግጅቴ ለጋብቻ ብቁ ሲሆን የፈለጉ አመታት ቢነጉዱ እንኳ

ኢክራምን ፈልጌ ካላገባች እሷኑ ላገባ። አዎ በፍቅር

የሰከርኩላትን ፣ ከማንም በላይ የማዘንላትን ኢኩፌን

ለማግባት!!

.

ከስድስት ኪሎ ወደ ፒያሳ ተሳፍሬ ሄጄ የሰማሁት ነገር አቋሜን

ለዉጦት ወደ ስድስት ኪሎ ተመለስኩ።

አሁን ለኢክራም እንዴት ማስረዳት እንደምችል አሰብኩ።

መጀመሪያ እኔ ከሷ ጋር ግንኙነቴን ለማቆም ምክንያት የሆኑኝን

ሁለት ነገሮችን አሰብኩ። ጌታዬን እያስቆጣሁ መሆኑና ኢክሩ

ከእኔ ጋር በመሆኗ ምክንያት አለማግባቷ ናቸዉ። ከኔ ጋር ፍቅር

የሚሉትን እቃቃ ባትጀምር ኖሮ የማግባት እድሏ ሰፊ ነበር። የሷ

ማግባት ደግሞ ለቤተሰቦቿም ጥቅም አለዉ።

ኢክራምን በምክንያት ለማስረዳት ከሞከርኩ እኔዉ ራሴ ከዚህ

በፊት ባስጠናኋት የቃላት ድርደራዎች ልትረታኝ ትችላለች።

ስለዚህ አዲስ ስልት መጠቀም ነበረብኝ። ኢክራምን

እንድትጠላኝ ቢያደርጋትም እንኳ ግንኙነታችንን ለማቋረጥ

እንደሚረዳ አሰብኩ። አዎን ዉጤታማ መንገድ አቀድኩ!!

ለበጎዉም ለመጥፎዉም የማቀድ በሽታ አለብኝ።

.

ኢክሩ ፌስቡክ ላይ ስትፅፍልኝም እንደድሮዉ ትኩረት ሰጥቼ

አላወራት አልኩ። የሳምንቱ የትምህርት የመጨረሻ ቀን ጁምዓ

(አርብ) ሲደርስ ከስድስት ኪሎ ዶርም ወደ ሰፈር ተመለስኩ።

በነገራችን ላይ ከዶርም ወደ ቤት የምመለስበት ዋነኛዉ

ምክንያት ቤተሰቦቼ ናፍቀዉኝ ሳይሆን ኢክራምን ለማግኘት

ነበር። እሷ ሰሞኑን ብዙም በስልክም ስላልተገናኘን ናፍቂያት

ነበር። ደዉላ የምንገናኝበትን ሰዓት ጠየቀችኝ ፤ነገርኳት። አሁን

ልቤ ለአንድ አመት ያክል አብሬያት የነበረችዉን ልጅ ይብቃን

ለማለት ያለዉን ጥንካሬ ሁሉ እየሰበሰበ ነዉ። በቃ ከእዉነታዉ

ጋር መጋፈጥ አለብኝ!!

.

ሰዓቱ ሲደርስ ከኢክሩ ጋር ወደኛ ሰፈር የሚያስገባዉ መንገድ

ጋር ተገናኘን። ኢክሩ ዛሬ ጅልባብ ለብሳ ነዉ የመጣችዉ።

ጅልባብ ማለት ሙስሊም ሴቶች የሚለብሱት ፊትንና እጅን ብቻ

የሚያሳይ ልብስ ነዉ። የሰዉነታቸዉን ቅርፅ በፍፁም አያሳይም።

ሰፊ ነዉ። ኢክሩን በጅልባብ ሳያት ደስ አለኝ። በጅልባብ ደግሞ

በጣም ነዉ የምታምረዉ። ይሄ ፈገግታ ፣ ይሄ ዉበት ላይ ነዉ

ጨክኜ ፣ ከፈገግታዋናዉበቷ ዘላቂ ደስታዋን እና የጌታዬን ክብር

መርጬ በቃን ልላት የወሰንኩት።

ልክ አጠገቤ እንደደረሰች እንደተለመደዉ ከአጠገቤ ቆማ

"አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላህ" አለችኝ። የአላህ ሰላምና

እዝነት ባንተ ላይ ይሁን ማለት ነዉ።

"ወአለይኩሙሰላም ወራህመቱላህ" አልኳት።

ባንቺም ላይ የአላህ ሰላም እና እዝነት ይሁን ማለት ነዉ።

.

ሰላም ተባብለን ከጨረስን በኋላ ወዲያዉ እዛዉ እንደቆምን

ወደገደለዉ ለመግባት ፈለግኩ።

ፊቴን አጨፈገግኩ እና ትንፋሼን ዉጬ "ኢክሩዬ ለረዥም ጊዜ

አብረን ቆይተናል ግን ግንኙነታችን ወዳልሆነ መስመር እየወሰደን ነዉ። ባለፈዉ ያደረግነዉን ታስታዉሻለሽ አይደል?(መሳሳሙን ማለቴ ነበር) በዚህ ከቀጠልን ሌሎች ነገሮች ላይም ልንወድቅ እንችላለን። ስለዚህ ከዚህ በኋላ ለዝሙት ካልሆነ በቀር ወደ እኔ አትምጪ!!" አልኳት።

ኢክሩ ፊቷ ተቀያየረ ፣ አይኗ በእንባ ተሞላ ፣ ወዲያዉ በዉሸት ፈገግታዋ እንባዋን ለማጨንገፍ ሞከረች።

"ኢክሩ መናገር የምትፈልጊዉ ነገር አለ?" አልኳት። ልቤ በጣም ይመታል።

ትንሽ አየችኝና በአሉታ አንገቷን ነቀነቀችልኝ። በቀመችበት ትቻት ሄድኩ!!

ንግግሬ በራሴ ጆሮ ላይ እየደጋገመ ያስተጋባል። "ለዝሙት ካልሆነ በቀር ወደ እኔ አትምጪ" የኢክራምን እኔን ለመመለስ የሚያስችሉ ሙከራዎች ሁሉ ለመክሸፍ የተጠቀምኳት ቃል ነበረች።

.

እኔ ከኢክራም ጋር ስለያይ ምንም እንኳ ከዚህ በፊት አብረን የነበርን እንደመሆናችን መልካም የሆነ ወንድማዊ ግንኙነት እንዲኖረን እናድርግ ማለቴ እንጂ በደረስኩበት አትድረሺ ማለቴ አልነበረም።

ኢክሩ ዉሳኔዬን ማክበሯን ፌስቡክ ላይ አንፍሬንድ ከማድረግ ጀመረችዉ።

መንገድ ላይ ስታገኘኝ ባላየ ማለፍ ወይም ለሰላምታ ከብሩክ ጋር ስሆን ብሩክን ብቻ ጠርታ ሰላም ማለት ጀመረች።

ነገሩ ምንም አልጥምህ ስላለኝ አግኝቼ ላናግራት ወሰንኩ።

ኢክሩ በጣም ልቧ ተሰብሯል ፤ አዝናብኛለች።

ልትረዳዉ ያልቻለችዉ ትልቅ ሀቅ አለ። እኔ ዛሬ ማንንም አይቼ

አይደለም ይብቃን ያልኳት። ግን እዉነቱን መቀበል ነበረብን።

እዉነቱ ደግሞ ድርጊታችን ጌታችንን የሚያስቆጣ ከመሆኑም ጋር

የኢክሩን እምቡጥ እድሜ የሚያባክን ነበር። ግን ከማንም በላይ

የምወዳት ሴት እሷ ነበረች።

.

ኢክራምን አግኝቼ በመካከላችን ያለዉ ግንኙነት የጠላት

እየመሰለ እንደሆነ እና እንድናስተካክለዉ ነገርኳት።

ኢክሩ በሂደት በመካከላችን ያለዉ ግ

ንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን

የበኩሏን አደረገች።

ሀሙስ ቀን ላይ ኢክሩ ስልክ ደወለችልኝ።

"ወዬ ኢክሩ" አልኳት መደወሏ ገርሞኝ

"ፈዊ ላገኝህ እፈልጋለሁ የማማክርህ ጉዳይ አለኝ።" አለችኝ።

በሰዓቱ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ነበርኩ። ከፈለግኩ መምጣት

እንደምትችል ነገረችኝ።

በጣም ግራ ስለተጋባሁ ወደ ሰፈር ስመለስ ለመገናኘት

ተቀጣጠርን።

ከራሴ ጋር ከባድ ትግል ዉስጥ ነኝ። ኢክሩ ለምን ፈለገችኝ?

ግራ ያጋባል።

.

ይቀጥላል...

ልብ ወለድ

ማንበብ ሙሉ ሰው ያረጋል.....

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራአራት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ወደ ሰፈር ከመመለሴ በፊት አንድ የማላዉቀዉ ስልክ

ተደወለልኝ።

"አቤት!!" አልኩ ስልኩን አንስቼ!! አንዲት ሴት እንደ ሙዚቃ

በሚሰረቀረቅ ዉብ ድምፅ "ፈዉዛን ነህ አይደል?" አለችኝ።

ድምፁ አዲስ ስለሆነብኝ ግራ እየተጋባሁ "አዎ ነኝ ምን

ልታዘዝ?" አልኩ።

ልጅቷ ኢክራም የምትመራዉ ሀይማኖታዊ ማህበር ዉስጥ የስነ

ፅሁፍ ዘርፍ ላይ እንደምትሰራ እና መፅሔት ለማዘጋጀት

እየሞከሩ ስለሆነ እንዳግዛቸዉ ዘፈነችልኝ። (የልጅቷ ድምፅ

ከመስረቅረቁ የተነሳ ተናገረች ማለት ስለሚከብደኝ ነዉ

ዘፈነችልኝ ያልኩት)

እኔም ወደ ሰፈር ስመለስ ላገኛቸዉ ለጁምዓ(አርብ)

ተቀጣጠርን።

.

ጁምዓ(አርብ) ዕለት ከደወለችልኝ ልጅ ጋር ሰፈር መስጂድ

ዉስጥ በመካከላችን መጋረጃ ተጋርዶ በአካል አወራን።

አልተያየንም!! አብረዋት ሁለት ልጆች ነበሩ። ወንድና ሴት

ዉይይት ሲያስፈልግ ሁሌም እንዲህ ነዉ የሚደረገዉ መጋረጃ

ተጋርዶ እንወያያለን። ይሄ የሚደረገዉ ሀራም(ክልክል) ዖታዊ

መፈላለጎችን ለመታደግ ነዉ።

ልጅቷ ስሟ ሱመያ ነዉ። ድምጿ በጣም ያምራል። በምችለዉ

ሁሉ ላግዛት እና ስለሰራዉ በስልክ እየተደዋወልን ለመነጋገር

ተስማምተን ተለያየን።

ሱመያ ገና ከዛዉ ቀን ጀምሮ ፌስቡክ ላይ ስለብዙ ነገሮች

ታማክረኝ ጀመር። ምናለ ታይፕ ተደርገዉ የተላኩ ሚሴጆችን

በፀሀፊዉ ድምፅ የሚያነብ ማሽን በኖረ!! የሱመያን መልዕክቶች

በሷ ድምፅ እሰማበት ነበር። የፈጣሪ ያለህ የሰዉ ድምፅ እንዲህ

ይስረቀረቃል? የሷ በጣም ይለያል።

.

በነጋታዉ ቅዳሜ ኢክሩ ደዉሎ የምንገናኝበትን ሰዓት ተነጋገርን።

ሰዓቱ ሲደርስ መንገድ ላይ ተገናኝተን ወደዚህ ካፌ መጣን።

ኢክሩ ጥቁር ሰማያዊ ጅልባብ ለብሳለች። ረሂማ መጥታ

ከታዘዘችን በኋላ ኢክሩ አይኔን ትኩር ብላ እያየችኝ "ፈዉዛኔ ግን

ምንም የአቋም ፅናት የለህም።" አለችኝ። እዉነቷን ነዉ አንድ

ነገር ላይ ለረዥም ጊዜ በፅናት መቆም ይከብደኛል። አሁንም

ከሷ ጋር በፍቅር ግንኙነት ዉስጥ ለመቆየት ከጌታዬ ጋር

የምጋፋበት ፅናት አጥቻለሁ።

እየሳቅኩ "ኢክሩ ልክ ነሽ" አልኳት።

አሁን ከኢክራም እየተረዳሁ ያለሁት ግን ከዚህ ቀደም

በመካከላችን ያለዉን ግንኙነት የጠላት አናስመስለዉ ማለቴን

እንደገና ወደፍቅር ህይወት እንመለስ ለማለት እንዳሰብኩ

አድርጋ ነዉ የተረጎመችዉ። በፍቅር አብረዉት ከነበሩት ልጅ ጋር

ወንድም ሆኖ መቀጠል ይከብዳል። ኢክሩ እኔን ወንድም ብሎ

መቀበል ከብዷታል። እንዴት አይከበዳት? ስንቱን አብረን

አሳልፈናል እኮ!! ትዳር ተወድዶ ጉድ አደረገን። ማህበረሰባችን

የትዳርን ዋጋ አስወድዶ የዝሙትን ዋጋ አርከሰንብን ተቸገርን!!

ወሬ ለመቀየር ያህል "ሱመያ የምትባል ልጅ ከናንተ ጀመዓ

(ህብረት) አናግራኝ ነበር።" አልኳት።

እየሳቀች "እኔ ነኝ እንዲያናግሩህ የጠቆምኳቸዉ!!" አለችኝ።

እኔም ሳቋ ተጋባብኝ!! ከዛ ደግሞ አሳዘነችኝ።

ኢክሩ ነገረ ስራዋ ሁሉ ግራ ያጋባል።

.

ኢኩ ለሷ ጥላቻ እንዳለኝ መጠርጠር ሳትጀምር አትቀርም።

በስልክ ስናወራ እየጮህክብኝ ነዉ ፣ ተቆጣኸኝ ምናምን የሚሉ

ሰበቦችን እየፈለገች ታኮርፋለች። የሚንቃትን ፈዉዛንን እና

ኩርፊያዉን አራሷ በጠርጣሪዉ ጭንቅላቷ ትፈበርካለች። እኔ

እንዴት ኢክሩን እጠላታለሁ? የማይመስል ነዉ።

የዛን ቀን ጉዳያችንን እንደጨረስን ወደ ቤቷ ሸኝቼያት ተመለስኩ።

ከዚህ ቀን በኋላ ከኢክራም ጋር በስልክም በአካልም ያለን

ግንኙነት እየቀዘቀዘ መጣ። እኔ ፍቅረኛ የሚባለዉን ታፔላ

ብታነሳልኝ ከጎኗ ሆኜ እንደወንድም ላማክራት ፈቃደኛ ነበርኩ።

እሷ ግን የፈለገች አይመስለኝም።

.

ከነሱመያ ጋር በቀጣይ ልንገናኝ ስንቀጣጠር ከመስጂድ ዉጪ

ስለነበር ከብሩክ ጋር አብረን ሄድን። አንድ ሙሉ የቆንጆ ቡድን

ከተቀጣጠርንበት ህንፃ ስር ቆሞ ጠበቀን። አራት ነበሩ። ሱመያ

የትኛዋ እንደሆነች አላዉቅም። ወደኔ ቀረብ ሲሉ አንደኛዋ ቀደም

እያለች ስትመራቸዉ እሷ መሆኗን ገመትኩ። ከአራቱ ዉስጥ

አንደኛዋ በጣም ነበር የምታምረዉ!! በጣም!! ሲጀመር ሁሉም

ቆንጆ ነበሩ።

ሱመያ እንደሆነች የገመትኳት ልጅ ፈገግ ብላ አንድ ደብተር

እየሰጠችኝ "ሁሉንም እዚህ ላይ ፅፈነዋል እየዉና አስተያየትህን

ትሰጠናለህ!!" ብላ ሞዘቀች!! ሱመያ ነበረች። ድምጿ ሲሰረቀረቅ

ነበር የለየኋት።

ብሩኬ እኔ ከሱመያ ጋር ሳወራ እሱ አብራት ያለችዉን ቆንጅዬ

ልጅ እየተመለከተ ተቁነጠነጠ። ደብተሩን ተቀብያቸዉ ገና ዞር

እንዳሉ ብሩኬ ደብተሩን ቀምቶኝ ሮጠ።

ነገረ ስራዉ ሁሉ ስለገባኝ "ብሩኬ አይሆንም!!" እያልኩ

ተከተልኩት። ደብተሩ ላይ ስልክ ቁጥሮችን ስላየ ነበር ነጥቆኝ

የሮጠዉ።

ብሩኬ ስልክ ቁጥሩን ስልኩ ላይ ለመመዝገብ አስፖልት ተሻግሮ

ሮጠ። ተከተልኩት። ረዥም መንገድ ተሯሯጥን። እኔ በሀይማኖት

ጉዳይ ምክንያት ሴቶች የሰጡኝን የግል መረጃ አሳልፌ መስጠት

አልፈልግም። በሀይማኖት ጉዳይ ተገናኝቶ ፈጣሪን የሚያምፅ

ነገር መፈብረክ ያስጠላል። አንዳንዶች ሀይማኖታዊ ህብረቶችን

ሲቀላቀሉ ቁጥብ እና ቆንጆ የሆኑ ልጆችን ለማጥመድ ነዉ።

ለነገሩ ሁሉም የህሳቡን ያገኛል። ቆንጆ የፈለገዉ ቆንጆ ፣

የቆንጆዎች ካዝና ባለቤት የሆነዉን ፈጣሪዉን የፈለገ ደግሞ

ፈጣሪዉን!! ለዛ ነዉ ከብሩኬ ጋር እንዲህ የተሯሯጥነዉ።

አለማዊ ሽኩቻዉ ሰልችቷቸዉ መስጂድ የመጡትን ልጆች

ወደማይፈልጉት ጉዳይ ዉስጥ እንዲገቡ መሳሪያ ላለመሆን!! ግን

ብሩኬ ስልክ ቁጥሩ ያለበትን ገፅ ቀድዶ ወሰደዉ።

በኋላ ላይ ሳጣራ ብሩክ የሻፈደባት ልጅ ስም ኢማን ነበር። በኋላ

ላይ ከኔ የወሰደዉ ስልክ ትክክለኛ አለመሆኑን ሲያዉቅ ኢክራምን

እንድትሰጠዉ ለመናት። ኢክራም መጀመሪያ ላይ እኔ ባለሁበት

ሲጠይቃት አልሰጥህም አለችዉ። በኋላ ላይ ግን ሲያኮርፈኝ

ጨነቀኝ ምናምን ብላ ስልኳን ሰጠችዉ። የመጀመሪያ ቀንም

ያልሰጠችዉ እኔ ስለነበርኩና አቋሜን ስለምታዉቅ ላለመጠቀር

ይመስለኛል።

.

አንድ ቀን ከሱመያ ጋር ቻት እያደረግን ሁዳ የምትባል ልጅ አዉቅ

እንደሆነ ጠየቀችኝ። እኔ ማዉቃት ሁዳ ቤተ መፅሀፍ አብረን

የምናነብ የነበረችዉን ቀጭዋን ሁዳ እንደሆነ ነገርኳት። እህቷ

እንደሆነች ነገረችኝ። ገረመኝ በፍፁም አይመሳሰሉም።

መልካቸዉም ድምፃቸዉም ፈፅሞ አይመሳሰልም ነበር። ሱመያ

የሁዳ እህት መሆኗን ካወቅኩ በኋላ በመካከላችን ያለዉ

ግንኙነት እየጠነከረ ሄደ።

.

ብሩክ ሴት ማሯሯጥ ላይ በጣም በርትቷል። ከሪሀና ጋር በአንዴ

ከነሱ ከሷ ጋር ሲደባበሩ ይኸዉ ኢማንን ለመጀንጀን ይሞክራል።

ለነገሩ ኢማን ፊትም አልሰጠችዉም። አልሰማህኝ አለችው። እኔ

የስነ አእምሮ እዉቀቴ ከፍ እያለ ሲመጣ ሰዎችን እንደድሮዉ

በግርድፉ ማዳመጥ አቆምኩ። በንግግራቸዉ ዉስጥ

ስሜታቸዉን እከታተላለሁ፣ በሰዉነት እንቅስቃሴያቸዉ ብቻ

የደበቁትን እረዳለሁ። የተለየ የእይታ ምህዳር ፈጠሩልኝ።

.

ጊዜዉ የፈተና ወቅት የደረሰበት ስለነበር እና ሰፈር ስለነበርኩ

ከሰፈራችን ቤተ መፅሀፍ አልጠፋም ነበር። የረዊና እህት

እምነትም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ስለደረሰ አብራኝ ቤተ

መፅሀፍ መዋል ጀመርን። እምነት በጣም ደስ የምትል ልጅ ናት።

ብሩኬ ሊጀነጅናት ፈልጎ አይሆንም ብዬዋለሁ። የረዊና አደራ

ስላለብኝ እና ብሩኬም በኔ ምክንያት ስለተዋወቃት አርፎ

እንዲቀመጥ ነግሬዉ እሺ አለኝ። ጓደኝነት ለኔ ከአንድ ብቻ

ሳይሆን ከብዙ አቅጣጫ የሚታይ ነገር ነዉ። ረዊናም እንደ ብሩክ

ጓደኛዬ ናትና አደራዋን መጠበቅ ይኖርብኛል። አደራዉ እምነትን

ያልሆነ ነገር ዉስጥ ከመግባት መታደግ ነዉ።

.

አንድ ቀን አስራአንድ ሰዓት አካባቢ እኔናእምነት ቤተ መፅሀፍ

እያነበብን ኢክሩ መጣች።

ከኢክሩ ጋር አስተዋዉቂያቸዉ ስለነበር

ምንም አላለችም። እንደዉም ከእምነት ጋር ጥሩ ወዳጅ

ሆነዋል። እንዴት እንደሆነ ባላዉቅም ብሩኬ ቤተ መፅሀፍ መጥቶ

ተቀላቀለን። እያጠናም አልነበረም። ሰዓቱ ሲገፋ ወደ ቤታችን

ለመመለስ መንገድ ጀመርን። እምነትን እና ኢክራምን ሸኝተን

እኛ ወደየቤታችን ለመመለስ ነበር ያሰብነዉ። መንገድ ላይ

እየሄደን ኢክሩ እግሯ ትቦ ለመሸፈን የተደረጉ አርማታዎች

መካከል ሾልኮ ገባ። ለማዉጣት ስትሞክር በፍፁኝ እግሯ

አልወጣም አላት!!

.

ይቀጥላል...

ልብ ወለድ

ማንበብ ሙሉ ሰው ያረጋል.....

https://telegram.me/amharicfiction

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራአምስት

(ፉአድ ሙና)

.

.

የኢክራም እግር ትቦጢን ለመሸፈን በተረበረቡ አርማታዎች

መካከል ሾልኮ ሲገባ እኔ ተንደርድሬ ያዝኳት። እግሯ ለመዉጣት

ስላልቻለ ረጋ ብላ እንድታወጣዉ እና ሰዉም እየበዛ ስለነበር

ከሰዉ እይታ ኢክሩን ለመሸፈን ኢክሩን ለቅቄ ከእምነት ጋር ጎን

ለጎን ቆመን ለመከለል ሞከርን። እኔ እግሯን ጎትቼ ላወጣላት

አልችልም። ምክንያቱም አርማታዉ እግሯን ሊቧጭራት ይችላል።

ሁሉም ሰዉ ከመዉደቁ በላይ የሚያመዉ በሰዉ መታየቱ ነዉና

እሷ ተረጋግታ እግሯን እስከምታወጣዉ ድረስ ከእይታ ልጋርዳት

ፈለግኩ። በዚህ መካከል ብሩኬ ኢክራምን ደግፎ ይዟት ነበር።

ሁላችንም የትናንት ጭንቀታችንን አልፎ ስናየዉ ደስ ይለናል።

ኢኩዬም እግሯ ከትቦዉ ዉስጥ ከወጣ በኋላ እንዴት እንደነበረች

እያሰበች እንድትስቅ ብዬ ፎቶ አነሳኋት። ትልቁ ስህተት

የተፈጠረዉ እዚህ ጋር ነዉ። ፎቶ ያነሳኋት በእኔ ሳይሆን በእምነት

ስልክ ነበር።

አንድ አሮጊት "ተሰበረች?" አሉ ወደ ኢክራም እየመጡ።

"የሚሰብር ነገር ይስበሮት!" አለ ብሩኬ በንዴት። አንዳንዴ ሰዎች

የሚጠይቁትን ጥያቄ በአግባቡ አያዉቁም። የታመመ ሰዉ

"ተሻለዉ ወይ" ተብሎ እንጂ "ሞተ ይሆን?" ተብሎ አይጠየቅም።

ሴትየዋም ኢክሩን "እግሯ ከጉድጓዱ ወጣላት?" ብለዉ

እንደመጠየቅ "ተሰበረች?" ብለዉ መጠየቃቸዉ አግባብ

አልነበረም። ግን የዛን ቀን እኔ ስሜታዊ ያልሆንኩትን ያህል

ብሩኬ እንደዛ መቆጣቱ ገርሞኛል። ለነገሩ እኔ ምክንያታዊ

ከርከር እንጂ ዉልታዊ ምልልስ ሲጀመርም አልወድም።

በስንት መከራ የኢክሩ እግር ከትቦዉ ዉስጥ ወጣ። አካባቢዉ

ላይ ከነበረ ቤት ዉሀ ጠይቀን ኢክሩ ተጣጠበች። ዘንቦ ስለነበር

ትንሽ ጭቃ ነክቷት ነበር። የዛን ቀን ብሩኬ ላደረገዉ ነገር

ምስጋና ይገባዋል። በጣም ነበር ሲጯጯጥ የነበረዉ።

.

ከዛ ሁሉ ጭንቅ በኋላ የኢኩዬ እግር በሰላም ወጥቶ መንገድ

እንደጀመርን እኔ ስትወጣ አይታዉ ዘና ትልበትና እናጠፋዋለን

ብዬ አሰቤ በእምነት ስልክ ያነሳኋትን ጉድጓዱ ዉስጥ እግሯ

እያለ የሚያሳይ ፎቶ አሳየኋት። አይታዉ ፈገግ አለች!! ልናጠፋዉ

ስንል ግን እምነት በፍፁም አይሆንም አለች። ስልኳ የሚስጥር

ቁጥር ስለሚጠይቅ ያለ እምነት ይሁንታ ማጥፋት አይቻልም።

ነገሩ ከቁጥጥሬ ዉስጥ እንደወጣ ተረዳሁ። ኢክሩ በጣም

እንዳዘነችብኝ ገብቶኛል። እኔ ግን ፎቶዉን ያነሳሁት የኢኩ ፊት

ላይ ፈገግታ ለመፍጠር ነበር። እምነት ሁሉንም ነገር

አበላሸችዉ።

በነጋታዉ ከእምነት ጋር ቤተ መፅሀፍ ስንገናኝ ሰበብ ፈልጌ

የስልኳን የሚስጥር ቁልፍ እንድትከፍትልኝ ጠየቅኳት።

ከፈተችልኝ። ወዲያዉ በፍጥነት ትናንት ያነሳሁትን ፎቶ ከእምነት

ስልክ ላይ አጠፋሁት። እምነት ስልኳን ስመልስላት ወዲያዉ ፎቶ

ዉስጥ ገብታ ምስሉን ማጥፋቴን አይታ ሳቀች።

"ፊዊ እንደምታጠፋዉ አዉቅ ነበር!!" አለችኝ እየሳቀች!

"አሁን እንዴት ቀለል እንዳለኝ ብታዉቂ ከምር ጨንቆኝ ነበር!!"

አልኳት

ሳቋን መቆጣጠር እያቃታት "አይቅለልህ እንደምታጠፋዉ

ስለገመትኩ ኮፒ አድርጌ ሌላ ቦታ ላይ አስቀምጨዋለሁ። ፒሲ

ላይ ሳይቀር አለ።" አለችኝ።

ሌላ ሰዉ ቢሆን እጣላዉ ነበር ግን እምነት ስለሆነች ምንም

ማድረግ አልቻልኩም። ዉስጧ ምንም ክፋት ኖሮ አይደለም

እንዲህ ያደረገችዉ።

.

በቀጣይ ከኢኩ ጋር ቤተ መፅሀፍ መጥታ ስንገናኝ ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ዉጪ ሆኖ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክሬ ስለፎቶዉ ይቅርታ ጠየቅኳት። ኢክራም ግን ከላዩ ይቅርታ ብታደርግልኝም በዉስጧ እንዳዘነችብኝ ያሳብቃል።

ያደረግኩት ነገር በራሱ ትክክል አይደለም። ያደረግኩትን ነገር ትክክል የሚያደርገዉ ያደረግኩበት ምክንያት ነበር። ኢክሩ ፊት ላይ ፈገግታ መፍጠር። ግን ሁሉም ነገር ከቁጥጥሬ ዉጪ ሆኖ ኢክሩ ፊት ላይ ፈገግታ ይፈጥራል ብዬ የሰራሁት ስራ በእምነት ምክንያት ኢክሩ ፊት ላይ ሀዘን ፈጠረ።

አላማዬ ለመልካም የነበረ ቢሆንም ዉጤቱ መጥፎ ሆኖ ስላረፈዉ ይቅርታ ከመጠየቅ ዉጪ አማራጭ የለኝም። ይቅርታ የማያሸረዉ በሽታ የለም!! እምነቴ ነዉ!!

.

ኢክራም ከነዚህ ቀናት በኋላ ከእኔ ጋር ያላት ግንኙነት እየቀዘቀዘ መጣ። የሚያገናኙንም ምክንያቶች ጠፉ። እኔም እሷ እየቀዘቀዘች ስትሄድ በጣሙን እየቀዘቀዝኩ መጣሁ።

በዚህ መሀል አንድ የግቢ ጓደኛዬ ሁለት ቆንጆዬ የግቢ ተማሪዎች ሊተዋወቁኝ እንደሚፈልጉ ነገረኝ። በቁንጅናቸዉ ከግቢያቸዉ ተነጥለዉ የሚታወቁ ናቸዉ። እነሱ የአምስት ኪሎ ግቢ ተማሪዎች ሲሆኑ እኔ ደግሞ የስድስት ኪሎ ግቢ ተማሪ ነኝ። የቆንጆዎች መናኸሪያ የሆነዉ የአምስት ኪሎ ግቢ ዉስጥ በቁንጅና መታወቃቸዉ ምን ያህል ቆንጆ ቢሆኑ እንደሆነ ግልፅ ነዉ። ለጊዜዉ ስለማይመቸኝ ከአንድ ሳምንት በኋላ እንደማገኛቸዉ ነገርኩት።

.

ኢክሩ እኔ ጋር አትደዉልም ግን ብሩኬ ጋር ትደዉላለች። እሱም

ይደዉልላታል።

አንድ ቀን እነ ብሩኬ ቤት ሆንን ብሩኬ ኢኩን ችላ ሳይል

እንዲያማክራት አደራ አልኩት። እሱም አደራዉን ተቀበለ።

ኢክራም ወደ ትዳር ህይወት እንድትገባ ብዬ እንደተዉኳት

ያዉቃል። ስለዚህ ከማንም ጋር እንዳትንዘላዘል መምከር

አያቅተዉም ብዬ አስባለሁ።

.

በቀጣዩ ሳምንት ልጆቹን ለመተዋወቅ ወደ ተቀጣጠርንበት

ከስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ዋናዉ በር ፊት ለፊት ወዳለዉ መናፈሻ

ሄድኩ። ከአንድ ዛፍ ስር ያለ ወንበር ላይ የተቀመጠች ቀይ ሴት

እጇን አዉለበለበችልኝ። እኔ ሁለት ሴቶች እንደሚጠብቁኝ ነበር

የተነገረኝ።

"ፈዉዛን ዌልካም!!" አለችኝ ከመቀመጫዋ ተነስታ እንድቀመጥ

እየጋበዘችኝ።

"ሁለት ሰዉ እንደሚጠብቀኝ ነበር የተነገረኝ!!" አልኳት።

"አዎ ነዉ ግን ዛሬ ለምናወራዉ ነገር የሜሮን መኖር አስፈላጊ

ስላልሆነ ነዉ ብቻዬን የመጣሁት!!" አለችኝ።

"ባይዘዌይ ፊርደዉስ እባላለሁ!!" አለች የአክብሮት ፈገግታ

እያሳየችኝ።

አየኋት በጣም ቆንጆ ናት! በጣም!! ከኢክሩ ሌላ ቆንጆ ነበር

እንዴ? የእዉነት በጣም ዉብ ናት። የለበሰችዉ ቀሚስ ሰፋ ያለ

ነዉ። አይጨንቅም!! በጣም ልብሱን አሳምራዋለች።

"እና እንደዚህ ዉብ ሆነሽ ፊርደዉስ ካላሉ ምን ብለዉ ስም

ሊያወጡልሽ ነበር?" አልኳት እየሳቅኩ!

ፊርደዉስ ሳቋን ለቀቀችዉ!! ጉንጯ ላይ ስርጉድ አለ። ወይኔ በቃ

ይህቺ ልጅ ልቤን ልታሰረጉደዉ ነዉ።

ፊርደዉስ ከጀነት በጣም ያማረዉ ጀነት ነዉ። ጀነት እንደሆቴል

ባለ 4 ባለ 5 ኮከብ እንደምንለዉ ይለያያል። ሰው እንደስራዉ

ምርጡ ላይ ይገባል። ስሟ እና ዉበቷ በጣም የተስማማ ነዉ።

ፊርደዉስ ስቃ ስትጨርስ "ፈጠዛን መንገድ ላይ ነበር ያየሁህ!

ከዛም ከሰዎች ስላንተ አንዳንድ መረጃዎችን አገኘሁ!!" አለችኝ።

ፈገግ አለችና እጇን እየዘረጋችልኝ ያዘዉ አለችኝ። ይሄ ነገር

ወዴት ወዴት እየሄደ እንደሆነ ግራ ገባኝ።

"ይቅርታ ሴት አልጨብጥም!!" አልኳት

"ለምን?" አለችኝ

የእዉነት የእስልምና እምነት ተከታይ አልመስልህ አለችኝ።

ሙስሊም ሆና ይህን አለማወቋ አሳዘነኝ።

"ቁርዓን ላይ ማን ማንን መንካት እንደተፈቀደልሽ ተፅፏል

አንብቢዉ!!" አልኳት።

"እሺ ለዛሬ ብቻ ጨብጠኝ!!" አለችኝ በአይኖቿ

እየተለማመጠችኝ። አለንጋ ጣቶቿን ፊቴ ድረስ አስጠጋቻቸዉ።

የአይኗን እንቅስቃሴ በሚገባ አጤንኩት ይዞር ይዞርና ወደ ግራ

እየሰረቀ ያያል። የስነ አእምሮ ተማሪ እንደመሆኔ በግራ በኩል

የሚያየን ሰዉ እንዳለ ገመትኩ። ዞር ስል አንዲት ሴት የስልኳን

ካሜራ አነጣጥራ እየቀረፀችን ነዉ።

.

ያላየሁ መስዬ

"ፊርደዉስ ሪያሊቲ ሾዉ ለመስራት አስበሽ ነዉ እንዴ የጠራሽኝ?"

አልኳት

ወዲያዉ እንደባነንኩ ስለገባት ጓደኛዋ መቅረፅ እንድታቆም

በእጇ ምልክት ሰጠቻት።

.

"ፈዉዛን በጣ

ም ይቅርታ!! በቃ እዉነቱን እነግርህለሁ!!" አለችኝ

የመሸነፍ ስሜት እየታየባት

እኔ የሰዉነቷን እንቅስቃሴ እና የምትመርጣቸዉን ቃላት

በማዳመጥ የምታወራዉ እዉነት መሆን እና አለመሆኑን ለማጤን

ተዘጋጀሁ።

"ፈዉዛን እኔ የሶፍትዌር ኢንጅነሪንግ ተማሪ ነኝ። እኛ ባች ዉስጥ

"አይ ዊል ዱ ኢት" የሚባል ሙድ አለ። አንድ ቀን ጓደኛሞች

አንድ ላይ ሆነን የኛ ጓደኛ ልትጨብጥህ ስትል ሴት

አልጨብጥም ስትላት አየሁ። እና እኔ "አይ ዊል ዱ ኢት" አልኩ።

እኔ አንተን በግድ እንድትጨብጠኝ ላደርግህ ከነሱ ጋር

ተወራረድኩ።" አለችኝ።

"ዉርርዱን ባትፈፅሚ ምን ይከተልሻል?" አልኳት በጣም

አሳዘነችኝ!

"ለኔ ዉርደት ነዉ!! ማንንም የሚያንበረክክ ዉበት አለኝ!! ጓደኞቼ

መቀለጃ ነዉ የሚያደርጉኝ የምፈራቸዉ እነዚህን ነዉ ሲቀጥል

ሁሉንም ሸራተን አራት ለመጋበዝ እገደዳለሁ።" አለችኝ።

ሁለት ነገሮች አስገረሙኝ በዉበቷ እርግጠኛ መሆኗ እና

ሀንዳዉት ኮፒ ማድረጊያ ያጡ በሞሉባት ሀገር ለቀልድ ሸራተን

ራት የሚገባበዙ ተማሪዎች መኖራቸዉ። ደግሞ እኮ እራት

መጋበዙ ለሷ ቀላል ነዉ። ያስፈራት ሙድ መያዣ መሆኑ ነዉ።

"ልትጨብጪኝ ብቻ ነዉ የፈለግሽዉ?" አልኳት ድርድሩ

ለመጨባበጥ ብቻ የተደረገ አለመሆኑን ከመቀጮዉ

ስለተረዳሁ።

እንደማፈር እያለች "አይደለም ከንፈርህን መሳም ነዉ ዉርርዱ

አለችኝ።"

ከወንበሬ እየተነሳሁ "እንዳታስቢዉ!!" አልኳት።

ፊቷ በእልህ እየቀላ "ፈዉዛን ታደርገዋለህ!!" አለችኝ።

እንደተቀመጠች ትቻት ሄድኩ።

.

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/abpdfs

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራስድስት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ሰዓታት ምንም የሰዉ ልጅ ለዉጥ ቢፈጥርም ባይፈጥርም

ከመቁጠር አይወገዱም። ተኝተንም እንዋል በስራ ተጠመድን

ቀን ይነጉዳል። እንደቀልድ አመት አለቀ ይባላል።

ከኢክራም ጋር የፍቅር ግንኙነታችንን ካቋረጥን ከሶስት ወራት

በላይ ተቆጠሩ። በወንድምነት የነበረንንም ትስስር ኢክሩ

ካቆረፈደችዉ ሁለት ወር ሆነ።

የዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ አመት ትምህርቴን አጠናቅቄ ክረምቱን

እየቦዘንኩ ነበር። አንዳንዴ እዚህ ካፌ እየመጣሁ ከረሂማ ጋር

እጫወታለሁ። አንዳንዴ ብሩኬ ጋር እየሄድኩ እደበራለሁ። በዛ

ሰሞን ግን ለተለያዩ ተቋሞች የስነ ፅሁፍ ስራዎችን ድህረ ገፃቸዉ

ላይ በመስራት ተጠምጇ ስለነበር ኢንተርኔት ላይ ተጥጇ እዉል

ነበር።

.

አንድ ቀን እንደተለመደዉ ኢንተርኔት ላይ ተጥጇ ከማላዉቀዉ

ሰዉ መልዕክት ደረሰኝ።

ልጁ ሰላምታ እንደተለዋወጥን

"ፊዉዛኔ እኔ ሰፈር አካባቢ አዉቅሀለሁ። ከኢክሩ ጋርም ግንኙነት

እንደነበራችሁ አዉቃለሁ። አሁን የፍቅር ግንኙነት ዉስጥ ናችሁ

እንዴ?" የሚል መልዕክት ላከልኝ።

ወዲያዉ "እኔና እሷ መገናኘት ካቆምን በጣም ቆይቷል።

በመካከላችን ምንም አይነት ግንኙነት የለም።" አልኩት።

ልጁ አመስግኖ ተሰናበተኝ። ትንሽ ቆይቼ አሰብኩና በመልሴ

ተፀፀትኩ። ፍቅረኛዬ ናት ነበር ማለት የነበረብኝ። ኢክሩን ከዚህ

በኋላ አግብታ እንጂ ከማንም ወንድ ጋር ስትንዘላዘል ማየት

አልፈልግም። የልጁ ጥያቄ ደግሞ ከተዉካት ልዉሰዳት አይነት

ነዉ። ማንም የጣለዉን ሲያነሱበት አይወድም። ሊያዉም

እንድታገባ የምመኝላትን ሴት አብራዉ ስትንዘላዘል ማየት

ያመኛል። ዉስጤ ሰላም አጣ። የኢክሩን የፊስቡክ ገፅ

ለመንብኘት ገባሁ አንፍሬንድ እንደተደረግኩ ነዉ። ላወራትና

ከልጁ ላስጥላት ፈለግኩ።

.

ከኢክሩ ጋር ከሶስት ወራት በኋላ ድጋሚ ፊስቡክ ላይ አወራን።

ስላለችበት ሁኔታ አንዳንድ ነገሮችን ጠየቅኳት። እንደድሮዉ

በመካከላችን ሰላም አዉርደን በወንድምነት እንድንቀጥል

ጠየቅኳት። መልዕክቱን የላኩላት በእንግሊዘኛ ስለነበር የፍቅር

ግንኙነታችንን ድጋሚ መልሰን እንቀጥል ያልኳት መስሏት

እንዲህ አለችኝ:

"እኔ ስትፈልግ የምትጥለኝ ስትፈልግ የምታነሳኝ እቃ

አይደለሁም። አሁን ከሌላ ሰዉ ጋር የፍቅር ግንኙነት

ጀምሬያለሁ።"

ደነገጥኩ!! እሞትልሀለሁ ስትለኝ የነበረችዉ ኢክሩ ናት በሁለት

ወር ዉስጥ ከህይወቷ ማህደር ፍቃኝ ከሌላ ወንድ ጋር ፍቅቅሮሽ

የጀመረችዉ? ወይስ ሲጀመርም አፈቀርን ሲሉ ሰምታ እንጂ ፍቅር

ምን እንደሆነ እንኳ አታዉቅም? እንዴ እኔ እኮ ኢክሩ ግጥም

ስለማትወድ ብዬ ግጥም መፃፍ ያቆምኩኝ ይኸዉ እስከአሁን

ግጥም አልፃፍኩም። ቆሻሻ ላይ የተወለደ ፍቅር ንፅህና ሊኖረዉ

እንደማይችል ግልፅ ነበር። ትዳር ላይ ያልተመሰረተ ግንኙነት

ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። ኢክሩ እንዴት እኔን ረስታ ሌላ ወንድ ጋር

ለመሄድ ደፈረች? እኔ እኮ እንኳን ልረሳት በጣም ስትሰቅ

የሚሸበሸበዉ አፍንጫዋ አሁንም አይኔ ላይ አለ። ኢክሩ እኮ

እየተኮላተፈች 'ደ' ስትል አሁንም ጆሮዬ ላይ ይደጋገማል።

.

እራሴን አረጋጋሁ እና ኢክሩ ልታናደኝ ፈልጋ እንጂ እንደዚህ

የምታደርግ ልጅ እንዳልሆነች ብዙ ምክንያቶችን እየሰጠሁ ራሴን

አሳመንኩት።

እንደዉም እኔ እወድሻለሁ ስላት አይኗን ወደ ሰማይ እየሰቀለች

"ፊዉዚዬ የኔ ድመት አንተ ትወደኛለህ። እኔ ላንተ ያለኝ ፍቅር ግን

ካንተ በጣላላአም ይልቃል።" ያለችዉን አስታወስኩ።

ኢክሩ በሁለት ወር ዉስጥ ይሄን ፍቅሯን ከልቧ አስወጥታ

ከነገስኩበት የልቧ ዙፋን ላይ ሌላ ሰዉ እንደማታስቀምጥ ለራሴ

ነገርኩት።

"ምንም ችግር የለዉም። መብትሽ ነዉ!" ብዬ መለስኩላት።

አልተናደድኩልሽም እንደማለት ነበር ያሰብኩት።

እኔ ፍቅረኛ ይዤ ከሆነ ጠየቀችኝ እንዳልያዝኩ ነገርኳት።

.

ወደ ማታ ላይ ብሩኬን አግኝቼ የተፈጠረዉን ነገር ነገርኩት።

ኢክሩ ፍቅረኛ ይዛ ከሆነም ሁለቱን ለመነጣጠል ስል የፍቅር

ግንኙነት ከሷ ጋር ልጀምር እንደምችል ነገርኩት። ማንም እንደኔ

ሊያስብላት አይችልም ብዬ አምናለሁ። ቢያንስ ከኔ ጋር ከሆነች

ዝሙት ላይ አትወድቅም። ሌላ ወንድ ኢኩ ላይ ስሜቱን

ሲያስታግስ መመልከት አልፈልግም። ኢኩ ንግስት ሆና ባል

ስታነግስ ነዉ መመልከት የምሻዉ።

አንገቴን አቀርቅሬ "ብሩኬ ኢኩ የእዉነት የፍቅር ግንኙነት ጀምራ

ከሆነ እኔ ኢኩን እና ልጁን ለማጣላት ከሷ ጋር የፍቅር ግንኙነት

እስከመቀጠል ድረስ ለመጋፈጥ ወስኛለሁ።" አልኩት

ብሩኬ እንደመቆጣት እያለ "በቃ ተዋት የራሷን ህይወት

ትኑርበት!!" አለኝ

ሳግ እየተናነቀኝ "ብሩኬ እኔ እኮ እንድታገባ እንጂ ከማንም ጋር

እንድትንዘላዘል አይደለም የተዉኳት!!" አልኩት።

"በቃ ተዋት አይመለከትህም!!" አለኝ አሁንም ቆጣ እንዳለ ነዉ።

ብሩኬ ይሄን አቋሜን ስላልደገፈልኝ ተበሳጨሁ። ከዚህ በኋላ

የምወስዳቸዉን እርምጃዎች እሱን ሳላማክር ለመዉሰድ

ወሰንኩ።

.

ፊርደዉስ ክረምቱን በተደጋጋሚ እየደወለች እንድንገናኝ

ትጠይቀኛለች። እኔ ግን ዉርርድን ልትፈፅምብኝ እንደሆነ

ስለማስብ ላገኛት ፈቃደኛ አልሆን አልኳት። እዉነት ለመናገር

በኔና በሷ መካከል ሀይማኖት እና ማህበራዊ ስርዓታችን ልቅ

መሳሳምን ባያወግዝ ኖሮ እኔ ነበርኩ ከንፈሯ እንደ ኢክሩ

እስኪያብጥ የምስማት!! ግን ሰዉ እንደመሆኔ እንደ እንስሳ

ማሰብ የለብኝም። ስጋዬ ይፈልጋል አልዋሽም!! ግን ፈጣሪዬን

ማስቆጣት አልፈልግም። እሱን ካስቆጣሁ አንጂን ፊርደዉስን

አግኝቼ ጌታዬን ላጣ እችላለሁ። እሱን ባስደስት ግን ጌታዬ

የፊርደዉስ አይነት ሴቶች ካዝና በእጁ ነዉ።

አንድ ቀን ሀሙስ እለት ፊርደዉስ ደዉላ የጓደኞቸዉን ልደት

ስለሚያከብሩ እንድገኝ ጠየቀችኝ። ሙስሊም ስለሆንኩ ልደት

እንደማላከብር ነገርኳት።

"ኧረ ፈዉዛኔ ይሄን ያህልማ አታካብደዉ!!" አለችኝ።

በሷ ቤት አክርፊባት ሞታለች።

"ፊርደዉስ እኔ ሙዴ እንደዚህ ነዉ!! እንደየሙዳችን ብንሆን

ይሻላል ከምንከራከር!" አልኳት

"እሺ በጣም ጥሩ!! በርገደይ ፓርቲዉ ላይ እኔም አልገኝም።

ካንተ ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ።" አለችኝ።

ተስማምተን ቀጠሮ ያዝን።

.

ፊርደዉስ ስትስቅ ጉንጮቿ በጣም ይሰረጉዳሉ። በጣም

ታምራለች። ሳር ቤት አካባቢ ተገናኘን። መኪና ይዛ ነበር

የመጣችዉ። ገቢና ገብቼ ከዚህ በፊት ገብቼበት ወደማላዉቀዉ

መናፈሻ ይዛኝ ሄደች። ቦታዉ በጣም ቆንጆ ነዉ። መኪናዋን ቦታ

አስይዛ ካቆመችዉ በኋላ ከመኪናዉ ወርደን ዉቡ የሳር መናፈሻ

ላይ የተቀመጡት ወንበሮች ላይ ተቀመጥን።

"ፈዉዛኔ እኔ ማንንም ወንድ እንዳንተ ተለማምጬ አላዉቅም።

ይህን ሁሉ የማደርገዉ እንድስምህ ስለተወራረድኩ ብቻ

መስሎህ ከሆነ ተሳስተሀል! አንተ የራስህ አቋም አለህ። እንቢ

ማለት መቻልን አስተምረኸኛል። እኔ ደግሞ አላማ አለኝ። ይሄን

አላማዬን ለማሳካት ካንተ የተሻለ አማካሪ የማገኝ

አይመስለኝም።" አለችና በረዥሙ ተነፈሰች

ፊርደዉስ የኮምፒዩተር እዉቀቷ በጣም ከፍተኛ መሆኑን

ከነገረችኝ እቅዶቿ ተረዳሁ። ያለማቋረጥ ለአንድ ሰዓት እቅዷን

ነገረችኝ። አሁን ፊርደዉስን በጣም አከበርኳት። በምችለዉ ሁሉ

ላግዛትም ቃል ገባሁላት።

.

የኢድ አል አድሀ ማለትም የሀጅ ስነ ስርዓት እንዳለቀ ያለዉ

የኢድ በዓል ደረሰ። ሁልጊዜም እንደማደርገዉ በሰም ቅደም

ተከተል ሰዎች ጋር እየደወልኩ እንኳን አደረሳችሁ እያልኩ በኢ

ተርታ ያሉት ጋር ደርሼ ኢክራም ጋር ደወልኩ።

የዛሬን አያድርገዉና ሌላ ጊዜ መጀመሪያ እሷ ጋር ደዉዬ ነበር

ቀሪዎቹ ጋር በሰም ቅደም ተከተላቸዉ የምደዉለዉ።

አነሳችዉ "ኢኩዬ እንኳን አደረሰሽ!!" አልኳት።

"እንኳን አብሮ አደረሰን!" አለችኝ እየተንጠባ

ረረች

"በዓል እንዴት ነዉ?" አልኳት

"ጥሩ ነዉ አለችኝ" በአጭሩ።

በመልሷ በጣም ተበሳጨሁ በስርዓቱ ተሰናበትኳትና ስልኩን

ዘጋሁት። እኔ የስነ አእምሮ ተማሪ ነኝ ኢክራምን እንዲህ

ያንጠባረራት ጉዳይ እንዳለ ተገለፀልኝ። አዎ ኢክራም ፍቅረኛ

ይዛለች። ካንተ ሌላ ላፈር ስትለኝ የነበረችዉ ኢኩ በሁለት ወር

ዉስጥ ሌላ ሰዉ ለምዳለች። ሰዉዬዉ ማን እንደሆነ ማወቅ

ፈለግኩ። ኢክራምን በቅርብ ርቀት መሰለል ይኖርብኛል።

ትኩረቴን ሙሉ ኢክራም ላይ አደረግኩ። አሁን ስላለችበት ሁኔታ

በአምስት ቀናት ዉስጥ ሙሉ መረጃ ሰበሰብኩ። አዎን የኢክራም

ህይወት ባልገመትኳቸዉ መንገዶች ሁላ ሳይቀር ተለዉጧል።

ማመን የማልችላቸዉን መረጃዎች አገኘሁ።

.

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/abpdfs

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራሰባት

(ፉአድ ሙና)

.

.

ብዙ ሰዎች ኢክሩ በፍፁም ጥፋተኛ እንዳልሆነች ነዉ

የሚያስቡት። "ሳይቸግርህ ጭረሀት" "አንተ ነህ የተዉካት!!"

ምናምን ይሉኛል። መተዉ ምን ማለት ነዉ? እኔ እኮ ኢክሩን

በጊዜዉ ለማግባት ስለማልችል እንድታገባ ብዬ ነበር

የተለየኋት። አደራ ያልኩት እኮ ፊጣሪዬን ነበር። እኔ እሷን

የመናፈቅ እሳቴን አፍኜ ይብቃን ስላት ለሷ የወደፊት ህይወት

ማማር እየተሰዋሁ እንደነበር ለምን አይገባቸዉም? ተዋት ይላሉ

እንዴ? አቅሜን አዉቄ ለፈጣሪ አሳልፌ በሰጠሁ ገፋት ይላሉ

እንዴ? አስመሳይ ሁላ!! ለነገሩ የነሱ ወሬ ለኔ ምንም ነዉ።

ያመንኩበትን ነገር እንጂ አላደርግም! ስሜት ያወረዉ ትዉልድ

የሚታይ ድርጊት እንጂ የታፈነ ስሜት አይገባዉም። ኢክራም

እንደተሰዋሁላት እንዲገባት ከፎቅ ላይ ራሴን መፈጥፈጥ

አይጠበቅብኝም። ማንም ሳያዉቅ በልቤ እንደታፈንኩ እኖራለሁ።

በኔ ዝምታ ዉስጥ ብዙ ትርጉም ነበር። እሷን በመተዉ

ያሳለፍኩትን ስቃይ እኔ ነኝ የማዉቀዉ። እስከዛሬ ጠረኗ

የማይረሳኝ ሰዉ እኮ ነኝ!! ከሷ በኋላ ማንንም ያላየሁ!! አዎ

የሱመያን የድምፅ መስረቅረቅ አድንቄያለሁ ፣ የፊርደዉስን ዉበት

አሞግሻለሁ ግን አንዳቸዉንም ከምላሴ አሳልፌ ልቤ ዉስጥ

አላስገባሁም። በሁሉም ሴቶች ዉስጥ የምትታየኝ ኢኩዬ

ነበረች። ሁሌም ቃሌን አስታዉሳለሁ። ስንለያይ ለራሴ የገባሁትን

ቃል!! የማግባት የስነ ልቦና እና የገንዘብ አቅም ሲኖረኝ

መጀመሪያ ኢኩዬን ፈልጌ ካላገባች ላገባት ለራሴ የገባሁትን

ቃል!! ተዋት ይላሉ እንዴ? ለሷ አልጋዉን አደላድዬ እኔ መሬት

ላይ በተኛሁ ገፋት ይላሉ እንዴ? ወረኛ ሁላ!! ሲጀመር እነሱ

የመዉደድን ልክ የወደዱትን የራስ ከማድረግ አሻግረዉ

መመልከት አልቻሉም። እኔ ዉዴታዬ በዝቶ ለኢክሩ ባል

ተመኝሁላት!! ኢክሩ ንግስት እንድትሆን ከነክብሯ እንድትለየኝ

አደረግኩ። ጌታዬን አስደስቻለሁ እሷ የፈለገችዉን ትበል ግድ

የለም። እንደኔ ያሰበላት፣ ወደፊትም የሚያስብላት ሰዉ ግን

የሚኖር አይመስለኝም።

.

ኢክራም ፍቅረኛ ይዣለሁ ያለችኝ ልታናደኝ ፈልጋ መስሎኝ ነበር።

የኢድ ቀን ስደዉልላት በንግግሯ ዉስጥ የሰማሁት ኩራት እና

ንቀት ግን ኢኩ የእዉነት ፍቅረኛ ይዛለች ወደሚለዉ ድምዳሜ

ስላደረሰኝ ነበር ለአምስት ቀናት ስለሷ መረጃ ያሰባሰብኩት።

ኢክራም በህይወቷ ላይ ብዙ ለዉጦች አስተናግዳለች።

ያቺ የጅልባቧን እጇታ ይዛ ጅልባቧን በጥርሷ ነክሳ እያየችኝ

ስትስቅ ትዝታዋ የማይረሳኝ ኢክራም ጅልባቧን አሽቀንጥራ ጥላ

የቱርክ ፋሽን ማራገፊያ ሆናለች። ያቺ ወንድ የማትጨብጠዋ

ኢኩ ማንም እንዳሻዉ የሚያቅፋት ተራ ሴት ሆናለች። ሌላዉ እነ

ኢክሩ ሰፈር ቀያረዉ እነ ሄናክ ሰፈር ገብተዋል። እናቷ

አግብታለች።

በጣም ቀፈፈኝ!! ለማንም ያላረከስኩትን እኔነቴን ያረከስኩላት

ሴት ከማንም ጋር እየተንዘላዘለች ነዉ። ከቻፒስቲክ ያለፈ

የማትቀባዋ ኢክራም ሜካፕ ይሉት ዱቄት ማራገፊያ ሆናለች

አሉኝ። በዚህ ሰዓት አጠገቧ ሆኜ ልረዳት ባለመቻሌ በጣም

ተሰማኝ። ሱመያን በቻለችዉ ኢክሩ የተሻለ ሰዉ እንድትሆን

እንድትረዳት ተማፀንኳት። ሱመያ ነገሩ ለጊዜዉ እንደሚከብድ

ነገረችኝ። ከሰፈሩ መራራቅ ባሻገር ለነሱመያ አልተበላሸሁም

ትላቸዉ ስለነበር በግልፅ እስከሚያገኟት መጋፈጡ ከብዷቸዋል።

ኢክሩን ፌስቡክ ላይ አንዳንድ ነገሮችን አወራኋት ፍቅረኛ

የሚባለዉም ነገር ቢቀርባት እንደሚሻል መከርኳት። ሁሉም

ወንድ እንደኔ ነዉ ብዬ አላምንም!! ኢክራም ላይ ማመን

የምችለዉ ወንድ እኔን ራሴን ብቻ ነዉ። ለምክሩ አመስግናኝ

የራሷን መስመር መከተል ጀመረች። እኔ ግን አሁን ላይ ማወቅ

የምፈልገዉ ኢክሩዬን እንደዚህ ያዘቀጣትን ፍቅረኛ ተብዬ ነዉ።

ግን በየት በኩል? እንዴት ልወቀዉ? ለጊዜዉ ጭንቀቴን በስልክ

ለረዊና ሁሉንም ነገር እየተነፈስኩላት አስታግስ ነበር።

.

የሁለተኛ አመት ተማሪ ሆንን አራተኛዉ ወር ተጀምሯል። ረዊናም

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እየተማረች ነዉ።

ብሩኬ የግል ካምፓስ አካዉንቲንግ ተመዝግቦ እየተማረ ነዉ።

ግን ትምህርት ቤቱ የሱሰኞች እና የሴሰኞች መናኸሪያ ስለነበር

ብሩኬ አይኔ እያየ ጫት ሙዱ ሆነ። ስለሴቶች አዉርቶ

አይጠግብም!!

"ፈዉዛዬ የእዉነት ሴቶች ርካሽ ናቸዉ!" አለኝ አንድ ቀን አብረን

ተቀምጠን

"እንዴት ብሩኬ?" አልኩት በጅምላ ሲፈጃቸዉ ደንግጬ

"ፈዉዛዬ እኛ ግቢ ያሉት ሴቶች እንዴት ሱሰኛ እንደሆኑ ብታይ፣

ደሞ ሴክስ በቃ እንደሰላምታ ነዉ!" አለኝ።

ዝም አልኩት!! በንግግሩ ዉስጥ ተግባሩን እየኮነነዉ ቢመስልም

እንደወደደዉ ተረድቻለሁ። ሴት ብቻዋን እንዴት ትረክሳለች?

አብሯት የሚንፈራገጥ ወንድ ግዴታ ያስፈልጋል። ይሄ ማለት

ደግሞ ሁለቱም ረክሰዋል ማለት ነዉ። ወይስ ወንድ

የማይረክሰዉ ሲጀመርም ክብር ስለሌለዉ ነዉ? እኔ የነብሩኬ

ሎጂክ አይገባኝም። ነገር ግን የብሩኬ አካሄድ እያማረኝ

ስላልሆነ አንድ ቀን ከትምህርት ስመለስ ቁጭ አድርጌ እንደ

ክብት እንዳይነዳ እና እንቢ ማለት መቻል እንዳለበት መከርኩት።

ነገር ግን የነብሩኬ ትምህርት ቤት መዓበል ብሩኬን ወደ

ጠጪነት መደብ ወረወረዉ!! እኔ እንዳልሰማ ይጠነቀቃል።

ይቅማል፣ይጠጣል!! በቀን እንደቁምነገር ከጓደኞቹ ጋር መጠጥ

ቤት ይዉላል። ብሩኬን ለማዳን አልቻልኩም!! በሰዓቱ ትኩረቴን

ሙሉ በሙሉ ትምህርቴ ላይ አድርጌ ነበር። ዉጤቴን ለማሻሻል

ታላቅ ትግል ላይ ነበርኩኝ።

.

ጁምዓ(አርብ) ቀን ፊርደዉስ ከትምህርት ስወጣ ልታገኘኝ

እንደምትፈልግ ነገረችኝ። ተገናኝተን ከሷ እቅድ ጋር በተያያዘ

ብዙ አወራን። የተቀመጥንበት ካፌ ዉስጥ ከመቀመጫዋ ተነስታ

ወንበሯን እየጎተተች ከጎኔ ተቀመጠች። ፊርደዉስ ሽቶ

አልተቀባችም። አጠገቤ እንደተቀመጠች

"ፊዊዬ የሆነ ነገር በህይወትህ ዉስጥ አልተፈጠረም? እስኪ

ካንተም ልስማ ንገረኝ!" አለችኝ።

የኔና የኢኩን ታሪክ እስኪሰለቻት ተረኩላት። አሁን ላይ ፍቅረኛ

ተብዬዉ ማን እንደሆነ ማወቅ እንደምፈልግ እና ማወቅ

እንዳልቻልኩ ነገርኳት።

ፊርደዉስ ከአይኖቿ እንባ እየፈሰሰ "ፊዊ በጣም ጥሩ ሰዉ ነህ።

እሷ ብትረዳዉም ባትረዳዉም አንተ ለህሊናህ ታምነህል!"

አለችኝ።

ወዲያዉ እንባዋን እየጠረገች "ፊዉዛኔ እኔ በቀላሉ ፍቅረኛዋ

ማን እንደሆነ እንድታዉቅ እረዳሀለዉ!" አለችኝ።

አይኗን እያየሁ "እንዴት?" አልኳት።

ፊርደዉስ ወደኔ ጠጋ እያለች

"ፊዉዛኔ ኢክራም የፌስቡክ አካዉንት እንዳላት እርግጠኛ ነኝ።

ፍቅረኛ ተብዬዉም አይ ቲንክ ይኖረዋል። እና በፌስቡክ

መጀናጀናቸዉ ኢቲ ኢዝ ኦቪየስ!! እኔ የሶፍትዌር ኢንጅነሪንግ

ተማሪ እንደመሆኔ የፌስቡክ አካዉንት ለመጥለፍ የሚያስችል

ማስፈንጠሪያ(Pheshing link) አሰራልሀለሁ። አንተ በቅርብ

እሷ በምታዉቀዉ ስልክ ቫይበር ላይ ሊንኩን ልክህ የሷ ፎቶ

ስላለዉ እንድታየዉ ትነግራታለህ። ታዲያ በራስህ ስልክ ሳይሆን

እሷ በምታዉቀዉ የሌላ ሰዉ ስልክ መሆን አለበት። እሷ ሊንኩን

ስትከፍተዉ ለመግባት ኢሜይል እና ፓስወርዷን እንድታስገባ

ይጠይቃታል። እሷ ፓስወርዷንና ኢሜይሏን ስታስገባ

ከማስፈንጠሪያዉ ጋር በተያያዘዉ የጂሜይል አካዉንት እኛ

ፓስወርዱን እና ኢሜይሉን እናገኛለን። የዛኔ አካዉንቷ ላይ

በነፃነት ገብተህ ጉዷን መበርበርም ሆነ ፍቅረኛዋን ማወቅ

ትችላለህ!! ክሊር?" አለችኝ።

"በጣም ግልፅ ነዉ። የኔ እብድ ምናለ እስከአሁን በነገርኩሽ

ኖሮ!" አልኳት እንደ ህፃን ልጅ እየቦረቅኩኝ።

.

የሰዉን የግል የህይወት መስመር ተላልፎ የግል መረጃዎቹን

መበርበር አግባብ እንዳልሆነ አዉቃለሁ። ግን ኢክሩ ከማን ጋር

እየተንዘላዘለች እንደሆነ ለማወቅ እና ዉስጤ ላይ የሚሰማኝን

መረበሽ ለማስወገድ ያለኝ የመጨረሻ መንገድ ስለሆነ የኢክሩን

የሚስጥር ጓዳ ለመፈተሽ እና የግለኝነት መብቷን ለመግፈፍ

ወሰንኩ።

ፊርደዉስ በሶስት ቀናት ዉስጥ የፌስቡክ ፓስወርድ መስረቂያ

ሊንኩን (Pheshing link) ሰርታ ላከችልኝ። አሁን ለኢክራም

ሊንኩን ልኮ እንድትከፍተዉ ለማድረግ አንድ የምታዉቀዉ ሰዉ

ስልክ ያስፈልጋል። አዎ አዩብ!! አዩብን ስልኩን እንዲያዉሰኝ

ማድረግ እችላለሁ!! የሪም ፍቅረኛ አዩብ!! ለኢክራምም ቅርብ

ስለሆነ በሱ ስልክ አታልዬ ሊንኩን መላክና እንድትከፍተዉ

ማድረግ እችላለሁ።

ቅዳሜ ማታ ላይ አዩብን መስጂድ አገኘሁት። የዛን ቀን ማታ ላይ

ስልኩ እኔ ጋር እንዲያድር ጠየቅኩት። እሱም የዛን ቀን ይፈልገዉ

ስላልነበር ለምን እንኳ ሳይለኝ ጠዋት ለፈጅር ሰላት(ለንጋት

ስግደት) እንዳመጣለት ነግሮኝ ስልኩን ሰጥቶኝ ሄደ።

ገና መንገድ ላይ ሆኜ የአዩብን ቫይበር ከፈትኩት ኢክራም ኦን

ላየን አለች። ሰላም ብያት በቅርቡ ስላገባች አንድ ጓደኛቸዉ

አወራኧት። እሷ ከአዩብ ጋር እንደምታወራ ነዉ እያሰበች

ያለችዉ። አሁን ለሰርጉ የተነሱትን ፎቶ እንዳየሁት ነግሬያት

ማስፈንጠሪያዉን ተጭና እንድታይ ነግሬ የፌስቡክ ፓስዎርድ

መስረቂያ ሊንክ (Pheshing link) ላኩላት። ይመስለኛል አሁን

ፖስወርድና ኢሜይሏን አስገብታለች። አሁን ከመስረቂያ ሊንኩ

ጋር በተያያዘዉ ጂሜይል አካዉንት ሁሉም መረጃ ፊርደዉስ እጅ

ላይ ይገባል።

ወዲያዉ ለፊርደዉስ ያደረግኩትን በቴክስት ሚሴጅ ነገርኳት።

እሷም የጂሜይል አካዉንቱን ቼክ አድርጋ መረጃዉ እጃችን ላይ

መዉደቁን አበሰረችኝ። በነጋታዉ ተገናኝተን ጉዱን ለማየት

ተቀጣጠርን።

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/abpdfs

ነጫጭ ጥቁረቶች

ክፍል አስራስምንት

(ፉአድ ሙና)

.

.

አይነጋም የለ ምሽቱን መንጋቱን በመናፈቅ ስገላበጥ አሳለፍኩት!

የንጋት የስግደት ጥሪ ድምፅ መሰማት ሲጀምር ወደ መስጂድ

አቀናሁ። የሰፈሩ ፀጥታ ደስ ይላል። ከራሴ ጋር ክርክር ዉስጥ

ገባሁ! አዩቤ መልዕክት መላላኬን እንዳያዉቅ ከቫይበር ላይ

እኔና ኢክሩ ያደረግነዉን ምልልስ አጥፍቼዋለሁ። ስልኩን

ያለአግባብ በመጠቀሜ ሌላ ቀን ሰበብ ፈልጌ ይቅርታ ለመጠየቅ

ወሰንኩ።

የንጋት ስግደት እንደተጠናቀቀ ፊርደዉስ ጋር ደወልኩ። ገና እንዴ

እንደጠራ አነሳችዉ።

"ፊዉዛኔ ለሊቱን እንደ አክሱም ቆመህ አደርክ አይደል?" አለችኝ

እየተፍለቀለቀች

"ፊርዱ ተገናኝተን አካዉንቷን እስክንበረብረዉ ልቤ ተሰቅሏል።"

አልኳት ፉገራዋን ችላ ብዬ!

ቁርስ እንደምትጋብዘኝ እና በዛዉም የኢክራምን ጉድ ለማየት

ከአንድ ሰዓት በኋላ መጥታ እንደምትወስደኝ ነገረችኝ። ፊርዱ

ጠዋት ላይ ማንበብ ስለሚያስደስታት በጊዜ ነበር የምትነሳዉ!

.

ባለችኝ ሰዓት መጥታ ወሰደችኝ። ግን የወሰደችኝ ወደ አንድ

የማላዉቀዉ ቤት ነበር።

ከመኪናዉ ሳልወርድ "የማን ቤት ነዉ?" አልኳት።

"ኦፊስ ነዉ ባክህ! ቤት መሆን ሲደብረኝ እዚህ እመጣለሁ። እኔና

ሜሮን ነን የተከራየነዉ!" አለችኝ።

ብቻችንን አንድ ቤት ዉስጥ መግባታችን አግባብ አለመሆኑን

ባዉቅም የኢክሩን ጉድ ለማየት ስለጓጓሁ ከመኪናዉ ወርጄ ወደ

ቤቱ ገባሁ።

ቤቱ ሁሉም ነገር የተሟላለት ነዉ። ሳሎኑ ላይ ሶፋ አለ። መኝታ

ቤቱ ዉስጥ አልጋ እንዲሁም የኢንተርኔት መቀበያ ኬብሎች

የተገጠሙበት ጠረጴዛ ላይ ደግሞ ላፕቶፕ አለ።

"እዚህ ነዉ ብዙዎቹን እቅዶቼን የምነድፈዉ!" አለችኝ ወደ መኝታ

ክፍሉ እየጎተተች እያስገባችኝ።

ወዲያዉ ላፕቶፑን ከፍታ ማታ የሰረቅነዉን ኢሜይል እና

ፓስወርድ አስገባች። ልክ ሲከፈት ወደኔ እየዞረች "ይሄ ነዉ

አይደል ፈዊ? ና እየዉ!" አለችኝ።

አዎ የኢክራም አካዉንት እጃችን ላይ ወድቋል። ወዲያዉ

በፍጥነት ፍቅረኛዋን ለማወቅ ሚሴጅ ዉስጥ ገባሁ። ብፈልግ

ብፈልግ የተለየ ሰዉ የለም! ከማዉቃቸዉ ሴቶች እና ወንዶች ጋር

ነበር የምትግባፈዉ።

ወይኔ ብልግናዬ! ኢክሩ ልታናደኝ ነበር ፍቅረኛ ይዣለሁ ያለችኝ

ማለት ነዉ?

.

"ምን አገኘህ ፊዊዬ?" አለችኝ ፊርዱ ቁርስ ልትሰራልኝ ኪችን

ዉስጥ እየተንጎዳጎደች።

"ባክሽ ጥርጣሬዬ ትክክል አልነበረም! ማንም የማላዉቀዉ ወንድ

የለም!" አልኳት ለሷ እንዲሰማት ድምፄን ጮክ አድርጌ።

ፊርዱ ቁርስ መስራቱን ጨርሳ እስክትመጣ ኢክሩ ከማዉቃቸዉ

ሰዎች ጋር የተለዋወጠቻቸዉን መልዕክቶች ለማንበብ አሰብኩ።

መጀመሪያ ላይ የአዩብን አገኘሁት ስከፍተዉ ሰላምታ እና ምክር

ነዉ። እሱ ይመክራታል እሷ ልክ ነህ ትለዋለች። ትንሽ

ተዝናናሁበት።

ቀጣይ ላይ ብሩኬ አለ! የኔዉ ጉድ! ደሞ ብሩኬ ምን እያለ

እየመከራት እንደሆነ ለማየት ምልልሳቸዉን ከፈትኩት።

የመጨረሻዉ መልዕክት "አራት በላሽ?" ይላል! ከብሩኬ የተላከ

ነበር። አይ ብሩኬ እየፎገራት መሆን አለበት። መልዕክቶቹን

ወደኋላ እየመለስኩ አነበብኳቸዉ።ቀስ በቀስ እንደ ድንጋይ ደርቄ

ቀረሁ!

"አፈቅርሀለሁ የኔ አይጥ!"

"እኔም እወድሻለሁ የኔ እብድ!"

"ቆይ በኔና ባንቺ መሀል የፈጠዛንን ያረጀ ታሪክ የሚያዉቅ ማን

አለ?"

"ሪሀና እና ሄኖክ ብቻ!"

"እርሺያቸዉ ባክሽ! ፈጠዛን እንደሆነ ሞኝ ነዉ አይጠረጥረንም!"

"በቃ ረሳኋቸዉ! የኔ ጣፋጭ"

"በርዶኛል አትመጪም?"

"መጥቼስ?"

"እቅፍ አደርግሻለሁ!"

"እቅፍ ብቻ?"

"ኧረ እናግለዋለን አንቺ ብቻ ነይ!"

ከዚህ በላይ ማንበብ ከበደኝ። በምድር ላይ የማምናቸዉ ሁለት

ሰዎች እኩል ከዱኝ። ብሩኬ! እኔ እኮ ለሱ የአስር ዓመት ጓደኛዉ

ነበርኩ። እኔ እኮ ለኢክሩ ማንም ከሚያዘንላት በላይ የማዘንላት

እና የምሳሳላት ሰዉ ነበርኩ። ምናለ ባልጠፋ ወንድ ብሩክን?

የፈጣሪ ያለህ! ብሩኬ ስንት ነገር አብረን እንዳላሳለፍን ለአንዲት

ሴት ብሎ ጓደኝነታችንን ናደዉ? መታመን ካለመቻል በላይ

ዉድቀት የለም። ከህደት የትንሾች ባህሪ ናት። ታላቅ ሰዉ መቼም

አይከዳም! እንቢ ለጓደኝነቴ ይላል! እና ብሩክ ትንሽ ሰዉ ነዉ

ማለት ነዉ? እና ኢክራም ትንሽ ሰዉ ናት ማለት ነዉ? ያሳዝናል!

ቆይ ኢክሩ ይህ ሁሉ የፍቅር ዉዳሴዋ ተረስቷት ፣ እነዛ ሁሉ ዉብ

ጊዜያት ተዘንግተዋት እኔን ከልቧ ማህደር ፍቃ ጓደኛዬን

አፈቅርሀለሁ ስትል ፈጣሪን እንኳ አልፈራችም? ለነገሩ እኔንም

ከትዳር ዉጪ አፈቅርሀለሁ ስትለኝ ፈጣሪን አልፈራችም ነበር።

ምን እያሉ ቀለዱብኝ ይሆን? ምናልባት ብሩኬ እየዘፈነ እሷ

እያጨበጨበች እንዲህ ብለዉ ይሆናል።

"ባልሽ ግን ሞኝ ነዉ፣ እኔ እወደዋለሁ!

እሱ ባያመጣሽ የት አገኝሻለሁ።"

ደግሞ እሱ እያጨበጨበ እሷ እያዜመች

"ጓደኛህ ሞኝ ነዉ ፣ እኔ እወደዋለሁ!

እሱ ባያመጣህ የት አገኝሀለሁ።" የሚባባሉ ይመስለኛል።

.

የክህደታቸዉ ተራራ ላይ ተኮፍሰዉ እኔን እንደሞኝ አይተዉኝ

ይሆናል። እኔ ለኢክሩ መልካም መሆኔን እና የኢክሩን ክብር

መጠበቄን እንደሞኝነት ቆጥረዉ ተዘባብተዉብኝ ይሆናል። እነሱ

ያልተረዱት ግን በመልካምነት እና በሞኝነት መካከል ልዩነት

መኖሩን ነዉ። እኔ እነሱ መልካም እንደነበርኩ እንዲረዱት ብዬ

መጥፎ አልሆንም! ለፍቅራቸዉ ያልተቀየረዉ አቋሜ

ለጥላቻቸዉም እጅ አይሰጥም። ኢክሩ እኮ ጨዋ ነበረች። እንኳን

እኔ ስለሷ የነገርኩት በሙሉ የሚወዳት ሴት ነበረች። በመቼዉ

ክብሯ ተገፎ እንዲህ ርካሽ ሆነች?

እኔ የሳምኳቸዉን ከንፈሮቿን ብሩክ ነካቸዉ? ቅፍፍ አለኝ። እኔ እኮ

የማግባት አቅም ሲኖረኝ መጀመሪያ ማግባት አለማግባቷን

ላጣራ የወሰንኩት ኢክራምን ነበር። አክብሬያት ከህሊናዬ ቤተ

መንግስት ዉስጥ ንግስት አድርጌያት ነበር። እሷ ግን የንግስትነት

ክብሯን አሽቀንጥራ ከስድ ባሪያዬ ጋር የኩበት በረት ዉስጥ

መኖርን የመምረጥ ያህል ረከሰች።

ህልሜን ሁሉ አበላሸችዉ! ረከሰች እና ለክፍታዬ አልመጥን

አለች።

.

ሰዉነቴ ተንዘፈዘፈ። ጣቶቼ የላፕቶፑን ማዉዝ መዳሰስ አቃታቸዉ።

እየተንሰቀሰቅኩ መሬት ላይ በግንባሬ ተደፋሁ። ጌታዬን

አመሰገንኩት። ብሩክን ሩቅ ሳልጓዝ ማንነቱን አሳወቀኝ። ለትዳር

የማስባት ሴት ለክብሬ እንደማትመጥን አሳየኝ። ምንም ነገር

ቢወስድብኝ በተሻለ ነገር ሊተካልኝ ቢሆን እንጂ

የማይወስድብኝን ጌታ አመሰገንኩት። ጌታዬ ከኢክራም የተሻለች

ሴት ቢወስንልኝ ነዉ። አመሰገንኩት። እየተንሰቀሰቅኩ

አመሰገንኩት። ከጌታዬ በቀር እንዲህ ላምነዉ የሚገባ ሰዉ
አለመኖሩን ሊያስተምረኝ እንዳደረገዉ አሰብኩ።
በግንባሬ ከተደፋሁበት ተነስቼ ስለ ኢክራም አሰብኩ። እሷ
እንዲህ ከሆነች ሌላ ሴት ማን ይታመናል? አልኩ በልቤ።
አልጋዉ ላይ በጀርባዬ ተዘረርኩ። ከዚህ በፊት ብሩኬን ኢክራም
ፍቅረኛ እንደያዘች የጠረጠርኩ ቀን ሳማክረዉ "የራሷን ህይወት
ትኑርበት! ተዋት!" ያለኝ ትዝ አለኝ። በርግጥ ከዛ ቀን በኋላ
ብሩኬን ምንም ነገር አላማክርኩትም ነበር። ጥርጣሬ ዉስጥ
ገብቼ ነበር። ግን ጓደኛዬን መጠርጠር ብልግና ነዉ ብዬ
ረሳሁለት። ብሩክ እና ኢክሩን መንገድ ላይ አብረዉ አግኝቻቸዉ
አዉቃለሁ። ግን ድረዊንግ ልስልላት ነዉ ስለሚለኝ እና በፍፁም
ብሩኬ እንዲህ ይከዳኛል ብዬ ስላልገመትኩ
አልጠረጠርኳቸዉም። እህቴ ብሩክን እና ኢክሩን መንገድ ላይ
በተደጋጋሚ አየኋቸዉ ትለኝ ነበር። ግን ብሩኬን እንዴት
ልጠርጥር? ኢክሩ ይህ ሁላ የፍቅር ሙገሳዋ በክህደት
ይታጠባል ብዬ እንዴት ላስብ? እሺ እኔን ትተወኝ! የጓደኛዋን
የሪሀናን የቀድሞ ፍቅረኛ ማማገጥ ምን የሚሉት የክህደት
ጀብዱ ይሆን?
እሱም የቀድሞ ፍቅረኛዉን የሪሀናን ጓደኛ እና የአስር አመታት
ጓ

ደኛዉን የእኔን የትዳር ቅዠት ሲያማግጥ ህሊናዉ እንዴት ዝም
አለዉ? ደግሞ እኮ ቃል በቃል "ኢክሩ እንድታገባ እንጂ ከማንም
ወንድ ጋር እንድትንዘላዘል አይደለም የተዉኳት!" ብዬዋለሁ።
አደራ ብዬዉም ነበር! ጌታዬ ሆይ በከለከልከኝ መንገድ ላይ
ተጉዤ የነገድኩት ንግድ ኪሳራን እንጂ አላተረፈልኝም!

.

ፊርደዉስ ቁርሱን ሰርታ አቀራርባ እንድንበላ ልትጠራኝ ስትመጣ

አልጋዉ ላይ ተዘርፊያለሁ። ከአይኔ እንባ ይጎርፋል።

እንሰቀሰቃለሁ።

"ፈዉዛዬ ምን ሆንክብኝ?" አለች እየተንደረደረች መጥታ አንገቴን

ቀና እያደረገች።

በጣቶቼ ላፕቶፑን ጠቀምኳት። ሄዳ አነበበችዉ። ፊቷ ደም

እንደለበሰ ወደኔ ዞራ "ብሩክ አንተን ከዳህ?" አለችኝ ስለ ብሩክ

ታዉቅ ነበር።

ፊርደዉስ ከኔ በላይ መበሳጨት ጀመረች።

"ለኢክራም እኮ መልአክ ነበርክ ፈዊ! ምላሿ ይሄ ነዉ?" አለችኝ

ንዴቷ ይበልጡኑ እየተቀጣጠለ።

አልጋዉ ላይ ከወገቤ ቀና ብዬ ተስተካክዬ እየተቀመጥኩ "ብዙ

ጊዜ ያለመድሽዉ ዉሻ ነዉ የሚነክስሽ!" አልኳት።

"ፈዊ ኢክሩን ቆንጆ ቅጣት ልትቀጣት ይገባል!" አለች ፊርደዉስ

ግድግዳዉን እየደበደበች

እንደ እብድ ጮክ ብዬ እየሳቅኩ "ኢክራም እኮ ቅጣት

አያስፈልጋትም እኔን ከድታ ብሩኬ ላይ የወደቀች ቀን ራሷን

ቀጥታለች። ንፁህ ልቤን ረግጣ ፊልም ላይ ስትመለከተዉ

የኖረችዉን ዝቅጠት ለመተግበር ስትሞክር እና ከቅዱሳን ተራ

ስትወጣ ያኔ ራሷን ቀጥታለች። እኔ መቅጣት አይጠበቅብኝም።

የሚታዘንላት ለንግስትነት የታጨች ዉብ ከመሆን ማንም

እንዳሻዉ የሚጨልፋት ርካሽ መሆንን ስትመርጥ ያኔ ራሷን

ቀጥታለች።" ንግግሬ ሲያልቅ ሰዉነቴ መንዘፍዘፍ ጀመረ።

እየተንሰቀሰቅኩ አለቀስኩ። በህይወቴ እንዲህ ያለቀስኩባቸዉ

ቀናት ዛሬ እና ኢክሩ ልታገባ ስትል ናቸዉ። ሁለቱም በኢክሩ

ምክንያት! ደካማ ጎኔ ሴት ናት! ከሴት ደግሞ ኢክራም!

ፊርደዉስ ለቅሶዬ ሲበረታ አልጋዉ ላይ ከጎኔ ቁጭ ብላ ማባበል

ጀመረች። በእጆቿ እንባዬን ጠረገችልኝ። ደንዝዣለሁ።

ብደበደብም የሚሰማኝ አይመስለኝም። ፊርደዉስ እጆቿን ወደ

አንገቴ ወሰደቻቸዉ። ከንፈሬ ላይ ተለጠፈች። እኔ አያታለሁ

ላስቆማት አልቻልኩም ደንዝዣለሁ! አይኔ እያየ ስልኳን አዉጥታ

ከንፈሬ ላይ እንደተጣበቀች ሰልፊ ፎቶ አነሳች። ፊርደዉስ

ዉርርዷን ፈፀመችብኝ። አደነቅኳት። ምንም የስነ አእምሮ ምሁር

ብትሆን ሴት ልጅን ተንኮል አትበልጣትም። ዛሬ ካፌ ሳይሆን ቤት

እንድንገናኝ ያደረገችዉ አጋጣሚዉን ለመጠቀም ብላ ነበር።

በንፁህ አእምሮ ብሆን ኖሮ ሁሉም ይገባኝ ነበር። ግን

የኢክራምን ጉድ ለማየት መጓጓቴን ፊርዱ ተጠቀመችበት።

ፊርዱ ባደረገችዉ ነገር ምንም አልተቀየምኳትም። እልህ

ተያይዘን ነበር! እሷ አሸነፈች አለቀ!

አእምሮዬ ሲረጋጋ ፊርዱን በአክብሮት እንድታቆም ጠየቅኳት።

ወዲያዉ አቆመች። አየኋት ቆንጆ ናት! ከኢክራምም የበለጠች

ቆንጆ! ግን በሰዓቱ በፍፁም ስለሴት ማሰብ ስላልፈለግኩ ትቻት

ወደ ሳሎን ሄድኩ። ፊርዱ የሰራችዉ ቁርስ ላይ እልሄን

ተወጣሁበት! ፊርዱም መጥታ አብረን በልተን ተያይዘን ከቤቱ

ወጣን!

.

ይቀጥላል...

https://telegram.me/abpdfs

ነጫጭ ጥቁረቶች

የመጨረሻዉ ክፍል

ክፍል አስራዘጠኝ

(ፉአድ ሙና)

.

.

ፊርደዉስ የተሰማኝን መሰበር ስለተረዳችዉ ያን ሰሞን ከጎኔ

አትጠፋም ነበር። ትምህርት እየቀረች ሁላ እኔ ትምህርት

የሌሎችን ሰዓቶች አብራኝ ታሳልፋለች። የኢክራም መንፈስ

እየለቀቀኝ ነዉ መሰል ግጥም ፃፍኩ! ለፊርዱ አነበብኩላት

"ፀሀዩ ጠቋቁሮ ፣ ሰማይ ጠል ለበሰ፣

የክህደትሽ ክፋት ብዕሬን ነቅንቆ ጉድሽን አዳረሰ።

ዱላ አልማዘዝም ከድታኛለች ብዬ፣

እችልበታለሁ በብዕር መቅጣቱን በፍቅር አባብዬ"

.

እኔ ከጀርባዬ ሲሰራ የነበረዉን ድራማ እንዳወቅኩ ብሩኬም ሆነ

ኢክራም እንዲያዉቁ አልፈለግኩም። ትንሽ ጊዜ ብሩኬ እና

ኢክራም ላይ መዝናናት ፈለግኩ። ብሩኬን እንደድሮዉ በስርዓቱ

አገኘዋለሁ! ቤቱ ሳይቀር እየሄድኩ አብሬዉ አሳልፋለሁ።

የማዉቃቸዉን ነገሮች እጠይቀዋለሁ፣በዉሸቱ እዝናናለሁ።

ኢክራምን ፌስቡክ ላይ እንደድሮዉ አወራታለሁ። ልክ ምንም

እንዳልተፈጠረ! በነገራችን ላይ ፊርዱ የኢክራምን የፌስቡክ

ፓስወርድ አሳይታኝ ስቄ አላባራሁም። "ብሩክ" ነበር ፓስወርዷ!

ብሩክ የሚል ስም ይዞ አሁን ሰዉ እንደዚህ አይነት ተግባር

ይፈፅማል? ለነገሩ በስም ከተባለ የነብይ ስም ይዘዉ እንዲህ

ርካሽ ተግባር የሚፈፅሙም አይጠፉም። እምነት አንዴ ከተሸረሸረ

መልሶ ማምጣት አይቻልም። ፈረንጆቹ እምነት እንደ ድንግልና

ነዉ አንድ ጊዜ ከጠፋ መልሶ ማምጣት አይቻልም! የሚሉት

ለዚህ ይመስለኛል።

ጊዜዉ እየገፋ ሲመጣ ህመሙን ዉስጤ ማመቁ ስለሰለቸኝ

ብሩኬን ላናግረዉ ወሰንኩ።

.

ብሩኬ ጋር ደወልኩለት! እነ ሄኖክ ሰፈር እንደሆነ እና ሲመለስ

እንደሚደዉልልኝ ነገረኝ። እነ ሄኖክ ሰፈር ማለት እነ ኢክራም

ሰፈር ማለት ነዉ። ከሷ ጋር እንደሆነ እርግጠኛ ሆንኩ። ሲመለስ

ደወለልኝ። አገኘሁት። ሳየዉ ሳቄን መቆጣጠር አቃተኝ።

እየሳቅኩ "የት ነበርክ?" አልኩት።

በጥርጣሬ አይን እያየኝ "እዚሁ ነበርኩ ባክህ ማደያዉ ጋር!"

ምናምን ብሎ ቀባጠረ።

ዛሬ እዉነት እዉነቷን እንድናወራ ስለፈለግኩ በአይኔ የት

እንደነበረ እንደማዉቅ የሚያሳይ ምልክት ሰጠሁት። የስነ አእምሮ

ተማሪ ነኝ! ሰዉን በንግግሩ ዉስጥ ችግሩን ተረድቶ ማከም ነዉ

የምማረዉ።

ያወቅኩ መሆኑን ስለጠረጠረ እየሳቀ! "ባክህ ከሚስትህ ጋር

ነበርኩ!" አለኝ። የሚስትነት ስሟን ለኔ፣ ተግባሩን ደግሞ ለሱ

ከፋፍሎት መሆን አለበት ከሚስትህ ጋር ያለኝ!

"ሚስትህ ስትል አስታወስከኝ ባይዘዉይ ስሞኑን የሆነ ሰዉ

አካዉንቷን ሀክ አድርጎት ነበርና ከብዙ ሰዉ ጋር ያደረገቻቸዉ

ምልልሶች በሶፍት ኮፒ ተዘጋጅተዉ ሊላኩልኝ ነዉ!" አልኩት።

ብሩኬ ደነገጠ! "ማነዉ ይሄ ባለጌ የሰዉ አካዉንት ሀክ

የሚያደርገዉ?" አለኝ እየተበሳጨ። በዉስጤ እስቃለሁ።

"አላወቅኩም ግን የሚጠቅምህን ነገር አግኝተንበታል ነዉ ያሉኝ!

እነሱ ከኔ የሚፈልጉት ነገር ስላለ ጊቭ ኤንድ ቴክ መሆኑ ነዉ!"

አልኩት ፊቱን እያነበብኩ።

ከብሩኬ ጋር እያወራን የነበረዉ ዎክ እያደረግን ነበር። ዎክ

እያደረግን እነ ረዊና ቤት አካባቢ ደረስን!

ብሩኬ ወሬ ለማስቀየር ይሁን አላዉቅም "አንተ ግን እምነትን

ልብላት ስልህ እምቢ አልክ አይደል?" አለኝ። የረዊናን እህት

እምነትን ነዉ።

ፈገግ ብዬ "ብሩኬ ቆይ ስንቱን ልተዉልህ?" አልኩት!

ብሩኬ እንደድንጋይ ደርቆ "ማንን ተዉክልኝ?" አለኝ።

እየሳቅኩ "ከእምነት ሌላ ምድር ላይ ያሉትን ሴቶች ሁሉ

ትቼልህለሁ!" ብዬ አስቀየስኩ።

.

ብሩኬ የኢክራም አካዉንት ሀክ መደረጉ በጣም አንገብግቦታል።

"ፈዊዬ ጓደኛህ አይደለሁ! ቢያንስ የኔን እንዳይልኩልህ አድርግ!"

አለኝ።

"ያንተማ ቢላክልኝም ምንም ሚያስጨንቅህ ነገር የለም። እኔ ነኝ

ማነዉ! አንተ ከኔ ደብቀህ ከኢክራም ጋር የምታወራዉ ነገር

ስለሌለ አትጨነቅ።" አልኩት።

ከጀርባዬ ጭንቅላቱን ይዞ ቆሞ "ፈዉዛኔ ካነበብከዉ ያጣላናል!"

አለኝ። የእዉነት እኔን ከመረጠ መጀመሪያ እሷን እንቢ አይልም

ነበር! አንቺዉ ታመጨዉ አንቺዉ ታሮጨዉ አሉ!

መጫወቱ ሲበቃኝ ወደ ብሩኬ ዞር ብዬ አይን አይኑን እያየሁ

"ግን ምኗን ወደድከዉ?" አልኩት።

ብሩክ ሁሉንም ማወቄን አረጋገጠ። "በቃ ሁሉንም እነግርህለሁ!"

አለኝ።

ድራማዉ ከጀርባዬ ላለፉት ስምንት ወራት እየተተወነ እንደነበር

ነገረኝ። ኢክራም ስለምታሳዝነኝ ነዉ ምናምን ብሎ ቀባጠረ!

የእዉነት ቢያዝንላት የኔን ዉሳኔ እንድትተገብር ነበር ሊያበረታታት

የሚገባዉ።

"ብሩኬ እኔ ይቅርታ አድርጌልሀለሁ! ኢክራምን የምትወዳት ከሆነም ግንኙነታችሁን መቀጠል ትችላላችሁ!" አልኩት።

ብሩኬን ላለፉት አስር አመታት አዉቀዋለሁ! በአንድ ሴት ምክንያት በቃኝ ልለዉ አልችልም። ምንም ዛሬ ቢከዳኝም ብዙ ከባባድ ጊዜዎቼን አብራዉ አሳልፌያለሁ። ለኔ መልካም ሰዉ ነበር። ግን አንድ ፈተና ማለፍ አቃተዉ።

.

በቀጣዩ ቀን ከብሩኬ ጋር ተገናኝተን ስናወራ ስለሷ አዉርቶ መዘባረቅ ሲጀምር "ቆይ ግን እኔን እንደዛ እወድሀለሁ እያለች የከዳችኝ ኢክራም አንተን ዞራ እወድሀለሁ ስትልህ ነገ ወደ ሌላዉ እንደማትዞር በምን እርግጠኛ ሆንክ? ቢያንስ በኔ አትማርም?" አልኩት።

"ባክህ እኔ አልወዳትም!" አለኝ።

"ታዲያ ለምን እሺ አልካት?"

"እሷ እወድሀለሁ አለችኛ!"

በጣም ተበሳጨሁ! ቢያንስ ኢክራምን ወዷት ሴትነቷ አሳስቶት ቢከዳኝ እሺ! ግን እንዲሁ ለመንዘላዘል ነዉ ከህደት የሰራብኝ? ከምር አበሳጨኝ! እምቢ ማለት አለመቻል ትልቁ ዝቅጠት ነዉ።

ጠጣ እሺ! ቃም እሺ! ጓደኛህን ክዳ እሺ! በጣም ያሳፍራል።

ከብሩኬ ጋር እንደድሮዉ ለመሆን ብሞክርም በፍፁም ሊሳካልኝ አልቻለም። እምነት ከተሸረሸረ ትልቅ አደጋ ነዉ።

.

ኢክራም ያደረገችዉ ነገር ምንም አስቀያሚ ቢሆንም ልቤ ዉስጥ ቅንጣት ጥላቻ ሊፈጠር አልቻለም። አሁንም በጣም ታሳዝነኛለች። ምናልባት ፈጣሪዬ ከሱ ቀድቼ ለኢክራም

የተናገርኩትን ወዶልኝ ይሆን? "ያለፈዉንም የሚመጣዉንም

ጥፋትሽን ይቅር ብዬሻለሁ!" ያልኳትን። አይ እንደዉም የወደፊቱን

ይቅር ማለት ከሱ ሌላ ማንም እንደማይችል እያሳየኝ ነዉ

የሚሆነዉ! ግን አሁንም ለኢክራም ያለኝ እዝነት አልቀነሰም።

አንድ ቀን ሁሉንም ነገር ማወቄን ፌስቡክ ላይ ነገርኳት። በጣም

ደነገጠች። እኔ አሁንም የድሮዋን ጨዋዋን ኢክራም ለመሆን

ብትሻ ላግዛት ዝግጁ ነኝ። ግን ኢክራም ክህደቷን መቋቋም

አቃታት መሰለኝ ከፌስቡክ ብሎክ አደረገችኝ። የተበደልኩት እኔ!

ዘራፍ ባዩ ሌላ! ይገርማል። ፈጣሪዬ ግን ማገናኘት ካሻዉ ማንም

አያግደዉምና ብሎክ ባደረገችኝ በነጋታዉ መንገድ ላይ

ተገጣጠምን። ዉስጤ ላይ ምንም ጥላቻ የለም። ልክ

እንደድሮዉ ፈገግ አልኩላት! ፈገግታዬን ስታይ ወደኔ መጣች።

ሰላም ከተባባልን በኋላ ስለትምህርቷ አወራን! እሷ ግን

ከመወዛገቧ የተነሳ ስለያዝኩት ቦርሳ ዘባረቀች። ኢክራምን

ከረጅም ጊዜ በኋላ በአካል አገኘኋት! እንደሚሉት የተጋነነ

የአለባበስ ለዉጥ አላስተዋልኩም! በርግጥ ጅልባቡ ወልቆ

ቀሚሱም ጠቧል። የጠበቅኩት የተጋነነ ስለነበር ነዉ መሰለኝ

ብዙም አልደነገጥኩም!

.

አሁን የሚቆጨኝ እኔ ስበላሽ ከጎኔ ሆና ያረመችኝን ኢክራምን

ዛሬ የክህደት እና የስነ ምግባር ዝቅጠት ዉስጥ ስትዘፈቅ

ልታደጋት አለመቻሌ ነዉ።

ለሰዉ ልጅ ክብር ወሳኙ ነገር ከማንነት መስመር የወጣን

አፈንጋጭነት እንቢ ማለት መቻል ነዉ።

የመጀመሪያዉ ስህተት የኔ ነበር! ከፈጣሪ ትዕዛዝ ዉጪ ሴት

ስተዋወቅ! ህይወቴ ዉስጥ ልጨምራት ከፈጣሪ ተጋፍቼ

ያመጣኋት ኢክራም የነበረኝን ብሩክንም አሳጣችኝ። ጌታዬ ልክ

ነበር! ተሳስቶም አያዉቅም! አይሳሳትምም!

ኢክራም ዛሬም መልካም ለመሆን ቅንጣት እንኳ አልረፈደባትም።

ወደለመዱት መል

ካምነት መመለስ ለኢክራም አይከብድም።

ዛሬም የኢክራምን መልካም ስብዕና እናፍቃለሁ። የጋብቻ የጥሪ

ካርዷን ስትልክልኝ አልማለሁ! እሷ ራሷ ከዘቀጡበት ፈልጋ

ሰብስባ ያፀዳቻቸዉ ነብሶች ዛሬ እሷን እንደመታደግ

ሲጠቋቆሙባት ሳይ አበሳጫለሁ። ኢክራም ከነክህደቷ ብዙ

ንፁህንን አፍርታለች። በጨዋዋ ኢክራም እጅ ንፅህናን የተቀበሉ

በሙሉ ኢክራምን ወደነበረችበት ከፍታ የመመለስ ግዴታ

አለባቸዉ።

ብሩኬም መልካም ለመሆን ጊዜዉ አልረፈደበትም። ብሩኬ

ለመበላሸቱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ለማጤን ሞክሬ ነበር።

ዋናዉ ፊልም ነዉ። ፊልሞቹን በክፊል ወስጇ ተመለከትኳቸዉ።

ስሜት ተኮር ናቸዉ። "የሰዉ ልጅ የተመለከተዉን ነገር

ይተገብራል" ይላል ስነ አእምሮ! የሰዉ ልጅ ባህሪዉን

የሚገነባበት አንዱ መንገድ ሲደረግ ያየዉን በመማር

(imitation) ነዉ። ብሩክ ለመበላሸቱ ይመለከታቸዉ የነበሩት

ፊልሞች ግንባር ቀደም ምክንያት ናቸዉ።

ሁለቱም ሰዎች ናቸዉ ተሳሳቱ! እኛ ስህተት ባይኖርብን ፈጣሪ

እኛን አጥፍቶ ሌሎች የሚሳሳቱ ህዝቦችን ይፈጥር ነበር። ግን

ዋናዉ ነገር ጥፋትን ተረድቶ ለመፅዳት መሞከር ነዉ። ጥፋቱ

ከህደት ሆኖ ወንጀላቸዉን አገዘፈዉ እንጇ ብዙ መልካም ነገር

ይኖራቸዋል።

.

ብርጭቆ መሬት ላይ ወድቆ ሲሰበር ከነበርኩበት የሀሳብ

ሰመመን ነቃሁ! አንዱ ጠረጴዛ ላይ ያሉት ጥንዶች ናቸዉ

የሰበሩት። ካፌዉ ዉስጥ አራቱ ቴብሎች ላይ ጥንዶች

ተቀምጠዋል። ረሂማ እየሳቀች ወደኔ መጣች! ከኪሴ ልከፍል

ብር እያወጣሁ ነበር።

ረሂማ እየሳቀች "ወተቱስ?" አለችኝ።

ወይኔ ለካ ቅድም ልታሞቀዉ ወስዳዉ ነበር እርስት

አድርጌዋለሁ።

"እሺ የታለ?" አልኳት እየሳቅኩ!

"አሙቄዉ እዛ ቴብል ላይ ወተት ታዞ ነበር እና ለሱ የታዘዘ

መስሏቸዉ ወሰዱት! አንተም ሙድህ ስለወረደ አዉቄ ነዉ ዝም

ያልኩህ!" አለችኝ እየሳቀች።

.

ካፌዉ ዉስጥ ያሉትን ጥንዶች ተመለከትኳቸዉ! ይስቃሉ

፣ይጎነታተላሉ! እስከሚጣሉ ይጎነታተሉ አልኩ በልቤ! አዎ

ተዋደዱ፣ከነፉ፣ተጣልተዉ አረፉ! ነዉ ከትዳር ዉጪ ያለ ፍቅቅሮሽ

መዳረሻ። ሲከፉም የወንዱም የሴቷም ክብር በዝሙት ይገፈፍና

ለንፁህን የተከለከሉ ቆሻሻ መሆንን ነዉ የሚያተርፈዉ።

.

ፊርደዉስ ደወለችልኝ። አነሳሁት!

"አንተ እዛ መቆዘሚያ ካፌህ ነህ አይደል?" አለችኝ።

"አዎ ምነዉ ፊርዱ?" አልኳት

"በዚህ ስሜት ዉስጥ ሆነህ መጠየቁ አግባብ ይሁን አይሁን

አላዉቅም! ግን ፈዊ ፊቃደኛ ከሆንክ ካንተ ጋር ኒካህ ማሰር

እፈልጋለሁ! ገንዘብ ምናምን የሚለዉ አያሳስብህ ነብዩ

ሙህመድ(ሰዐወ) የመጀመሪያ ሚስታቸዉን ኸዲጃን(ረዐ)

ሲያገቡ እሷ በጣም ሀብታም ነበረች! የእዉነት ሀይማኖተኛ

ከሆንክ ይሄ አይጠፋህም" አለችኝ።

የኔ አንበሳ ይሄን ታሪክ ማወቋ በራሱ አስገርሞኛል። እንዴት

እንዴት ነዉ ያገናኘችዉ? ቆንጆ ፖለቲከኛ ይወጣታል። ደሞ ለሷ

ኒካህ ምን አላት? እድሜ ለአባቷ! ገንዘብ እንደልባ ነዉ። እኔ

የማስተዳድራት እንጂ የምታስተዳድረኝ ሴት ማግባት

አልፈልግም።

"ፊርዱዬ ከኔ ጋር ወንድምነቱ ይሻለናል እሺ! እኔ ለጋብቻ ብቁ

ነኝ ብዬ አላምንም!" አልኳት። ለጋብቻ ብቁ ሆኜ ቢሆንማ

ኢክራምን እስከአሁን አግብቼ ነበር።

"ፈዉዛን እኔ ምን ያንሰኛል? ዉበት ከፈለግክ ማንም አይጠጋኝም

ታዉቃለህ! ገንዘብ አለኝ እንደፈለግክ አድርገዉ! ከማንም እኔ

እሻልሀለሁ።" አለች እየተነጫነጨች። በራስ መተመመኗ እና

ግልፅነቷ በጣም ደስ ይለኛል።

"ፊርዱ እኔ አንቺ ምንም ይንድልሻል አላልኩም ግን እኔ ብቁ

አይደለሁም! ለሌላ ጊዜ ብቁ ስሆን ግን ከዉበትሽ እና ከገንዘብሽ

በላይ ሀይማኖትሽ ላይ ያለሽን አቋም ስለምፈልገዉ እሱን

አሻሽይ!" አልኳት እየሳቅኩ።

"እሺ በቃ እንደድሮዉ!" አለችኝ እንዳንኮራረፍ ፊርታ።

"እሺ ፊርዱ ፊታ በይ!" አልኳትና ስልኩን ዘጋሁት።

ረሂማ ሚስተናገድ ሰዉ የለም መሰለኝ አጠገቤ መጥታ "አንተ

ግን ዛሬ ምን ሆነህ ነዉ?" አለች። መልሴን ሳትጠብቅ ወዲያዉ

ስልኬን ከጠረጴዛ ላይ አንስታ ሰዓት አየች። እግረ መንገዷን

ሰሞኑን የፃፍኩትን ግጥም ዋልፔፐር አድርጌዉ ስለነበር

አየችዉ። እየሳቀች ጮክ ብላ አነበበችዉ

"ስምሽ ጎዳደፈ አነሱሽ በክፉ፣

ከንፈር ማሳበጤ ይሄ ነዉ ወይ ትርፉ?

ደግሜ ብስምሽ ይፀዳ ይሆን ወይ የህሊና እድፉ!"

አሽኮረመመችኝ! ረሂማ ወዲያዉ ተስተናጋጇ ስለመጣ ትታኝ

ሄደች። ወዲያዉ ስልኬ ጠራ! ረዊና ነበረች። አነሳሁት።

"ፊዉዛሄ የት ነህ? አዲስ አበባ መጥቻለሁ!" አለችኝ።

ረዊና ንፁህ እህቴ ናት! ሁሉንም ነገር ለሷ መተንፈስ ነበር

የሚቀለኝ።

"ስማ ከትምህርት ቤቱ ጀርባ ያለዉ ልብስ ቤት ነኝ!

አትመጣም?" አለች!

"መጣሁ!" ብያት ከካፌዉ ተነስቼ ወጣሁ። ከመሸሸጊያዬ ወጣሁ!

የወዳጇ ጦር ቅርብ ርቀት ላይ ነዉ። ንፁህ እህትነት! ረዊና!

.

ተፈፀመ!!

https://telegram.me/abpdfs